በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንዳፍታ



በግፍ የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ

ጥር/የካቲት
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት
ቁጥር ፬

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
Jan/Feb 1997
Vol.5 No.4

**Patrick A. Harton**
*Partner*

**Teketel Wegayehu**
*Legal Asst.*

**Samuel C. Henry**
*Partner*

**G. Angela Harton**
*Office Mgr.*

# HARTON & HENRY

Attorneys At Law

## "A Law Firm Proudly Serving the Ethiopian Community"

በየትም ቦታና ጊዜ ለሚያጋጥምዎ አጠቃላይ የሕግ ችግሮች
ምንም ነገር ከማድረግዎ በፊት በሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት
የታወቀውን የሐርትንና ሔነሪ የጥብቅና ድርጅት
በማነጋገር ለችግርዎችዎ በሙሉ አስቸኳይ መፍትሔ ያግኙ።

- Auto Accident
- Immigration Law
- Personal Injury
- Business Law
- Divorce
- Criminal Law

- Ethiopian National with extensive knowledge of Ethiopian history, laws, language and culture on staff.

## Free Consultation

**70 Fairlie Street, Suite 260, Atlanta, Georgia**

**404◆681◆1800**

# አስቴር አወቀ
## በለንደን
### ቪዲዮ ፤ ሲዲና ካሴት




የባርካንስ
ሬከርድስ
ዝግጅት

**Barkhanns Records**
163 Amesterdam Ave. No.316
New York NY 10023-5001
Tel: (212)969-8646

## ASTER AWOKE
### LIVE IN LONDON
Video & Audio

# ORDER FORM

Name: ______________________

Address: ______________________

______________________

______________________

Phone: ______________________

Please, ship Gift to:

Name: ______________________

Address: ______________________

______________________

Phone: ______________________

| ITEM | Unit Price | Quantity | Total Price |
|---|---|---|---|
| Aster in London (Video) | US $23.00 | | |
| Aster in London (CD) | US $13.00 | | |
| Aster in London (Cass) | US $6.00 | | |
| | | | |
| Ebo CD | US $13.00 | | |
| Ebo Cass | US $6.00 | | |

*Please, add **US $2.00 per item** for shipping & handling in US.*
*Outside USA add **US $ 4.00 per item.***

| | |
|---|---|
| Subtotal | |
| Ship & Hand | |
| Grand Total | |

*Make check or Money Order Payable to:*
Barkhanns Records or
LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359

For Information Call:
(404) 508-4657

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

5 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)
ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)
ሰላምታ ከባህር ማዶ (ይግለጡ)

14 ከአንባብያን

17 እንዲህ ሆነ (ዜናዎች)

21 እንወያይበት
“መከራ ሲመጣ አዋጅ አያስነግርም”
(ከሰብለወንጌል — ሆላንድ)

25 ከትዝታ ከታሪክ ማህደር

26 የግጥም ማህደር

30 ኑሮ በአሜሪካ
“አልፍ ሲሉ እልፍ . . .” (አትናትዮስ)
“የክርስቶስ ተከታዮች . . .” (እያዩ ቢልልኝ)

34 ኤግዚቢሽን በአትላንታ

36 ልብወለድ
“የተራበች ሕይወት” (ሰይፉ አዳነች ብሻው)

42 አዳምና ሔዋን
“ዕጣዬ” (አብረሽት)

44 ዜና ቤተክርስትያናት

45 ከዚህም ከዚያም

46 የሰንጠረዥ ጨዋታ




አፄ አምሐ ሥላሴ



የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ



ባህታዊ ገብረመስቀል
በእስር ላይ እያሉ
ታመዋል ይባላል

ሽፋን — በግፍ የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1997

ላንዳፍታ
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት ቁጥር ፬
LANDAFTA
JAN/FEB 1997 Vol. V- No.4



አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*

**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Gebrie (Pen Name)*
*Wuhib Tiruneh*
*Eyayu Beleigne (pen name)*
*Rev. Mekbib Atnaw*

**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant

Chicago, IL
Ethio-Village Rest.

Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery

Durham, NC
Blue Nile Ethiopian Cusine

Houston
Queen Sheba Rest.
Maru Grocery

L.A., CA
Merkato
Damera

Oak Land, CA
Albo-African Shop

San Diego, CA
Emebet Worku
Axum Market

San Jose, CA
St. Claire news Stand

Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery

St. Louis, MO
A & Z Liquor

St. Paul, MN
Merkato

Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)

Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu


# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል። እኛ ደህና ነን። 1989 ዓ.ም. ከገባ ወዲህ በአገራችን ብዙ ሁኔታዎች ታይተዋል። የአይሮፕላናችን መውደቅ፤ የታምራት ላይኔ መውረድ፤የሱዳንና የወያኔና የሻቢያ ግጭት፤ የባህታዊ በቤተርስትያን ግቢ በታቦት ፊት በጥይት መገደል፤ የ16 ብሔራዊ እግር ኳስ ተጫዋቾች አገር ለቆ መሰደድ፤ በአጭሩ ጎላ ብለው የሚታዩ ናቸው። ይህ አዝማሚያ ወዴት እየወሰደን ይሆን?

ዛሬም ትምህርት አዘል የሆነው የወርቃየሁ ከአገር ቤትና ገብርዬ ደግሞ ከአሜሪካ የሚጻጻፉት የሰላምታ ልውውጥ አለን። ወርቃየሁ የኢትዮጵያውያንን ብዙሃን ድርጅቶች አስፈላጊነት በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባ ይዞልን ቀርቧል። ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፤ ልሣኑ ስምረት፤ ግርማ ዘገየና ሰይፉ ብሻው ደግሞ በሸጋ ብዕሮቻቸው በሳል የሆኑ ግጥሞቻቸውን ጀባ ብለውናል። ሰይፉ ብሻው በደቡብ ኢትዮጵያ ባህል ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ አቅረቦልናል። እያዩ ቢልልኝ በተከታታይ በሃይማኖት ስም የሚደረገውን እሱ በቅርብ የሚያውቀውን ይነግረናል።

በይቀጥላል ከሚፃፉት የገጠመኝ ታሪኮች "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ" የሚለውን የአትናትዮስን ተከታታይ ጽሁፍና የአብረኸትን "ዕጣዬ" ተከታታይ ታሪክ አቅርበናል።

በዚህ አጋጣሚ ጽሑፍ የምታበረክቱልን ቋሚ ጸሐፊዎቻችንም ሆናችሁ ሌሎች በላንዳፍታ ላይ እንዲወጣ የምትፈልጉትን ጽሑፍ ቀደም ብላችሁ እንድትልኩልን አደራ እንላለን።


**ለኢትዮጵያውያን**
**የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች**
**እንኳን**
**ለኢድ አልፈጥር በዓል**
**በደህና አደረሳችሁ እያልን**
**መልካም ምኞታችንን እንገልፃለን!!**



የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- mgessesse@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com.landafta.htm



*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*



# የላንዳፍታ መጽሔት በ1991 ዓ.ም. ከጀመረችበት ከኢሊኖይ ገዥ ከተከበሩ ሚ/ር ጂም ኤድጋር ለአዘጋጁ የተላከ የመልካም መግለጫና የድጋፍ ደብዳቤ

STATE OF ILLINOIS

**OFFICE OF THE GOVERNOR**

CHICAGO 60601

JIM EDGAR
GOVERNOR

February 15, 1997

Mekonnen Gessesse
Editor
Landafta
4050 Seven Hills Court
Stone Mountain, Georgia 30083

Dear Mr. Gessesse:

As Governor of the State of Illinois, it is my pleasure to congratulate you on the 6th anniversary of your publication, Landafta.

Landafta has provided countless African Americans with an excellent source of national and community news. The ethnic media is a vital and integral part of our success in understanding different cultures. You can take pride in the many accomplishments that your publication has achieved.

On behalf of the citizens of Illinois, please accept my best wishes for an enjoyable anniversary and much continued success.

Best regards,

Jim Edgar
GOVERNOR

JE:tmm

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## ከወርቃየሁ

እንደምን ከርማችሁልኛል። ውድ ወገኖቼ፣ እኔ ልበል እንጂ እኛስ ለማለት ችግር ይኖርብኛል። ማን የማን ወኪል አደረገኝና፤ ... እኔ ደግ ነኝ። ምንም አልል። መስሎቼም አሉ እንጂ አልሞቱም። ነፍስ በሥጋ ውስጥ ኖራ የሰውነትን እንቅስቃሴ ስለፈጠረች ሕይወት አለ ከተባለ አለን። ኑሮ ከተባለ ማለት ነው።

«ተው ይህ ነገር አይበጅም፣ ቀና ቀናውን ያዙ» ብለን ብንምህ፣ ብንመክር፣ ብናስመክር፣ ብናድም፣ ብንሰለፍ፣ ብንፅፍ፣ አቤት ብንል፣ ... ወዘተ... የሚሰማን አጣን። ይባስ ብሉ በእግዚአብሔር ቤት ዓለም በቃኝ ብለው በመነኩሱ ባህታዊ ላይ የጥይት ቃታ መሳብ ተጀምሯል። እርር ድብን ብለን ነው የከረምነው። እንግዲህ ለአንድ ባህታዊ የሃይማኖት ይከበር ጥያቄ የጥይት መልስ የሚሰጥ «መንፈሳዊ አባት» ፓትሪያርክ ባለበት አገርና ጊዜ የምንኖር ሆነን ምኑን አለን እንላለን። ከዚህ በፊት አንዳንድ ሰዎች አባ ጳውሎስን «ተጋዳላይ ጳውሎስ»፣ «ካድሬ» እያሉ ሲያወሩና ሲያስወሩ እቆጣ ነበር። «ምንም ቢሆን አባት ናቸው፣ ሽማግሌ ናቸው፣ የቤተክርስቲያን ሰው ናቸው» ብዬ አስብ ነበርና እንኳን በጥይት ሰው ሊያስመቱ ይቅርና የታሰረን ያስፈታሉ ብዬ ነበር የማስበው። ለካ የሚይዙት ትልቁ መስቀል ከውጪ የሚታይ እንጂ ከውስጣቸው ያለው ሌላ ነገር ነበር። ባይገርምህ ዛሬ በአዲስ አበባ ከጠቅላይ ሚኒስትራችን ቀጥሎ በጦር መሣሪያ አጀብ ብዛት «ነፍሳቸውን» ሲያድኑ የሚታዩት እኚሁ ፓትሪያርክ ናቸው። በሰው ሰራሽ ያውም ለሰው መጥፊያ በሆነ መሣሪያና ጥይት ታጅበው የሚሄዱት በእግዚያብሔር ኃያልነትና በእግዚአብሔር ጠባቂነት ቢጠራጠሩ ነው ማለት ነው። ምናልባት ዶክተር ተመራማሪ መሆናቸው ይሆን ለዚህ ጥርጣሬ ያበቃቸው። አይ ኢትዮጵያ የወላድ ድሃ!

አቡኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናንን በእግዚአብሔር ስም ለመጠበቅ በወልደ እግዚአብሔር ስም ምለው የገቡትን ቃል ኪዳን ጥሰው፤ ምዕመናን ከአምላካቸው ይቅርታ በሚጠይቁበት በቤተክርስቲያን አውደ ምህረት፣ በታቦተ እግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሆኑ ባህታዊ ያስገደሉ «አባት» ናቸው። እንግዲህ እኚህ ናቸው ዶክተርነታቸውና አዋቂነታቸው የሚነገርላቸውና ከአሜሪካ ድረስ በባትሪ ተፈልገው የመጡት «ፓትሪያርክ ጳውሎስ» ... ለምን እያስፈልጉ? እንዲህ አይነት አባት እንዲህ በቀላሉ ከየትም እንደማይገኝ ሁላችንም እናውቃለን።

ከሁሉ የገረመን የጦር መሣሪያ በታጠቁ ወታደሮቻቸው መሐል ሆነው «ኢመኑኝ በእግዚአብሔር ስም እነግራችሁዋለሁ፣ እኔ እስከማውቀው የሕዝብን ሰላም የሚነሳ የተፈጠረ ስህተት የለም ...» ብለው ፓትሪያርኩ አባ ጳውሎስ ጥር 7 ቀን ሥላሴ ቤተክርስቲያን የተናገሩት ንግግር ነው። ሟቹ ባህታዊውም ይሁኑ ምን በእግዜር አምሳል የተፈጠረ ሰው በቤተክርስትያን ደጀሰላም በታቦት ፊት በጥይት ሲገደል ምንም ስህተት አልተፈጠረም አሉን አባ ጳውሎስ።

ሌላው የሲኖዶስ ፀሐፊ ተብዬው አቡነ ገሪማ ሲኖዶሱን ሰብስበው "መንግሥት ...በቤተክርስቲያን ከሕግ ውጭ የሚሆኑትን እንዲቆጣጠር" የተማጠኑ ሲሆን ይኸው የ"ሲኖዶስ" ጉባኤ 13 ነጥብ ያለውን የአቋም መግለጫ አወጣ ተብሎ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ መቅረቡን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘግቦት አየሁ። አይገርምም፤ እስቲ መለስ ጋ የሚቀርበው ለምንድነው? ከዚህ በኋላ እንግዲህ እንደ ቤተመንግሥት ቤተክርስቲያንም ስንገባ ልንፈተሽ ነው ማለት ነው። ሲያልቅ አያምር አለች ሴትየዋ!

ብቻ ምናለፋህ ጥር ከመግቢያው ጀምሮ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናትና ምዕመናን ሲታመሱ ነው የከረሙት። ጥር 1 የልደታ ዕለት ባህታዊ ፈቀደ ሥላሴ በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን መገደል ትልቅ ሽብር ፈጠረ። ጥር 4 ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን በዓሉን ለማክበርና ቃለ ቡራኬ ለመስጠት በፖሊስ ታጅበው በቦታው የተገኙት አባ ጳውሎስ «ቡራኬ» ሲሰጡ ሕዝቡ እጁን እያወዛወዘባቸው ተቃውሞውን በመግለፅ «ኃይል የእግዚአብሔር ነው ቡራኬውን አንቀበልም» የሚል ከፍተኛ ጩኸት ተሰምቷል። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ብጥብጥ ተነስቶ ብዛት ያላቸው ምዕመናን በፖሊስ ታፈሱ። ጥር 7 የሥላሴ ዕለት በቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ከተገኙ ምዕመናን መሐል ፖሊስ ወደ 20 የሚጠጉ የቤተክርስቲያኑን ወጣት መዘምራን አፍሶ በመውሰድ እንዳሰራቸው ጋዜጦች ዘግበዋል። ጥር 11 ቀን የጥምቀት ዕለት ጃልሜዳ አባ ጳውሎስ አሁንም በፖሊስ ታጅበው ቡራኬ ለመስጠት ከቦታው ሲደርሱ ሕዝቡ ቡራኬያቸውን ላለመቀበልና ተቃውሞውን ለመግለፅ ምዕመናኑ ጠቅላላ ጃንሜዳን ለእሳቸውና ለደቀመዝሙሮቻቸው ትቶላቸው ሄዷል። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሆነው በዚህችው በጥር ወር ግማሽ ጊዜ ነው። እንግዲህ ወዳጄ ይግለጡ «ይሰውረን ከመዓቱ» ብለን እግዚኦታ ከመግባት በቀር ምን ምርጫ አለን። ይህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ የደረሰው ችግርና እየታየ ባለው ሁኔታ አንዳንድ መጤ ሃይማኖቶች የተደሰቱበት ይመስላል። እንደውም እንደሚወራ ከሆነማ የአባ ጳውሎስ የቅርብ አማካሪያቸው ጴንጤ ነውም ይባላል። ምናልባት እሳቱን የሚጭሩት እነሱ ይሁኑ ሌላ ሰይጣን ሁሉን የሚያይ አምላክ ያውቃል። ለማንኛውም የአገራችን ነገር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየከፋ ሄዷል። ሲከፋን ጊዜ ሳንመርጥ ከአምላካችን የምንነጋገርበት ደጀ ሰላም እያስፈራን ከመጣ ሌላ ምን ቀረን እንላለን? ቢሆንም የተስፋ አገር ልጆች ነንና በክርስቶስ ተስፋ አንቆርጥም። አንድ ቀን አንዱ ሁሉ ነገር ይስተካከል ይሆናል። የዛ ሰው ይበለን!

ወዳጄ ገብርዬ፣ ይህ ነገር አዕምሮአችንን እያብከነከነው እያለ የ16ቱ የብሔራዊ እግር ኳስ ተጫዎቻችን ሮም ላይ መጥፋትና የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቅ ራሳችንን ሲያሳምመን ሰነበተ። ቀደም ሲል በደርግ ጊዜም እንኳ ቢሆን የብሔራዊ ተጫዋቾቻችን ተቃውሞአቸውን ለማሰማት በየሄዱበት አገር ይቀሩ ነበር።

ታዲያ ሁለቱ፣ ቢበዛ አምስቱ ነበሩ እንጂ እንዲህ እንዳለ 16 ተጫዋች ሁሉ በአንድ ጊዜ መጥፋት ተሰምቶም አይታወቅም። መቼም የዚህ ሁሉ ውጤት በአገሪቷ ያለውን የኑሮ ምሬትና ችግር የሚገልፅ መሆኑን እናንተም ሆናችሁ ሌላው የዓለም ሕዝብ ትረዱታላችሁ ብዬ እገምታለሁ። እኔን ያልገባኝ ጨዋታው የሚካሄደው አፍሪካ አገር ሆኖ ምን ሊያደርጉ ሮም ይዘዋቸው እንደሄዱ ነው። ጥፉ ሲላቸው መሰለኝ። ብቻ አንዳንዴ ሳስበው ሰው ሁሉ ሄዶ ሄዶ የቀረነው እነማን ነን እላለሁ? አገር ጠባቂ ወይስ ለሆድ አዳሪ አድር ባዮች!!

እንደው ገብርዬ ዛሬ ገና ከጅምሬ በቁንቅ ወሬ ይዤሃለሁ አንዴ እንደጀመርኩ ልጨርስና ወደ ሌላው እገባለሁ።

ሌላው ትልቁ ስጋታችን ደግሞ የሱዳን ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ጦርነት አውጃብኛለች ብላ ሱዳን ለአለም አስታውቃለች። ይኸው ነካክተው ነካክተው አንድ ትልቅ የጐረቤት ጠላት አትርፈውልናል። ለዚህ ያደረሰቻቸው ሱዳን መሆኗ ቀረና አለቆቻችን ይኸው ውለታ ነካሽ ሆነዋል። ያኔ ደርግ የጆን ጋራንግን ቡድን ይረዳ ነበር። ጋምቤላ ሳትቀር ማሰልጠኛ ሆና እንደነበር ትዝ ይለኛል። ያኔ ጋራንግ ከኤርትራና ከወያኔ ጋር ወዳጅነት አልነበረውምና ከደርግ ጋር ተባብሮ ይወጋቸው ነበር። ዛሬ ጋራንግ ደርግን ከጣሉት ከኤርትራና ወያኔ ጋር ወዳጅነት ገጥሟል። አንዳንዴ ሳስበው የዚህ ፖለቲካ ጉዳይ ይገርመኛል። እንደ ንግድ ነው—ትርፍ በተገኘበት። እናም ወዳጅ አገር የነበረችው ሱዳን ጠላት ሆናለች። እንደገናም ሱማሌ። ብቻ የእኛ መንግስት ከዋናው መንግስት ትቶ ከሸማቂው ከሸማቂው ጋር ለምን ወዳጅነት እንደሚፈጥር አልገባኝም። ለነገሩ እነሱም በኢትዮጵያ ላይ የሸመቁ የአንድ ብሔር ጥርቅም አይደሉ! ለምን አይረዳዱ የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ አሉ!

ወዳጄ ገብርዬ!

ባለፈው የደብዳቤ መልዕክትህ ስለጦቢያው ፀጋዬ አስታከህ የፃፍከው ቁም ነገርና ትምህርት አዘል ምክር ልቤን ነክቶታል። እኔም የነበረብኝን አንዳንድ ደካማ አስተሳሰብ ወደ ኋላ መለስ ብዬ እንዳጤነው አድርጐኛል። እንደውም በዚህ ነገር ላይ ከጓደኞቼ ጋር ትልቅና ጥሩ ውይይት አድርገንበታል። በእውነቱ በጣም ነው ደስ ያለኝ። ጥሩ አስተማሪ የብዕር ጓደኛ በማግኘቴ ኩራት ብጤም ተሰምቶኛል። ገብርዬ ይህ ብቻ ሳይሆን ከአንተ ጋር በማደርገው የሀሳብ ልውውጥ ብዙ አዳዲስ ነገሮችንና ታዋቂ የዓለም ሰዎች አባባሎችና አስተሳሰቦች እንዳውቅ ረድቶኛል። አየህ እኔ ብዙውን ነገር የምፅፈው ሀገር ቤት ስላለው ሁኔታ ከማየውና ከምረዳው ነገር እንጂ እንደዚህ እንዳንተ በጥልቀትና በጥናት የተደገፈ አይደለም። ስለዚህ ከአንተ ጥሩ እውቀት እየቀሰምን ነው እልሃለሁ። ብቻ ብዕርህ እንዳይነጥፍብኝ አደራዬ የበዛ ነው።

አያ ገብርዬ! ዞሬ ዞሬ ያው ደህና ወሬ የለኝምና ሰሞኑን አፄ አምሐ ስላሴ (የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጅ) ለአገራቸው አፈር በቅተዋል። እኚህ ለረጅም ጊዜ በስደት ከእናት ሀገራቸው ተለይተው የኖሩ ሰው ለቀብራቸው ብቻ መግባታቸው በጣም ያሳዝናል። ቢሆንም ሁሉም በአገር ያምራ ልና ቀብራቸው ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በጥሩ ሁኔታና በክብር ነው የሆነው። ገብርዬ የእሳቸው ብቻ ሳይሆን ይህ በየጊዜው ባማረ የሬሳ ሳጥን እየመጣ የሚቀበረው ዜጋ ቀላል አይምሰልህ። እኔ ግን ከልቤ የምላችሁ ኢትዮጵያ መቀበሪያችሁ ብቻ አትሁን።

በሉ የነገ ሰው ደግሞ ይበለን! ደህና ክረሙልኝ።

የናንተው ወርቃየሁ ከሸገር

---

## ሠላምታ ከባህር ማዶ ከገብርዬ — ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

የተለመደው ሰላምታዬ ይድረስህ። «ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም» እንዲሉ ባለፈው ጦማርህ የዘገብከው የትዝብት የወያኔ የንግድ መዋቅር እንዲያው ተመዝግቦ ብቻ የሚረሳ ሳይሆን አድሎአዊና ጐሳዊ አጉራረሱ ለታሪክ የሚቆይና መዘንጋት የማይገባው ነው። የነፍቅረስላሴንና የሌሎችን የቀድሞ የደርግ ጎብረገነን መደብ (Nomenclatura) አብሮ መጉራረስን ሺህ ጊዜ ልቆ የሚያስከነዳው የሕወሓት እኩይ የጐሳ መሠሪ መደብ (Ethnic Cleptocracy) ሕዝባችንን ለዓለም የገንዘብ ድርጅቶች ወለድ አገድ በማስያዝ የሚያደርገውን የማፊዮስ ዓይነት መጠቃቀም አጋልጠሃል፤ ጉሽ አበጀህ!! ይህንን በተመለከተ ከዓለምአቀፍ የሞኖፖልና የመክሊት ድርጅቶች ፍትሕን ያዘለ ዳኝነትና የፖሊሲ ማስተካከል አትጠብቅ። ማንኛውም የሦስተኛ ዓለም አሻንጉሊት መንግሥት የጌቶቹን ፖሊሲ እስከተከተለና እንደዚሁም መዋቅራዊ ማስተካከልን በግብር እስከተረጐመ ብሎም ሕዝባችን ወገቡ እየጐበጠ ግብር በመክፈል ብድሩን እስከመለሰ ድረስ ሚሊዮን ሠራተኛ በግፍ ከሥራ ቢባረር ወይም ሺ ጋዜጠኛ ቢታሰር ደንታ የለውም። ትምሳሌ ይሁንና የጅብ ምስክር ገላጋይ ሆኖ የወደቀችዋን ፍየል ከቀበሮ አያስጥላትም። የጅቡ ግብ ከተቻለ ፍየሏን ተወዳዳሪን አባሮ ለብቻ መብላት ካልሆነለትና ካልቻለ ደግሞ በግድ እርስ በእርሱ እየተገላመጠ አብሮ መቀራመት ነው። ጌቶቻችን በቃል ደረጃ የዓለም የኢኮኖሚ ተራድዖ የታቀደው ድኅነትን ለማጥፋትና የሕዝቦችን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ነው ቢሉም ገቢራዊ ሁኔታው «ትልቁ አሣ ትንሹን ከመዋጥ» የማይቆጠብበት፣ ጉልበት ያለው ደካማውን የሚደፈጥጥበት፣ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋዩን የሚቦረቅስበትና ግፍ የሞላበት እንደዚሁም በመዋቅራዊ ኃጢአት የጨቀየ የዓለም ሁኔታ ነው። ስለዚህም ነው ባለፉት ደብዳቤዎቼ ምንም እንኳ ከ1950ዎቹ ዓመታት ጀምሮ በብሬተንውድስ (Bretenwoods) ተጠንስሶ በታቀደው ፖሊሲ መሠረት ብድር ለሦስተኛ ዓለም የሚረጩት የዓለም የመክሊት ተቋሞች ከሠሐራ በረሐ

በታች ያለውን የአፍሪቃ ምዝብር ሕዝብ ከድኅነቱና ከርዛቱ ፍንክች ያላደረጉት። ይህንን በአሁኑ ትውልድና በታሪክ ካልመሰከርን ኃቀኛ ዜጐች ከዚያም አልፎ ሕሊና ያለን የመሬት ኗሪዎች ልንሆን አንችልም።

አንዳንድ ለሆዳቸው ያደሩ ምሑራን ስለፓሲፊክ የገበታ ሀገሮች (Pacific Basin Countries) እንደኮሪያና ታይላንድ ያሉትን በብድርና በዓለም አቀፍ ተራድዖ መሻሻላቸውን እንደምሳሌ ቢያቀርቡም የእነዚህ ሀገሮች ታሪካዊ ዕድገትና ከኃያላን መንግሥታት ጋር ያላቸው ግኑኝነት ልዩ በመሆኑ ሌላ ራሱን የቻለ ትንታኔ ያስፈልገዋል። አውሮፓውያን ጨለማውን አኅጉር ሰንጥቀው የገቡት ለባሪያ ንግድና ለጥሬ ሀብት ነው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላም የፓሲፊክ ገበታ ሀገሮችን ምዕራቡ ዓለም ጠንከሮ በኢኮኖሚ ያለማው የሩሲያና የቻይና ኮሚኒዝም እንዳይስፋፋ ገድቦ ለመያዝ (contain ለማድረግ) ነው። ለዘላቂ መፍትሔ የአፍሪቃ ሕዝብ ግን በችግር ጊዜ ደራሽ ጉረቤት ስለሌለው ዛሬም በድኅነት፣ በሕክምና እጦትና በዲክቴተሮች ጥይት የእሳት እራት እየሆነ ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም።

ከታሪክ ብዙ ቁምነገሮችን መማር እንችላለን። ታሪክ የተውኔታችን መስታወት ነው። ታሪኩን የረሳ የአንድ ሀገር ሕዝብ ራሱንም የረሳ ነው። በምዕራቡ ዓለም የተወለደው በ18 እና በ25 ዓመት የዕድሜ ክልል ያለው ወጣት እጅግ የሚያሳስብ ነው። ትልቁ ፍራቻዬ ይህን ታዳጊ ወጣት ካላስተማርነው ኢትዮጵያዊነት እና ሀገር ወዳድነት ይጠፋል የሚለው ሀሳብ ነው። ይህንን ፍርሐት የሚያስወግደው የብዙኃንና የባሕል ድርጅቶች መመሥረት ነው። ታሪኩ የጠፋበት ትውልድ የሞተ የቁም ሬሣ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ በየደቂቃው በየሴኮንዱ በማሰብ መፍትሔ መሻት የእያንዳንዱ ኃላፊነት የሚሰማው ኢትዮጵያዊ ትግል መሆን ይኖርበታል። ይህ ሁኔታ እንደጨለማ እጅግ የሚያስፈራ ነው። ማሰላሰሉም እጅግ ያስደነግጣል። ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ታሪኳንም የተዛባ ትርጉም በመስጠት ለማበላሸት የሚጥሩ አውሮጳውያን፣ የጥንት ጠላቶቿ ና የዘመኑ የጉሳ አመለካከት አራማጅ «ልጆቿ» የሚመኩት በዚህ ግዴለሽ ታዳጊ ትውልድ ነው። ዛሬ አርባ ዓመት የደረሱ ታጋይ ምሑራንና የኢትዮጵያ ልጆች እድሜያቸው በገፋ ቁጥር የመቃብር የስበት ኃይል (Gravity) ይስባቸዋል። ነገሩ «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» ሆኖ የምዕራቡ ዓለም ራስ ወዳድነት የወጣቱን ትውልድ ልብ እንደአዙሪት እያሽከረከረ በግዴለሽነት አሻራ ውስጥ በማስገባት ላይ ይገኛል። እጅግ አስፈሪና አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ይህን ደብዳቤ የምታነብ ኩራትና ታሪክ ያለህ ኢትዮጵያዊ እጅግ ልታዝን ይገባኃል። እኔ ካልተቆረቆርኩ ሌላው ይቆረቆራል ብለህ ፅዋውን አታስተላልፍ። አባቶችና እናቶች ፅዋውን ለሌላው አስተላልፈው ቢሸሹ ኖሮ ዛሬ የጣሊያን እንቁላል ተሸካሚ ነበርን። የቃል ኪዳን ፅዋ እንኳ ሲቀባበሉ «... ማነው የሚካኤል አጋር ... እኔ ነኝ ... ያስጠምደኝ ባሥራሁለት ...»፣ ካልረሳችሁት ታስታውሱታላችሁ። ፅዋ ሲቀባበሉ እንኳ በቃል ኪዳን ነበር። ያ የታሪክ ቃልኪዳን አደጋ ላይ ነው ያለው። የታሪክን ቃልኪዳን ለትውልድ ለማስተላለፍ የጉሳን አመለካከት ለመምታት መቻል አለብን። ለትግሬውም ለኤርትራውም ሳናስልስ በማስረዳት አንድነትን ለመፍጠር መታገል ይኖርብናል። ከሰላዮችና የሥርዓቱ አቀንቃኞች በመለስ በጅምላ ሁሉንም ማግለል የለብንም። የአውሮጳውያን ጥቅም የትግሬው፣ የአማራው፣ የኦሮሞውና የኤርትራው ጥቅም እንዳልሆነና የሕዝባችን መለያየት ማንኛችንንም እንደማይጠቅም ለሁሉም ማስረዳትና ማሳመን አለብን። የእነዚህ ሕዝቦች አንድነት ቢጠናከር በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባችንን ከድኅነትና ከድንቁርና ማላቀቅ እንችላለን።

ውድ ወርቃየሁ! በይስሙላ ብድርና እርዳታ (Foreign Aid) ምዝብር ሕዝቦች ኑሮአቸውን ያሻሽላሉ የሚል የሞኝ እምነት የለኝም። ብድር እና የውጭ እርዳታ መሻሻልን የሚያመጣ ቢሆን የሞቡተዋ ዛየር (Zaire) ዛሬ ጨረቃ ላይ በደረሰች። አይ ኤም ኤፍ (IMF) እና የዓለም ባንክ (World Bank) ይህን ጠንቅቀው ያውቁታል። ብድር ቢያበለጽግ ኖሮ ዛሬ የሜክሲኮ ቺያፖስ አርሶአደሮች፣ በብራዚል የሚረሸኑ ሕፃናት፣ በጓታማላ የሚጨፈጨፉ ሠርቶአደሮች፣ በታይላንድ ለባለብር ስልጡኖች ለወሲብ ማርኪያ የሚቀርቡ ከ15 ዓመት በታች ያሉ ሴት ሕፃናት በደስታ በፈነደቁ። ዛሬ የዓለም አቀፍ መክሊታዊነት ዋናው ተግባር የሀገር ውስጥ ባለጠጎችንና የውጭ አቀባባይ ከበርቴዎችን በመደጐም ድኃውን የበለጠ ድኃ እንዲሆን ማድረግ ነው። ይህ ሥርዓተ—ማኅበር የሚደጉመው ያለውንና በሥልጣን ላይ የተቆናጠጠውን ኃብታም ነው። አንዳንድ የምዕራቡ ምሑራን ይህንን የባለጠጋ ግብረሠናይ (Corporate Welfare) ይሉታል። የባለጠጋ ግብረሠናይ የአሜሪካ ሐብታሞችንና በውጭ እርዳታ ስም የዓለም አምባገነኖችንና መራሽ መንግሥታትን ይደጉማል። ስለዚህም ነው የላቲን አሜሪካ የነፃነት ሥነ መለኮት አቀንቃኝና ታጋይ ቀሳውስት "ይህ ዓለማዊ የመክሊት ሥርዓት ከሕፃናት ሳይቀር የጡጦ ወተታቸውን የዱቄት ወተት ሰጥቶ ይነጥቃቸዋል፤ በግራ እጁ አንድ ብር ሰጥቶ በቀኝ እጁ አራት ብር ይወስዳል" የሚሉት።

እያ ወርቃየሁ!

የዚህ ዱርዬ ሥርዓት ዋነኛ መሣሪያ የግኑኝነት ሐብቱ ነው። ፊልሞቹ መጽሔቶቹ፣ ጋዜጣዎቹና ቴሌቪዥኖቹ እናቱ የሞተችበትን ሕፃን እንኳ ያሳስቃሉ። ማታለሉን ለመግለፅ ከጽሑፍ ችሎታዬ በላይ ስለሆነ አንዳንዴ እኔንም ድጦኝ ስለሚጉለብት በእውነቱ ኃጢአቱን ለመግለፅ ቃል የለኝም። ስለዚህም ነው ሐቅንና ስነጽሑፍን (Literature) የገደለ ሁሉ እናቴን ያገባል ያልኩት። በምዕራቡ ንግግሩ ሁሉ ስለዓለም ሕዝቦች ደስታና ብልፅግና ነው። የማን ብልፅግና? የማን ወለድ? የማን ብድር? የማን ዕድገት? የማን የሰው ልጆች መብት መከበር? የማን ልግስና? የማን ደግነት? ... ጥያቄው ይቀጥላል።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ምንም እንኳ የወያኔን የስለላ ማዋከብ ባፍራሽነቱ ብገልፀውም ችግራችን ሁሉ በወያኔ ምክንያት ነው የመጣው በማለት የራሳችንን ድክመትና ልሽቀት በጠላት ላይ ብቻ እንዳንከብ አንባብያን ይረዱ ዘንድ ሀሳብ ልለግስ እወዳለሁ። የወያኔ የስለላ እምርታ ከ1992 በኋላ ያደገ ነው። ያዳከመን ከሌሎች ችግራችን ጋር ተዳምሮ ነው። ችግራችን በሁሉም በኩል ማየት እንዲቻል የቀረበ ነው። መፍትሔው ሁሉን አቀፍ መሆን አለበት።

መፍትሔው የታሪክን ትምህርት መርሳት የለበትም። ታሪክ ቀጣይ ነው። ታሪክ ያለፈውንም እንደዘገበው ለአሁኑም ትውልድ አብሪ መብራት ይሆናል። ስለዚህ ቁም ነገር ፈላስፋውና ታሪከኛው በርክሐርት (Burkhardt) «በተራማጅነት» የላሸቀውን አእምሮዬን ገርተውታል። የታሪክን ቀጣይነትና እንክብካቤ እንደዚህ ሲሉ በምሑርነቱ ላልሰማ አሰማ ብለው ያስተላልፋሉ። “ጓናም ደግሞ የሆነ ዓይነት ቋሚነት እረፍት በሌለው የታሪክ እንቅስቃሴ ውስጥ አለ፤ ይህም ቋሚነት ያለው ባሕርይው ቀጣይነቱ ነው። ... ቀጣይነት መገስገስ ብቻ አይደለም፤ ከቸኳይ ተራማጅነት አደብ የገዛና ከችኩልነት ጋብ ያለ ነው፤ በቸኳይነቱም ከዘመናዊ የግብ ግስጋሴ ይለያል። [*ከተርጓሚው፦ <u>አበው የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ይሉ ነበር።</u>] ስለሆነም በበርክሐርት አባባል የሰው ልጅ ነፍስና አእምሮ የተሟላው ገና ድሮ ነው። ስለሆነም ቀጣይነት ከግስጋሴ ይለያል፤ ቀጣይነት አዲስ ከምንፈጥረው ረጋ ሠራሽ ባሕል ይልቅ የትውልድ ቅርስንና ተሐድሶን ያስታውሰናል፤ በንቃት የሚከሰት ቀጣይነት የሕዝብን ቅርስ የማይረሳ የሕዝብን ባሕል የማይሰርዝ በሁሉም መልኩ ነፃነትን የሚለግስ ነው። ይህንንም በንቃት የተዋበ የታሪክ የክብር ውርስን የሚረሱ ያልሰለጠኑ የድንጋይ ዘመን ሕዝቦችና በስልጣኔ ነቅተናል የሚሉ የዘመኑ ጉግማንጉግ ሕዝቦች ናቸው።” ይለናል።

ወርቃየሁ!

ይህንን ጽሑፍ ሳገባድድ የአንድን ባሕታዊ በጥይት በአደባባይ መረሸንና የጦቢያን ፀሐፊዎች መታሠር ሰማሁ። እስቴት ዲፓርትሜንት ለአሜሪካ ግብር ከፋይ ሕዝብ ስለኢትዮጵያ ምን እንደሚል በጉጉት በመጠባባቅ ላይ ነኝ። ይህ «የሞቦቱ ዓይነትየመፃፍና የመናገር መብት ነው» በማለት በ1970ዎቹ መጨረሻ ዓመታት የዛየርን ተቃዋሚዎች እንዳደናገረው ዓይነት መግለጫ ሳይሰጥ አይቀርም። ይህቺ ናት የሱካርኖና የፈርዲናንድ ማርቆስ የመፃፍና የመሰብሰብ ነፃነት፣ ይህቺ ናት የፒኖሼ ነፃ ፕሬስ! አይ እስቴት ዲፓርትመንት! ለምን በቃላት ከሚሸነግለን ቃሉም ጉልበቱም የእኔ ነው ዝም ብላችሁ ተገዙ ቢለን! ከእርሱ በላይ በምድር ማን ጉልበተኛ አለ? የመክሊት ኀብረገነንነት (Capitalist totalitariansm)በዓለም አቀፍ ደረጃ ይፏችኋል ይሄ ነው!!

የብዙኃን ድርጅቶች በኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ዜጐች መደራጀት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። የስቴት ዲፓርትሜንትን ፖሊሲ እንደግብር ከፋይታነትን መታገል እንችላለን። ሌላውን መቀስቀስና ማስተማር መብታችን ነው። የሕገመንግሥቱን መብትና ግዴታ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። ባይወድም ቢወድም በመጨረሻ የአሜሪካ ፖሊሲ እንደሚለወጥ ጥርጥር የለኝም። አለቆቻችን እንደጦር የሚፈሩት ነገር ቢኖር የሕዝብን የተቃውሞ ምርጫ ነው። የእኛም የቅርብና የረዥም የፖለቲካ ጥያቄ በአሜሪካ የምርጫ ሳጥን ላይ ማተኮር አለበት። ለምሳሌ በኮንግሬስ ወይም ሴኔት ምርጫ አሜሪካ ላይ ካሉት ኢትዮጵያውያን ውስጥ 5000 እንኳ ጠንክሮ ቢሰራ ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ ሊቀይር ይችላል። ይህም 1 ግለሰብ 100 ሰዎችን ለሚፈልገው ምርጫ ግብ ሊያደራጅ ይችላል። የግብረሠናዩን አዋጅ ከነግሪንግሪች አክራሪ ድንጋጌ የቀለበሰው የፍልስ ስደተኛው ድምፅ ነው።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ብዙዎቻችን እንደምንጠይቀው ሁሉ ዛሬ አንተም «ይህ እምባ እንዴት ይደርቃል፣ ድኀነትስ እንዴት ይጠፋል» ትል ይሆናል። ትልቁ መፍትሔ በኃያላን ሀገሮች ያሉ ሕዝቦች ቀስ በቀስ በደረጃዊ ዕድገት ብርኃዊነትን ማፍለቅ ሲችሉ ነው (Incremental Conscientizacion)። መንጋጭላን የሚያስብርና ደም የሚያፋስስ አብዮት ያለቀለት ይመስላል። መፍትሔው የፖርላማ ውይይትና ሰላማዊ መንገድ ነው። በምዕራቡ ዓለም ይህ የነጋንዲና የነማርቲን ሉተር ኪንግ መሰል ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እያደገ ነው። ለምሳሌ የሰውን ልጅ ኩላሊት እንደዕቃ በካልካታና ዲሊሒ የሚደልለው አቀባባይ ከበርቴ የተመታው በምዕራቡ ዓለም የሕዝቦች ንቃት ነው። አንድ ብር ሰጥተው ሕፃናትን ከ18 ሰዓት በላይ የሚያሰሩት የጫማና የልብስ ሕቡዕ የላብ እርም ሱቆች(Sweat Shops) የተዘጉት የምዕራቡ ዓለም ሕዝብ የራሱን ዓለም አቀፍ ቱጃሮች በሰላማዊ መንገድ በመታገሉ ነው። በእኛም ሀገር እንደዚህ ዓይነቱ ሰፊ ፀረ–ጉሰኝነት እንቅስቃሴ መስፋት አለበት። ይህ ሲያሚጥጥ ብቻ ነው ወደሌላ አማራጭ መኬድ ያለበት። የዚህ ዓይነቱን ነፍስ አድን ተቃውሞ (effective protest) ሳያስልሱ፣ ሳያቋርጡና ሳይደክሙ የሚመሩ ብቃት ያላቸው የብዙኃን ስብስብና የተወሰኑ ዓላማ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ያስፈልጉናል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊትና በኋላ የእስራኤል ዓለም አቀፍ ሕዝብ (International Jewry) ብተናንና እልቂትን ተዋግቶ የእስራኤልን መንግሥት በ1948 ዓ.ም. የመሠረተው በየሀገራቱ ባቋቋማቸው ሕዝባዊ የብዙኃን ድርጅቶች ትግልና እንቅስቃሴ ነው። ዛሬም ወገን ስደተኞችን ከሩሲያና ከሌሎች ሀገር ከማስወጣት አልፈው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ በቀጥተኛና በልዩ መንገድ ተፅዕኖ በማድረግ ለሀገራቸው ሕዝብ ይታገላሉ። ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለፍልስ–ስደት ጠቃሚ ፖሊሲዎች መነደፍ፣ ለእሥራል ጥንካሬ፣ ለእርስ በእርስ መረዳዳት፣ ለባሕላቸው ዕድገትና ከዚያም አልፈው ሌሎችን በመርዳት ይህ ነው የማይባል ሚና ስለተጫወቱ ለእኛም እንደምሳሌ ሊቆጠሩ ይገባል። ዘግይተው ወገንነታቸውን የተቀበሉት ጥቁር እስራኤላውያንን በሱዳን ስደት ሲሰቃዩ ከሌሎች ሰብዓዊ ድርጅቶችና ከኃያላን መንግሥታት የስለላ ድርጅቶች ጋር እንኳ በመተባበር ለሕዝባቸው ፈጥነው መድረሳቸውን ሱዳን በወቅቱ «የሙሴ ግዳጅ»(Operation Moses) ሲካሄድ የነበሩ ስደተኞች የሚረሱት አይመስለኝም። ይህን ሁሉ ያደረጉት በዓለም አቀፍ ደረጃና በአሜሪካ የተጠናከሩ ማኀበራት ስላላቸው ነው። ዛሬስ እኛ በኬንያ፣ በጂቡቲና በሌሎች የአፍሪቃ ሀገሮች ስላሉት ስደተኛ ወገኖቻችን ያደረግነው ጥረት የቱን ያህል ነው?

ውድ ወርቃየሁ!

በእርግጥም በአሜሪካ በአንዳንድ ሥፍራዎች የተጠናከሩ የኮሚኒቲ ማኀበራት፣ የብዙኃን ድርጅቶችና ሕዝቡ በአምልኮተ–አበው የሚሰባሰብባቸው አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ኃይላቸውን አጠናክረው የተፈለገውን ያህል በመተባበር ሃገርአቀፍ ወይም ዓለምአቀፍ ስብስብ ሊፈጥሩ አልቻሉም። ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የሚከተሉት ዋነኛ ነጥቦች ናቸው።

1) <u>የኑሮ ሁኔታና የሀገሪቱ የውድድር (Competition) ባሕል</u>

እርስ በርስ የመቀናናት ባሕል በእኛም ዘንድ ቢኖርም በሥራ የመጠመድና የግሳንግስ እሽቅድምድም እንደዚሁም በግለሰቦች የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክር ካለው የሀገሪቱ የሩጫ ባሕል ጋር በመጣመር በስደተኞች ላይ የውድድር ሁኔታው እንዲባባስ አድርጉታል። ሌሎች ንዑሳን ዜጎች ለምሳሌ የሩቅ ምሥራቅና የአውሮጳ ስደተኞች ማኅበራቸውን ለማጠናከር የበቁት ከሁለተኛ ዜግኘነትና (2nd generation) ብዙ ዓመታትም በአሜሪካ በመቆየት እንደዚሁም ተመክሮ በመገብየት ነው።

2) <u>የእኛ የፖለቲካና የኅብረተሰባዊ–ስነልቦናዊ ባሕሎች</u>

ምንም እንኳ የውጭ ወራሪ ኃይል ሲመጣ ለምሳሌ እንደማይጨውና አደዋ ጦርነቶች ሕዝባችን ያሳየው መተባበር በታሪከኛነቱና በምሳሌያዊነቱ የሚያኮራን ቢሆንም በሰላሙ ጊዜ እርስ በርሳችን አንስማማም። የዘመነ–መሳፍንት ታሪክ እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይገባዋል። አፄ ቴዎድሮስ ደጃች ውቤን፣ ሌሎችንም መሳፍንቶችና ቀሳውስትን ሲያሳድዱ ነው ለጠላት የተጋለጡት፤ አፄ ዮሐንስም በምንሊክና በቴዎድሮስ ላይ በወጣትነታቸው ጊዜ የሠሩት አሻጥር ቀላል አይደለም። እንዲያውም የጄኔራል ናፒየርን ጦር መርተው መቅደላ ያስገቡት እርሳቸው ናቸው። ተፈሪ መኮንንም አልጋ ላይ ሊወጡ ሲሉ ያደረጉት ስያፍ የፖለቲካ ማወታ ብዙ ነው። የእኛም ያደግንበት የፖለቲካ ባሕል እንደዚሁ ነው። በእርግጥም በፖለቲካ መጉሻሸምና መመታታት በሁሉም ያለ ባሕል ቢሆንም የአሜሪካ ፈረንጅ ግን በፖለቲካ ቢጉሻሸምም በጋራ ጥቅሙ ላይ እንደርሱ የሚያብር የለም። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና የሀገር ውስጥ ፖሊሲ ሲነድፍ ለሀገሬ የቱ ይረባል (What is in the best interest of my country ይላል።) እጅግ ጮሌ ነው። ሌላው ቀርቶ ሞኙ የሞስኮ ሕዝብ ታሪካዊ የሌኒንን ኃውልት በገመድ እንደበሬ ጉትቶ ሲጥለው የአሜሪካ ሕዝብ ራሱን የጉዱትን የጥንት መሪዎችንና የባሪያ ፈንጋይ አበውን ኃውልት አልደረመሰም። እንዲያውም ለሀገሩ ባሕልና ትምህርት አርብቷቸዋል። አንድ አረጋዊ ነጭ ስለ ኤፍ ቢ አዩ መሪ ኤድጋር ሁቨር ያጫወቱኝ ትዝ ይለኛል። «ኢኛም እኮ በቅርቡ የጭለማ ዘመን ነበረን፣ እኝህ የሕዝብ አገልጋይ ብዙ የሠሩት ወንጀል አለ። ግን ሐውልታቸውን አንደረምስም። ቢከፉም ቢለማም ከእኛ ነው የወጡት። ጥፋታቸውም ታሪካችን ነው፤ መጥፎውንም ጥሩውንም ከታሪክ ለመማር ማስታወስ አለብን ...» ሲሉኝ የእኛን መንግሥታት ከጥንት ጀምሮ እስከመለስ ዜናዊ ድረስ በሐሳቤ ምዕራፎች ቃኘኋቸው። ነጭ ብልጥ ነው፤ ታሪኩን አይገድልም፤ ለጥቅሙ ይተባበራል። እየተወዳደረ ብዙኃን ድርጅቶችን ችግሮቹን ለማቃለል ይመሠርታል። ካለፈው ስሁተቱ ይማራል። በሳዳም ሁሴን ላይ አሜሪካኖች የወሰዱት እርምጃ ሊሳካ የቻለው በቬየትናም ባገኙት ተመክሮ ነው። ከተመክሮው በመማር የሚበልጠው የለም።

ውድ ወርቃየሁ!

እስከመለስ ዜናዊ ድረስ ያለው እንቶፈንቶው የፖለቲካ አመለካከታችን ከጉሳና ካለው የምዕራቡ የውድድር ባሕል ጋር ተዘንቆ የበለጠ በመካረሩ አብዛኛው ሕዝባችን ሀገሩን ቢወድም በግለሰብ ደረጃ የጉሪጥ ይተያያል፤ ይናናቃል። ለምሳሌ በዋሽንግተን ዲሲ ኢትዮጵያዊው በግለሰብ ደረጃ የሚተያየው ማዶ ለማዶ ነው። ሆኖም በወያኔ መንግሥት ላይ ተቃውሞ ሲኖር ሁሉም ከያለበት በመተባበር ይወጣል። ያገር ነገር ክብሩ ነው። በኢትዮጵያ የመጣ በዓይኑ የመጣ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ላይ የበለጠ «ቤንዚን በማርከፍከፍ» እንዲቀጣጠል ያደረገው ልብ አደንዛዥ የምዕራቡ ዓለም ባሕል ነው። አንዱ አዲስ የቆርቆሮ መኪናና ጣውላ ቤት ሲገዛ የእኔ ብጤ ድኃውን ይንቀዋል። ዶፍቶር ተሁኖ ቦርጭ ሲሞላ (በጥቂቶች ላይ እንደሚታየው) የሀገርና የሕብረቷሰብ ነገር ይረሳና ስለሀጋራቸው ሌት ተቀን በሚሰሩ ላይ ይንጓጠጣል። ከመርካቶ መጣሁ የሚለውና የአማርኛን ቋንቋ በእሪ በከንቱ ላንቃ(EBONICS) የተካው ምንም የረባ ቁምነገር ለራሱም ሆነ ለሀገሩ ሳይሠራ ሌላውን ባላገር እያለ ይሳደባል። ባላገር ስንት ብልሃት እንዳለው አይረዳም። የእኛ ነገር ተዘርዝሮ አያልቅም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በብዙኃን ድርጅት፣ በአብያተ ክርስትያናትና በፖለቲካ ፓርቲዎች ጥንካሬና ምሥረታ ላይ ተፅዕኖ ያደርጋሉ። ሌላው ደግሞ የኃይማኖትም ልዩነት አለ። ጴንጤው ራሱን የቻለ መዋቅር አለው። በዚህች በካፒታሊስት የዋሻ ጭጋግ ሰላሙ እንዳይናጋ ዓለማዊ በሚላቸው ላይ ውሱን የሕሊና ፍርዱን እየሰጠ ተከናንቦ የራሱን ቅዱስነት በልሳን የሚቀባዥር አለ። የእነእየሱስና የቋጥኙ ቅዱስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን አንድ እንዳልሆነች ሁሉ የጉሳ ቤተክርስቲያን በተመሠረተባት ሀገር ነው ያለነው። የትግሬና የአማራ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን አለ። የኦሮሞና የቀረው ኢትዮጵያዊ ወንጌላዊ የጴንጤ ቤተ ክርስትያናትም ተመሥርተዋል። እጅግ ያሳፍራል። ያ የምንፈራው ገሀነመ–እሳት ካለ እነዚህ እንዴት ከቃጠሎው ሊድኑ እንደሚችሉ አይገባኝም። እነዚህ ሁሉ በብዙኃን ድርጅቶችና ፓርቲዎች ላይ ተፅዕኖ አላቸው። እንደሌሎች አልታደልንም። ሆኖም ይህን የተረዱ ብሩኅ የኢትዮጵያ ልጆች አንድነትን ለማምጣት በአሜሪካ ሌት ተቀን እየታገሉ ነው።

3) *<u>በአንድ ወጥ ዘር አለመታደል</u>።*

ጃፓኖችና ከእስካንዲኔቪያ የመጡ ፈልሳውያን የብዙኃን ማኅበር የመመሥረት ችግር የለባቸውም። የኪዩባ ወይም የሚክሲኮ ስደተኞች ምንም እንኳ በመጠናዊ ሁኔታዎች ቢከፋፈሉም በአንድ ላይ ለመምጣት አይከብዳቸውም። ይህም የሆነው ኅብረተሰባቸው አንድ ወጥ (Homogeneous) በመሆኑና ቅይጥ ባለመሆኑ ነው። የቬይትናሞችም የኢኮኖሚ ዕድገትና ትብብር ከዚህ ተለይቶ መታየት አይኖርበትም።

በአንፃሩ ደግሞ ኢትዮጵያውያን በስደት ላይ ጠንካራ ሠራተኞች መሆናችን፣ አትንኩኝ ባይነታችን፣ አብሮ መብላታችንና ባሕላችን ብዙውን ነጭ አስገርሞታል። አብዛኛው ፈረንጁን አይለማመጥም፤ የሚያየው በአቻነት ነው። ዘረኝነትን አይወድም። በዚህም የተነሳ ባለመተባበራችን ቢስቁብንም ባለን አመለካከታችን ያከብሩናል።

4) *<u>የወያኔ የሥለላ ድርጅቶች</u>*

እነዚህ በኢትዮጵያውያን አካባቢ ያሉ መዋቅሮች በግልፅ ባይታወቁም ከግለሰቦችና ከሌሎችም ጋር ሀሳብ በመለዋወጥ የተገኙ እንደዚሁም በግልፅ ሳይሆን

በወንድማዊና እህታዊ ግኙኝነቶች በመቅረብ ከወያኔ አባላት በአንዳንድ አካባቢዎች የተገኙ መረጃዎች ናቸው። ይህ ወደፊት በመጽሐፍ መልክ እንደሚታተም አረጋግጥልሃለሁ። በጥናት መልክ በቅርቡ ይወጣ ይሆናል።

ውድ ወርቃየሁ!

ተገንጣዮች ራሳቸውን የቻሉ ሕዋሶች በየከተማው አሏቸው። በሰብዓዊ ድርጅቶችም ውስጥ አሉ። የራሳቸው መረብ (Network) በርካታ ኤርትራውያንና የትግራይ ምሁራንን ያቅፋል። አንዳንዶቹ ሥራ ሳይሰሩ ይኖራሉ። እነዚህም በወያኔ መደጐሚያ ይኖራሉ ተብለው ይጠረጠራሉ። ከአሜሪካ መንግሥት ጋር የቀረበ ግኑኝነት አላቸው ይባላል። የአሜሪካ መንግሥት ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር እንዳይገናኝ በሩን ሁሉ በመዝጋት እነርሱ በኢትዮጵያና በአፍሪቃ ጉዳዮች ላይ አማካሪዎች ሆነዋል ብለው የሚተቹ ግለሰቦችም አሉ። የአሜሪካ መንግሥትም በእውነቱ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለመቅረብ የረባ ጥረት አላደረገም። ስለሆነም የሚያገኘው መረጃ አንድ ወጥ ብቻ ነው። በዚህም በኩል የተቃዋሚ ድርጅቶች ድክመት አለ። እነዚህ በወያኔ ማዕከል ሥር የተሰባሰቡ ምሑራን ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ አፍሪቃዊ መባልን ይመርጣሉ። ምናልባትም የዚህ ዓይነቱ ዘመን አመጣሽ አፍሪቃዊነት ("Designer Pan-Africanism") በኢትዮጵያ የጐሳን አይዲዎሎጂ ከማራመድ የሚመጣ ስነልቦናዊ ፀፀት (Psychological guilt) ነው በማለት የሚነቅፉ ግለሰቦች አሉ።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

የብዙኃን ድርጅቶች፣ የአብያተ ክርስትያናት፣ የሰብዓዊ ማኅበራት፣ የፖለቲካ ማኅበራትና የዖታ ማኅበራት በኢትዮጵያዊነት መጠናከር ስለሚያስበረግጋቸው እነዚህ የወያኔ የስለላ ሕዋሶችና ድርጅቶች በግድ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን ማጥፋትና ማናከስ አለባቸው። ከብዙ ስቴቶች እንደሚሰማው በየጊዜው ልዩ ልዩ ዓይነት ዘዴዎችን በመፍጠር ሌላው ቀርቶ በሴት እንኳ በመግባት አይጠርጠሬ ድርጅቶችን ይበታትናሉ። የሚጠቀሙት ቅራኔ ሊፈጥሩ የሚችሉትንና አሉባልታና ውዥንብር ለመፍጠር ብቃት ያላቸውን የወገን እንከሮች ነው። የስለላና የውዥንብር ሥልት አረማጨታቸው እጅግ የተራቀቀ በመሆኑ አንዳንድ ታዛቢዎች ከምዕራቡ ዓለም የተማሩት የውዥንብር ዘዴ (Disinformation) ነው ይላሉ። በበርካታ ሥፍራዎች ይህ ጥረታቸው ተሳክቶላቸዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንደአሸን ፈልተው ወዲያውኑ የከሰሙት በወያኔው ዘመነ መንግሥት ነው።

ውድ ወርቃየሁ! እነዚህም ሰላዮች የምዕራቡን ትምህርት በመውሰዳቸውና ከላይ እስከ 3ኛ ተራ ቁጥር የገለፅኳቸውን የኅብረተሰባችንን ድክመቶች በሚገባ በመጠቀማቸው በርካታ አብያተ ክርስትያናትንና በመጀመር ላይ ያሉ ማኅበራትን አፈራርሰዋል። የውዥንብር ሥልቶች፦

ሀ) ገንዘብ ተበላ የሚል ውዥንብር በመርጨት እምነት በማሳጣት መሪዎችንና ገንዘብ የሚያዋጡ አባላትን መነጣጠል። አመራር ሊሰጡ የሚችሉትን ግለሰቦች ማስጠላትና መለየት (Isolate ማድረግ)። «ገንዘብ መልሱ» በማስባል «የራሱን በሬ በራሱ ሠርዶ» እንዲሉ ሚስጢራቸውን ሳይገልፁ በመለመሉዋቸውና ብዙ ሊያስተውሉ በማይችሉ [DUPES] ኢትዮጵያውያን ክስ እንዲመሠረት መገፋፋት፤ የበለጠ አሉባልታን ማሠራጨት። ስለተቃዋሚ ድርጅቶች ለእነርሱ የሀገር ቤት መዋቅሮች ዘገባ ማቅረብ፤ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች በሃገር ቤትም ሆነ ውጪ መጉዳት።

ለ) በተለይ አብያተክርስትያናትንና ማኅበራትን የነጉሡ ወልዴና የነፍጠኛ አማሮች ድርጅት ነው በማስኘት ለፖለቲካ ግድ በሌላቸው አንዳንድ ኤርትራውያንና ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ማስጠላት።

ሐ) ኤርትራውያን በወንጀል ሲያዙ ኢትዮጵያዊ ነን እንዲሉ መገፋፋት፣

መ) የአመራር አባላትን ነጥሎ በመጋበዝና ለረዥም ጊዜ አብሮ ጓደኛ በማድረግ ድርጅቶችን ለማፈራረስ መጠቀም፣

ሠ) ኢትዮጵያውያን ከሥራ እንዲባረሩና በአንዳንድ ሥፍራ ቁልፍ ቦታ እንዳይዙ አሻጥር በመሥራት ጥረት ማድረግ፣

ረ) አብዛኛውን ተቃዋሚ ድርጅቶች በአሜሪካኖች ማስጠላት፣

ሰ) «ብአሜሪካ ያሉ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ምን ይረባሉ?» በማለትና ተገቢ ነቀፌታን ለራስ በመጠቀም ( exploit በማድረግ) ተቃዋሚ ድርጅቶችን ማስጠላት፣

ሸ) ከእነርሱ ጐሳ ጋር የተደባለቁትንና ጓደኛ የያዙትንም ማለያየት፣ ግለሰቦች ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ለመጠቀሚያ ማሳካት፣

ቀ) ከኅብረተሰቡና ከአብያተክርስቲያናት ጋር የማይስማሙትን ግለሰቦች በመመልመል ለውዥንብርና ለማፈራረስ መጠቀም። ለዚህም ሰፊ ጥናት ማድረግ፣

በ) የዘር ሐረግ በመቁጠር የአንድን ማኅበር ቦርድ የአማሮች ስብስብ ነው በማለት ለአሜሪካኖችና ለመንግሥት ማሳጣት፤ እንዲዘጋም ሌት ተቀን መሥራት።

ተ) አዲሳባ ያደጉ ኤርትራውያንን ለሥለላ መጠቀም፣

ቸ) ለዚህም ሥራቸው ይረዳ ዘንድ በውሸት ስም በተቋቋሙ ንግዶች መጠቀም፣

ኀ) በከተማና በገጠር ልጅ፣ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተማዎች ወይም ገጠሮች አካባቢ በመጡ መካከል በማታለል በቀረቧቸው «ወገንን አድሚ» ግለሰቦች በመጠቀም መከፋፈል። ተፋላሚ ሀገር ወዳዶችንና ምሑራንን ማንቋሸሽና ማስጠላት። አመራርን ለመከፋፈል ነጥሎ መጋበዝና ጓደኝነት መፍጠር። ብሎም በአላማቸው ማሳመን፤ ኢትዮጵያዊ ወንድማቸውንና ወገኑን እንዲጠራጠር ማድረግ።

አ) ታጋይ ኢትዮጵያውያንና መጽሔቶችን በማንቋሸሽ ማስጠላት።

እንግዲህ ወርቃየሁ ድርጅቶች የተመቱትና ያልጠነከሩት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው። የሀገር ወዳድ የኢትዮጵያውያን ድክመት ቢኖርም የወያኔ የስለላ ድርጅት በእባብነቱ ብዙ ሚና ተጫውቷል።ከዚህ በፊት እንደገለፅኩት የትግራይን ሕዝብ በጅምላ መጥላቱ ስህተት ነው። እነዚህን ሰላዮች መታገል ግን የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆን አለበት። ለድርጅቶች በአሜሪካ መጠናከር ይህ ትልቁና ዋነኛ መፍትሔ ነው።ብዙኃን ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች እንደአሸን የሚፈሉት ለማፈራረስ ሥልቱ በቂ የሆነ አፀፋ ሲመለስና በስደት ላይ ያለው ሕዝባችን ሲነቃ ነው። አለበለዚያ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ይሆናል። ከየት እየለሌ ዘመን ጀምሮ

የሕዝቦች ትግልና ስብስብ ግቡን ሊመታ የቻለው በብዙኃን ማኅበራትና አንድነት ነው። ይህን የሚክድ ራሱንም የካደ ነው። ለሕዝባችን አንድነት ለኢትዮጵያ ከውርደት መውጣት የብዙኃን ድርጅት በሁሉም ማዕዘን መብዛት ቤዛ ይሆናል፤ ለፖለቲካውም መቃናት በር ይከፍታል፤ ጉስኝነትንም በመፋለም አንድነታችንን ያበረታታል። ተገንጣዮችና ኢትዮጵያን አፍራሽ ግብረ አበሮቻቸው በምሑራዊ ክርክርና በዴሞክራሲያዊ ውይይት ስም ሐሳባቸውን ለማራመድ ኢትዮጵያዊ መፅሔቶችን ተጠቅመዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ጠንካራ ሥልጣቸው የመገናኛ መሣሪያዎችን እንዴት ሊጠቀም እንደቻለ ነው። የኤርትራ «ሬፈሬንደም» ሊቃረብ ሲል እነ ጆርዳን ገብረመድኅንና ሌሎችም በኢትዮጵያ ሪቪው የፃፉት ምሑራዊ መስል የፈጠራ ታሪክ የሚረሳ አይደለም። በመንግሥቱ ኃይለማርያም ዘመንም ወያኔ በተለይም የእንግሊዝ ጋዜጠኞችን በመመልመል የራሱን ዓላማ ለማሳወቅ ጥሯል። በዚህም መንገድ የኛዎችም ምሑራን የሶቪየት ኅብረትንና የመንግሥቱን የመብት ረገጣ በመቃወም ስሌቱና አሰላለፉ ሳይገባቸው እናት ሀገራቸውን በምዕራቡ ዓለም ሆነው ባልጠረጠሩት መንገድ በማፈራረሱ ተግባር ተሳትፈዋል።

ዛሬም በኢትዮጵያ ሐብት በስኮላርሺፕ በልዩ ልዩ ከፍተኛ ዩኒቨርስቲዎች የሚማሩ ኤርትራውያን ታሪክን ለተማሪዎችና ለመምህራን እያጣመሙ ማስተማራቸውን አልተዉም። አንድ መጠየቅና መመለስ ያለበት ቁም ነገር አለ። ለመሆኑ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ እንደዚህ ዓይነት የከረረ ጥላቻ እንዴት ተፈጠረ? ለምን ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከምድረ ገፅ እንዲጠፋ ሌት ተቀን ይጥራሉ? ማንኛውም አፍሪቃዊ የጥንት የሀገር ስምና ታሪክ እንዲጠፋ አይፈልግም። እኔም በአፍሪቃዊነቴ ሱማሌ ... ኬንያ ... ሱዳን ... ወዘተ እንዲጠፉ አልፈልግም። ማንኛውም ቅን ኢትዮጵያዊ ዜጋ የማንም ሀገር ስልጣኔና ታሪክ እንዲጠፋ አይመኝም። ይህ እጅግ መጠነኛና ከማንኛውም ዜጋ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ከጥቂቶች ፅንፈኛ እስላሞች በስተቀር የአሜሪካ ጥቁር ሕዝብ እንኳ እንደዚያ ተበድሎ ለሌላ መንግሥት አልቋመጠም። አሁንም እንዲህ እየተሰቃየ ለብቻዬ ልሁን አላለም። ነጩንም አልጠላም። የኛዎቹ ግን ኢትዮጵያን፣ ታሪኳን፣ ለእነርሱም አኩሪ የሆነውን ባሕሏንና ሕዝቧን እንዴት እንደዚህ አክርረው ይጠሏታል? «ሻቆና» ከሚለው የተገንጣዮች መዝሙር በመለስ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ያስፈልጋል። እነሆ ትንሽ ግጥም፦

## እናት ዓለም

ዝናሽ ርቦኝ ትብብርሽ ቆሽቴ አሮ ኩላሊቴ
ተሰውሮ መድኃኒቴ
የጥንት ኃይልሽ መስተንግዶሽ፣
መልኬን መስሪያ መስታወቴ
ኢትዮጵያ አድባር አቴቴ።
ስንቱን ጀግና ፍታት ፈተሽ
አስቀብረሽ ያደራጀሽ
እርጉም ልጅሽን በአስካሪነት
አንቺን ገሎ እንዳንኮላ
በራስ ቅልሽ ሲጠጣበት
ቀንዲል ነድሎ ሠብሮ ወጪት
አስለቅሰሽ አስወቅሰሽ
አስተምረሽ ያንን ሹምባሽ።

ይህንኑ የእንግዴ ልጅ
የሠላዮች ሦላቶ ፈርጅ፣
አስረግመሽ ጊዜ ፈቅዶሽ
እንደ አደዋ ድባብ ለብሰሽ።
ዝናሽ ርቦኝ ትብብርሽ
እንዳላፍር መካር ሆነሽ፣
ፈውሺያቸው ልጆችሽን
የታወኩ ያበጡትን
የከረሩ ችኮዎችን
እናት ዓለም ወላድ ሆነሽ።
እንደጥንቱ አድባር ታርቆሽ
በሙት አጥንት አፀፅተሽ
ባራት ማዕዘን ፈውስ ረጭተሽ
ባባት ዓምላክ አሰባስበሽ
በማተብሽ ተለማምነሽ
ይቅር ለግዜር በቃ ብለሽ።
ቸር ይግጠመን!!
ገብርዬ (አትላንታ/ጆርጂያ)

# ከይግለጡ ለወርቃየሁ

ለጥቂት ወራት ተጠፋፍን መሠለኝ። በሠላምታ እንዳልጀምር እንደምላሽ የተሳለው ምላስህ የሠላምታ ማህደሬን እንዳልከፍት አገደኝ። ምነው በነገር ጉነጥከኝ እባክህ! አርፎ መቀመጥ እንደአድርባይነት የሚያስቆጥር ከሆነ በእኔ አስታከህ ድፍን አበሻን ማስቀየም እንዳይሆንብህ ፈራሁ። ደግሞስ ምነው ሁሉንም ነገሬህ። ትዝ እንዲልህ በጥቂቱ ልድገምልህ "የፈሪ ዱላ ይመስል ለሁለት አልጠምድህም ለአሁኑ ገብርዬ ስላለ እሱን በምትክነት ሰጥቼህ እኔ ደግሞ በሌላ ብዕር በሌላ ርዕስ ብቅ ለማለት እሞክራለሁ" ነው ያልኩት። አንተ ግን እንደሸሸት፣ እንደማፈግፈግና እንደአድርባይነት ቆጠርከብኝ። ለመሆኑ ከምንና ከእነማን ነው የሚሸሸው? እንኳን በነፃ ምድር ላይ ሆኜ በወንጭፍ ለምወረውረው መልዕክት ይቅርና መኖሪያዬ ቤተ መንግሥታችሁ ፊት ለፊትም ቢሆን ማለት የምፈልገውንና የሚሰማኝን ከማለት ወደ ኋላ የምል አይምሰልህ። ካገርም ያስወጣኝ ይኼው ግትር ባህሪዬ እንደሆን እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ። ለቆራጥነትህ ማስረጃ አቅርብ እንደማትለኝ ተስፋ አለኝ። ማስረጃውንም ባቀርብ ለአሁኑ ፋይዳ ስለሌለውና ስለማይሰራ «ለፍርድ ቀን» የእኔነቴን እውነትነት በቅርብ በሚያውቁኝ ምስክርነት ትረዳ

ይሆናል። ለአሁኑ ግን ለማረፍና ከአንተና ከገብርዬ መጣጥፍ ቁምነገር መሰብሰብ ስለፈለግኩ ገለል ማለቴን እንደደጅ ጠኚ አትቁጠርብኝ።

ባንተና በገብርዬ መካከል በሚደረገው የሰላምታ ልውውጥ ብዙ የማላውቃቸውን ቁምነገሮች ገብይቻለሁ። ብዕራችሁ ወርቅ ነው። ተናግሮ ያስተምራል፣ እኔም ሆንኩ ብዙዎች ሣይወዱት አልቀሩምና እንደምትገፉበት እገምታለሁ።

ሰቆቃው ወርቃየሁ፦ ለመሆኑ እንዴት ከርመሃል። ከእኔ ጋር የምታደርገው የሠላምታ ልውውጥ ለጊዜው ቢቋረጥም ያንተ ብዕር የሚፈስ የእኔ የደረቀ አድርገህ እንዳትገምት። ሁሌም በሣሣብ ካንተና ከሌላው ወገኔ ጋር ነኝ። ደግሞም ስለሃገር ማሰቤ ስለወገን በአቅሜ መጨነቁ ያበቃ አድርገህ እንዳትገምት።

ይኼውልህ እኛ የአበሻ አሜሪካኖች ሁሉ በጄ ሁሉ በደጄ የሆነልን ቁጥራችን ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ በመሄዱ በአሁኑ ሠዓት እንደዱሮው በየዕለቱ የሐገርና የወገን ጉዳይ እያነሱ መከራከሩና መፍትሄ ለመፈለግ መወያየቱ በአብዛኛው ወገን ላይ የሚታይ አይመስልም። በድንገት ያገር ጉዳይ ከተነሣ በጋራ ተመሣሣይ አቋም መያዙ ላይ ከማተኮር ይልቅ በአዲሱ የወረርሺኝ በሽታ ልክፍት መሠረት የሣሣብ አቅራቢው ዘርና ማንነት ይመረመራል። መልስም ሆነ አስተያየት የሚሰነዘረው ከዚያ በኋላ ነው። እስካሁን ያልደበዘዘና ሊታረም ያልቻለ በሽታ ይሄው ነው። የበሽታው ፈጣሪዎችም የወለዱት ነቀርሣ እንዳይጠፋ አጋጣሚና አመቺ ጊዜ ባገኙ ቁጥር ለማንደጃው ማራገቢያ ማቅረባቸው አልቀረም። ቢሆንም ለሀገር ደግ መመኘታችን አልቀረም። ለጊዜው ከዚህ ብዙ የማቀርብልህ ዜና የለም ሁሉንም ከናንተው ሬዲዮ ሳትሰማው አትቀርም። ፕሬዚዳንት ክሊንተን ለሁለተኛ ጊዜ በርዕሰ ብሔርነት ቢመረጡም ቃለ መሃላቸውን በቅርቡ ፈፅመው በትረ ስልጣኑን ለሚቀጥሉት አራት አመታት ይዘዋል። ሁለተኛ በትንሹም ላይሳሳቱ፣ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ፣ የሃገሪቱን የውጭ ግንኙነት በአሜሪካ ጥቅም ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና አሜሪካ በዓለም ላይ ያላት የበላይነት የማይገሰስና የማይነቃነቅ ጠንካራ መሠረት ላይ እንደሚያውሉት ምለው ተገዝተው ዳኛና ቄስ፣ ታዛቢ ህዝብና የውጭ ተጋባዥ እንግዶች ባሉበት ቀኝ እጃቸውን ከፍ አድርገው ቃል በመግባት ሲያስጨበጭቡን ከረሙ።

በሌላ በኩል ደግሞ ያንዱ ቤት ሲሰረግ ሌላው ቤት ለቅሶ አይጠፋምና የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉስ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ የነበሩት ልዑል ማንትስ የተባሉት ደግሞ የእድሜያቸውን ሩብ ዘመን በስደት አሣልፈው ላገራቸው መሬት ሣይበቁ በአሜሪካ መናገሻ ከተማ ህይወታቸው አልፏል። የሚያውቋቸው በከፍተኛ ስሜት ሀዘናቸውን ሲገልፁ በስም የምናውቃቸውም ከንፈራችንን እየመጠጥን ነፍስ ይማር ብለናል። እግዚያብሔር አስቀድሞ የሚወስደው የሚወደውን ነውና። ስለቀብራቸው ሥነሥርዓት ካንተ እጠብቃለሁ። የሞተ እዚህ እንደማንቀብር ጥንት ነግሬሃለሁ።

በአሜሪካን ኑሮ የአበሾች ፖለቲካ የጊዜው አቋም ደግሞ ትንሽ ረገብ ያለ ይመስላል። እንደቀድሞው ፈንጠር ፈንጠር የሚሉ ብዙ አይታዩም። አዲስ የፖለቲካ ድርጅትም እንደበፊቱ በየቀኑ እንደአሸን አይፈለፈልም። በቅርቡ ግን አንድ በቀድሞ የሃገሪቷ የበሰሉ ምሁራን በብዙ ጥናትና ቅድመ ዝግጅት የተቋቋመ ነው የሚባል አንድ ድርጅት ብቅ ብሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ራሱንና የድርጅቱንም መመሪያና ደንብ አስተዋውቋል። ብዙዎቹ አድናቆታቸውንና ድጋፋቸውን እንደሚሰጡ ቃል ሲገቡ አንዳንዶቹ ደግሞ ጥፈር ዘመት የማዘናጊያ ድርጅት ነው በሚል በትዝብት ተመልክተው ለወደፊት «ኧወጣዋለሁ» የሚለውን ለማየት በጉጉት ይጠብቃሉ። ከእናንተው ጋር በምስጥር የተላከና የተዋቀረ ቡድን ካልሆነ ነገሩ ደግ ሣይሆን አይቀርም። እስካሁን ድረስ ግን የት እንደነበሩ ሊገለጥልኝ አልቻለም።

ወገን ወርቃየሁ፦ በሌላ በኩል የአሜሪካ ነዋሪ አበሻ ለኑሮው መቃናትና የወደፊት ምኞቱ ግብ እንዲመታለት ከመቼውም ይልቅ በአሁኑ ሰዓት ጠንክሮ መሥራቱን ስታይ ያኮራሃል። ለአንድ ሥራ ብቻ ሳይሆን ለሁለትና ከዚያም በላይ ለሆኑ የእለት ሥራ ጉልበቱን የማይሸጥና ከሌላው በሁሉም ነገር በልጦ ለመታየት የማይፈልግ የአበሻ ዘር ያለ እንዳይመስልህ። አበሻ ደከመኝ ማለት ትቷል። የሃገሩን ጉዳይ ግን በለበጣ ዓይን የሚመለከት ቁጥሩ ቀላል አይደለም። ለሃገር ሠላምና ለእኩልነት በያለበት ቦታ የበኩሉን ድጋፍ ከመስጠት ይልቅ አገር ቤት የተረፉትን ዘመዶቹን እንደምንም ማስመጣት እንደአቋራጭ መንገድ አድርጐ የቆጠረው ይመስላል። በዚህም ይመስላል ድሮ ያላሰበውን ከሃያ አመታት ቆይታ በኋላ ዜጋ ለመሆንና አሜሪካ ውስጥ የቆየባቸውን ሠላሣ ዓመታት አስመስክሮ የመኖሪያ ፈቃድ ለማውጣት በየኢሚግሬሽኑ በራፍ ላይ የአበሻ ክምር መታየት መጀመሩ እያስገረመን ነው። አልፎ አልፎ በአንዳንድ ስብሰባ ቦታዎች ስለሃገራችን ያለችበት ሁኔታ የሚያነጋግር ስብሰባ ሲደረግ ውይይቱ ሁሉንም ማስደሰት ስለማይችል ተማምኖ የጋራ አቋም ከመያዝ ይልቅ በሃገር ጉዳይ ውይይት ላይ ኩርፊያ በዛ። የዘመኑ የአበሻ ፖለቲካ መደምደሚያው ኩርፊያ ሆኗል ብልህ እንዳይገርምህ። በየአደባባዩ የማየው ነውና።

ከዚህም ሌላ ሳልነካው የማላልፈው ጉዳይ አለ። አንድ ሰሞን ያኔ ኢትዮጵያ መገንጣጠልና አዳዲስ አገርና ዘር መፍጠር በተጀመረ ሰሞን በደህናው ቀን አዲሲቱ ነፃ አገራቸውን የሚያስተዋውቁ ጥፋት ወይም ወንጀል ፈፅመው በፖሊስና በህግ ሲያዙ ግን «ኢትዮጵያዊ» ነን የሚሉ እንደአሸን በዝተው ነበር። በአሁኑ ሰዓት ግን አቅምና ልካቸውን ገምተው "የማያዛልቅ ፀሎት" እንዲሉ ከዚህ አባባላቸው የቀዘቀዙ ይመስላል። ግን አልፎ አልፎ ይህንኑ ድግግሞሽ በአንዳንድ ቦታ ታያለህ። በዚያ ሠሞን ሚኒሶታ በሚባል እስቴት አንድ የዞረበት ፍጡር በሚሰራበት መስሪያ ቤት የገና በዓል ግብዣ ላይ አጠር ያለ ንግግር ለሥራ ባልደረቦቹ ካደረገ በኋላ ራሱን ከአፍሪካ ቀንድ «ኦሮሚያ» ከምትባል አገር የተገኘ አድርጐ ያስተዋውቅና በፈረንጆቹና በእሱ አገር መካከል ስላለው የገና በዓልና የቀን ልዩነት ዘርዝሮ በማስረዳት አድማጩን ያስገርማል። በዚህ በያዝነው ወር ደግሞ ይኼው ፍጡር ከፍተኛ የመኪና አደጋ ያደርስና በፖሊስ ተይዞ ማንነቱን ሲጠየቅ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ይገልፃል።

በዚህ መካከል ቀደም ብሎ የዚህን ፍጡር ሃገር ሰምቶ የነበረ የሥራ ባልደረባው «አረ እሱ ኦሮሚያ ከሚባል አገር ነው» በማለት ክርክር ቢገጥም ያ ፍጡር ምን እንዳለ ታውቃለህ? ወደ ስራ ባልደረባው ዞር ይልና «ኢሱ ለዚህ ጊዜ አይሆንም» አለው አሉ። እና አሁንም አንዳንዶቹ «ዋና ይዘው በትርፍ የሚጫወቱ»፣ «ለደጉ ጊዜ ሌላ ለክፉ ቀን ኢትዮጵያዊ» እየሆኑ እኛንም ሆነ አገራችንን ትዝብት ላይ ጣሏት እልሃለሁ።

ያገር ልጅ ወርቃየሁ–

ሰሞኑን ያሣቀኝን አንድ ነገር ላውጋህ። አገር ቤት ሳለሁ አንዳንድ ቀልደኞች በሰዎች ስምና ሐይማኖት ቀልድ ሲፈጥሩ እሰማ ነበር። እንዴት መሰለህ ቄስ አሊ፣ ሼክ ጳውሎስ፣ መምሬ አብደላ እና ሌላም ሌላም እየጨመሩ አጠራሩን ሌላውን ለማሳቅ ይጠቀሙበት እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ለእውነቱ ከሆነ የሃይማኖት መሪዎች የማዕረግ ስም ከሃይማኖታቸው ምንነት ጋር የተያያዘ ነው። ለምሣሌ የክርስቲያን ጳጳስ «አቡነ እገሌ» የሚል ስም ሲሰጥ ለእስልምና ሃይማኖት ደግሞ «ሼክ፣ ሱልጣን» እገሌ ተብሎ ማዕረጉ ይደለደላል። ግን የእስላሙን የሃይማኖት መሪ የማዕረግ ስም ለክርስቲያኑ በመስጠት ተስማሚ ያልሆነ መጠሪያ መስጠት በደንቡ መሰረት ተገቢ ሆኖ አልተለመደም።

ታዲያ እዚህ አሜሪካ የሃይማኖት ዓይነት በየቀኑ እንደአሸን በሚፈለፈልበት አገር «የእገሌ ሚኒስትሪ» በሚል ስም በየሥርቻውና በየመንደሩ አዲስ ስም በመስጠት አዲስ ሃይማኖት ወይንም የአንዱ ሃይማኖት ተቀጥላ በማቋቋም የሃይማኖት መሪ መሆን የሚያግድህ የለም። ታዲያ በዚያ ሰሞን አንድ ወዳጄ ወደሚሳተፍበት ቤተክርስቲያን አብሬው እንድሄድ ጋበዘኝና እሁድ ጠዋት ወደተባለው አዳራሽ አብሬው በመሄድ በሙዚቃና ዳንስ መሰል በሆነ ውዝዋዜ የታጀበውን ሰበካ ሳዳምጥ ቆየሁና ሲያበቃ መውጫው በር ላይ ሰባኪው በር ላይ ቆሞ ምዕመናኑን እየጨበጠ ሲያሰናብት የኔም ተራ ደርሶ እጄን ወደ ሠባኪው ዘረጋሁ ተዋወቅን። ምን ብሉ እንደተዋወቀኝ ታውቃለህ «ቄስ መሀመድ ጆንሰን»።

ሠባኪው በመሣቁ ተገርሞ አጥብቆ ጠየቀኝ። ልመልስለት አልፈለኩም። ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ ብዬ ተለየሁት። እንኳን ተመልሼ ላናግረው ቀርቶ በዚያ ሠፈር ባለፍኩ ቁጥር በሣቅ እፈነዳለሁ። ለካ አሜሪካም ውስጥ «ወሉዬ» አለ። አቶ ከበደ አሊ ሲባል አልሰማህም።

እንግዲህ ለጊዜው ደህና ሁንልኝ። ላንዳፍታ በይዘቷ ጥሩ ገፅታ እየተላበሰች መጥታለችና አንጠፋፉም። ያንተና የገብርዬን እንዲሁም ባለወርቅ ርዕስ ከታቢው የውሂብ ጥሩነህን መጣጥፍ ከገጿ ላይ ማጣት ስለማልፈልግ እባካችሁ በጅምራችሁ በርቱበት። ለወደፊት ግን በተለይ ለውሂብ ጥሩነህ የምለው ይኖረኛል። እስከዚያ በቸር ያቆየን።

ይግለጡ ነኝ – ከነፋሲት


R
T
S

RAPID TAX
SERVICE

ፈጣንና ቀልጣፋ
የታክስ
ሥራ አገልግሎት

PROFESSIONAL
TAX PREPARATION
INDIVIDUAL & BUSINESS
ELECTRONIC
TAX FILING

OFFICE HOURS
*Monday - Friday 8:00am to 7pm*
*Saturday 9am to 5 pm*
CALL (RTS) LEAKE MALEDE
PHONE: (404)296-3088
FAX: (404)296-7413
E-Mail: rapidtax@aol.com
*Accepted the past two years by the IRS to participate In the electronic filing Program*

ASAP COPIES

BEST PRICE IN TOWN!
*High-Speed Duplicating*

Business Cards
Flyers
Typesetting
Resumes
Fax Services

ካብኛን!!

Photo ID
Passport Photos
Laminations
Greeting Cards

Letterheads
Envelopes
Rubber Stamps
Copy Service
Self-Serve Copies

Conveniently located in Campus plaza Shopping Next to Dekalb Book Store

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



## እርስ በእርሳችን እንረዳዳ

ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና (ማቴ 25–35–37)

በእውነት እነዚህ ከላይ የምናያቸው ቃላቶች ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አዲሶች አይደሉም። ለምን ከስር ከመሠረታችን ይህንን ስናደርግ ነውና ያደግነው። ይህንን ያቋረጠ ቤተሰብ ወይም ኢትዮጵያዊ አለ ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ዕለት ከዕለት የምናደርጋቸው የቸርነት ስራዎቻችን ናቸውና።

የእኔም የዛሬው ሃሳብ ከዚህ የወጣ አይደለም። መቼም ሁላችንም ወደዚህ ሀገር ስንመጣ ተደስተን የመጣን የለንም፤ ሁላችንም የተለያየ ችግር አለብን። እንግዲህ ይህንን ችግራችንን ለማስወገድ ነው ባህር ተሻግረን የማናውቀውን የውጭ ሀገር ባህልና ኑሮን የተያያዝነው።

ወገኖቼ ነገር ግን ሁላችንም መዘንጋት የሌለብን አንድ ነገር አለ። እንደምንሰማውና እንደምናየው በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ብዙ ችግሮች አሉ። ዋናው ትኩረት ችግሮች አሉ ካልንና ወገኖቻችን እየተቸገሩ ነው ካልን ምን ብናደርግ ችግራችንን ማሻሻል እንችላለን ብለን መጠያየቅና መፍትሔ መፈለጉ ላይ ነው። በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ውስጥ ቁርስ ተበልቶ ምሳ የማይደገምበት፣ ምሳ ተበልቶ ራት የማይገኝበት ጊዜ ሆኖአል።

እንግዲህ ከላይ እንደዘረዘርኩት ምን ማድረግ አለብን ለሚለው እኔ አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ። ይኸውም በአሁኑ ሰዓት ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ወደ አሜሪካ ያልወጣ ባይኖርም ግማሾቻችን ኑሮ ከብዶን ቤተሰብ መርዳት አልቻልንም። ቢሆንም አንድ አማራጭ አለ ብዬ እገምታለሁ። ይኸውም በያለንበት አካባቢ አስር አስር ሰው ሆነን መሰባሰብ፣ በየሳምንቱ ቢያንስ አምስት ብር ከተቻለ ከፍ ያለ ብር እንደ ዕቁብ መጣል። ከዛ እጣውን በየሳምንቱ ማውጣት ከአስሩ ውስጥ ለአንዱ በአንድ ሳምንት ውስጥ አምሳ ብር ወይም ከዛ በላይ ደረሰው ማለት ነው። ይህም በቀላሉ እያንዳንዱ በየሳምንቱ ቤተሰቡን ረዳ ማለት ነው። ቤተሰቡን ረዳ ማለት አገሩንና ወገኑን ከችግር አዳነ ማለት ነው።

በእውነት እያንዳንዳችን ይህንንና የመሳሰለውን ካደረግን የመንፈስ እርካታ የምናገኝ ይመስለኛል፤ ሌላው ደግሞ በየሳምንቱ በመገናኘታችን የእኛም ጓደኝነት፣ ሕብረትና መተሳሰብ ከቀን ወደ ቀን ጨመረ ማለት ነው። ይህንን በጐ ምግባር ለማድረግ እግዚአብሔር ይርዳን።

ሚኪያስ አለሙ–ከSan Jose

## መሰላል ... መሰላልነቱ ለመወጣጫ ነው!!

አገኘሁ እንግዳ–ከአዲስ አበባ

በመዲናችን በሸገር ምሽቱ የራሱ የሆነ የአጀብ እድምታን የተጐናፀፈ ሁኔታዎችን አዋህዶ ሲያልፍ የጠጅ ቤትን የአካኪ ዘራፍ አስረሽ ምቺው ቲያትራዊ ህይወትን የሚያህልና ብዙ ቁም ነገሮችንም የሚያካትት መድረክ መኖሩን ይህንን ገፅታ የሚካፈለው ማህበረሰብ በውል ያውቀዋል። የአዝማሪ ልብ የሚነካ ንግርት የስንኝ ቋጠሮ በየጊዜው ለሚካሄዱ የወል ክንዋኔዎች መግለጫነት የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም።

መሰላል ከሆነ የዘመኑ ሰው፣

እንጨት መቀጣጠል አናጢም ይተው።

የምትለው የአዝማሪ የስንኝ ግጥም ዛሬ በህብረተሰባችን ውስጥ ሥርዓተ ማህበር በተለዋወጠ ቁጥር መወጣጫ ርካብ ስለሆኑት የዘመናችን ሰዎች የምታስተላልፈው መልዕክት ብዙ ቦታ በተበታተነ ልብ የሚዋዥቀውን የአገሬን ሰው ጎሳና ዘረኝነት ሲያምሰው፣ ለዚህ ስርዓት ቅኝ–ሀሳብ የተቀፈደዱ የአዕምሮ እስረኞች ሲያናውጡት ዳር ሆኖ ላለመመልከት ሁነኛነትን በኪነታዊ መግለጫ ለመጠቆም የታሰበች ናት።

በየሥርዓተ ማህበሩ የሚታቀፉ የርዕዮተ ዓለም ምርኮኞች የራሳቸው የሆነ የመታቀፊያ ብቃት ማስመስከሪያ ያላቸው ሲሆን የዘመናችን መረማመጃዎችም በራሳቸው ስብዕና ላይ ሥርዓቱ እንዲጓጓዝ መንገድ ጠረጋ የሚያከናውኑት የሦስት ሺህ ዘመን አንድነትን ጉዳት ላይ ጥለው በተፈረካከሰ ግዛታዊ ጥላ ውስጥ ተጠልለው ነው። በሁለት ቋሚ አጠናና የቁርጥራጭ አግድሞሽ አጠናዎች ግጣም የሚፈጥሩትን መሰላል አምሳያዎች ባለፉት ሥርዓተ ማህበር በእምቢተኛነትና በአይበገሬነት የሚመሰሉት በተለይ አፍላ ወጣቶችን መሆኑ የዛሬዎቹን ትውልድ ሥነ ምግባር ግምት ውስጥ የሚከቱና የወቅቱን የእንቅስቃሴ ሂደት ጥያቄያዊ መልዕክት ውስጥ ያካትቱታል።

በዓለማችን በተለይ ደግሞ በአህጉራችን ጎሰኝነት የሚያስከትለውን የማህበራዊ ግኑኝነት ሳንካና የፍልሚያ መዘዝ በአለም አቀፍ የዜና አውታሮች የሚንቆረቆረውን የመረካከሻ የዜና እውነታዎች በልቦና ውስጥ በአደራ ላለማስቀመጥ ምለው የተገዘቱት የሥርዓቱ መጓጓዣ ሐዲዶች የዕለት ተዕለት ትንፋሻቸው በሥርዓቱ ውስጥ በቆይታ መልክ ላላቸው ህልውና ጊዜያዊነት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በስተቀር ታሪካዊ ዘለዓለማዊነትን እንደማያጐናፅፋቸው እሙንነቱ አጠራጣሪ አይደለም። በኢትዮጵያዊነት፣ በሐበሻ የአንድ ዝርያ መለያ ባንዲራችን ስር እንሰባሰብ የሚለውን የአንድነት መልዕክት በጉያ ደብቆ ትናንት ለተመሰረተ ብሔረተኝነት የአደባባይ ፋኖነት መግለጫ ምሳሌ መሆን

የተወቃሽ ህሊና ባልተቤትነትን የሚያረጋግጥ የጊዜያዊነት ሰሌዳ ላይ የሚያስመዘግብም ይሆናል።

እንዴት? ለምን? ወዴት? የሚለው የራስ በራሳችን የህሊና መጠይቅ መሰሳልነታችንን ከሚያጐላው ድርጊታችን የወቅቱን ፍርክርክ አንድነት ከሚያመጣው ብልሹ ታሪክ ግንዛቤ ጋር ተዳምሮ የተወጠነ ቢሆን የሥርዓቱ እንደራሴዎች ላለመባል ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ህይወታችን በእግረ ሙቅ ተቸንክራ ጣር ውስጥ እንዳትገባ «የአገርህን እወቅ» ተከተል መርሆ ማበጃ መንገድ ሲሆን፤ መሠረታዊ በሆኑ በዕውቅና አድማሶች ውስጥ ለመንሸርሸር ዛሬን ሳይሆን ነገን በማሰብ ሁኔታዎችን ዳር ለማድረስ የአንድነት ካባ አጥልቀን ያሳለፍነውን ረጅም የትስስር ጉዞ እንቀጥለው ዘንድ በሚቀጥለው ትውልድ የውሁድ እምነት ላይ ተፅዕኖ እንዳናሳድር ራሳችንን የተመከሮ ዘመቻ እናካሂድበት።

በዚህ የትስስር የውህደት ጥያቄ በተለይ የምሁራን ቀርፋፋ አዝግመት የለፉበትን የወረቀት ምስክር ዕውቅና ክብረት የሚነፍገውና የራሳቸውን የሽንገላ ጊዜያዊ የህይወት ለውጥ ለማስተካከል ብቻ የተዘየደ መሳውን የአቢሲኒያን ማህበረሰብ አደጋ ላይ እንደሚጥል ግምቱን በዘፈቀደ ይሁን ብሎ የቁካኔ ፍርድ እንደመበየን ይቆጠራል። ቃል አባይነትና የብኩን አዕምሮ ተሸካሚነት ካላቸው እውቀት ጋር ሲመሳከር አዋቂነታቸው አንድ ቦታ ደርሶ ቆሞ የቀረና የሚንቀሳቀስ ትቢያ የለበሰ አስከሬን ምሳሌ ነው። ለሥጋቸው ያደሩ ነገን የማያስቡ ምሁሮች በተቀፈደዱት የመላ ምት ህይወት የሚመለኩት በሥርዓቱ አድራጊ ፈጣሪዎች ብቻ መሆናቸውን ሊያውቁትም ይገባል። ህዝቡ ለእነዚህ ቦታ የለውም የሚያውቀውን ታሪክ በአንካሴ እንደሚያስኬዱት ልብ ብሎ ያውቀዋል። በእጅ ሙያ ብቻ በሚታወቀው አናጢ በሚሰራው መሰላል የሚመሰሉት እነዚህ ምሁሮች ነገ በሚለየው የአደባባይ ምስጢር ዘመኑ ተፍቶአቸው ከሥርዓተ ማህበሩ ጥንብ አንሳዎች ጋር በአንድ ጉራ ተሰልፈው ህዝቡ ቁልቁል እንደሚያያቸው ዕድሜና ጤና ይስጠን የምንል በሙሉ የምናየው ዕውነት ይሆናል። ደህና ሁኑልኝ።

---

## ለሠነፎች አዋጅ!

ከሁሉ በፊት ሰላምና ጤና ለላንዳፍታ መፅሄት አዘጋጆች እላለሁ። ከእናንተ የተረፈውን ለእኔ ስለማይነሳኝ ፈጣሪዬን አልወተውተውም። ዳሩ በአሜሪካ ሞልቶ ለተረፈ ሰላምና ጤና ምን የጤናና የሰላም ምኞት ያስፈልጋል? እኔ እንኳን ከሀገራችን መዲና የመጣሁት በቅርቡ ነው። እዚያ ያጣሁትን ሰላም በባዕድ ሀገር አግኝቻለሁ። አንድ በሉልኝ። እዚያ ያጣሁትን ጤና እዚህ አግኝቻለሁ። ሌላውም እንደእኔ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም። የሆነው ሆኖ የውስጥ ዘሀኔ ግን እንዳለ አለ። ምነዋ ቢሉ የተቀሩት ወገኖቼ ሰቆቃና ዋይታ ረሀብና እርዛት በአጠቃላይ የሀገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብን ችግር የውስጥ አካል ክፍሌን እየጐዳው ያለ ጉዳይ ሆኖብኛል።

እንዲያም ሆኖ ያቺን ድሀ ሀገሬን እናፍቃለሁ። አቦ! እናንተ መጥኔ ይስጣችሁና ይሄ የአምቡላንሱና የፖሊስ መኪናው ጩኸት ነፍሴን ሊያወጣው ነው። ያገራችን ጅብ በስንት ጣዕሙ!! አምቡላንሱ እንዴ ከሚሮሀብኝ የአገሬ ጅብ ሌሊቱን ሙሉ ሲያላዝንብኝ ቢያነጋ እመርጣለሁ። እሺ ይህን ያህል ካልኩ ወደ ዋናው ጉዳይ ልለፍ እንደመጣሁ አካባቢ በተለያየ አጋጣሚ እጄ የገቡት የተለያዩ መጽሄቶችን አነበብኩ። ምርጫዬ ሆነና «ላንዳፍታችሁን» ወደድኳት። እናም እኔም የበኩሌን እህ! እጅህ ከምን አትሉኝም። ለዛሬ ለመተዋወቂያ ያህል በርዕሴ ላይ ላስፈርኩት ስንኝ ሰንቄ ቀርቤያለሁ። እነሆ ተቀበሉኝ።

### ለሠነፎች አዋጅ!

ያዳም ዘር የሄዋን ከፊል ሕይወት ያለህ
ከፅንፍ እስከ አፅናፍ ትቀሰቀሳለህ።
አዋጅ ለሠነፎች ለሴቱም ለወንዱ
በጊዜው ላይ ቆመው በጊዜው ለሚያብዱ።
ሳይሠሩ ታክተው ድክም ለሚላቸው
የሥራ ትርጉሙ ውሉ ለጠፋቸው
ሥራ እንደደመና ክብድ ለሚላቸው
ሞራላቸው ወድቆ ሀሞት ላነሳቸው።
ይጉሰም ነጋሪት ይነፋ እምቢልታ
ይድረሳቸው ጥሪው በያሉበት ቦታ።
ጊዜ ጊዜ እያሉ ይማረሩብሃል
አንተ አትናገሬ ምንድን ይሻልሃል?
ይስማልኝ ችሎቱ ይነሳለት ክሱ
«አይ ጊዜ!» በማለት አይመካኝ በእሱ።
ስንፍና ሲጣነው ማደግ ሲችል ሠርቶ
በጊዜ ያመካኛል ቆሞ ተጉልቶ።
በምኞት በተስፋ የምታሰላልስል
አፍ ከፍተህ አትጠብቅ የወፍ ልጅ ይመስል።
ሁለት ሞት ይሞታል ሰነፍ በሕይወቱ
አንዱ የማይቀረው ሌላው የቁም ሞቱ።

መክብብ ነኝ (ከዋሽንግተን—ሲያትል)

---

## ይድረስ ለእያዩ ቢልልኝ

በተቻለህ መጠን እውነትን ለማግኘት ያደረግከው ጥረትህ ጥሩ ነው። ባለፈው ጊዜ በላንዳፍታ መጽሔት እንደገለጽከው በውጪ ጴንጤ በመባል የሚታወቁና ራሳቸውን ግን ክርስቲያኖች(አማኞች) ብለው የሚጠሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ተከታዮች በስብሰባቸው በመገኘት የሚያደርጉትን የአምልኮ፣ የመዝሙር፣ የስብከትና የትምህርት ክፍለ ጊዜ አብረህ በመሳተፍ የአሉ አሉ ወሬ ሳይሆን በአይንህ አይተህ በጆሮህ ሰምተህ የተገነዘብከውና የተረዳኸውን አካፍለኸናል። ነገር ግን በቦታው በመገኘትህ ከእግዚአብሔር ቃል አንፃር ሊሆኑ የማይገባቸው ሲሆኑ፣ ሊነገሩ የማይገባው ሲነገሩና ሊደረጉም የማይገባቸው ሲደረጉ አየሁ ብለህ የተመለከትካቸውን ጉድለቶች በመጥቀስህ ስለ ጴንጤዎች ሰዎች ያላቸውን አመለካከት ቀና እንዳይሆን ለማድረግ አስተዋጽኦ ሳያደርግ አይቀርም። ምክንያቱም ከአንድ ራሱን የእግዚአብሔር ሰው ነኝ ብሎ ከሚል ሰው ሊንፀባረቁ የማይገባቸው ተግባራትን ሊነገሩ የማይገባቸው ንግግር ለመስማትህ የጆሮ፣ ለማየትህ የአይን ምስክርነትህን በመግለጽህ ነው። ሆኖም የእያንዳንዱ ሰው መረዳት የተለያየ በመሆኑ ከላይ የተገለጸው የአንተ

መረዳት ሲሆን በጠቀስከው ቀንና ቦታ የነበርኩ ልክ እንዳንተ ሌላ የአይን ምስክር ደግሞ አንተ መረዳትህን እንደገለጽከው መረዳቴን ልግለጽ።

በመጀመሪያ ደረጃ መጥቀስ የምፈልገው ስለ ጽሁፍህ ጉዳይ ነው። ይኸውም ስህተቶችን ስህተቶች ብለህ ገለጽክ እንጂ በአንጻሩ ትክክለኛው ምን መሆን እንዳለበት አልገለጽክም። በመሆኑም ሲያደርግ ለሚሳሳት ወቃሾችን እንጂ መልካም ነገር በሙከራ ለማግኘት የሚጥርን ዜጋ የሚያፈራ መልዕክት ለህዝብ አላስተላለፍክም። ይኸውም ማንኛውም በአለማችን የምናያቸው መልካም ነገሮች ሁሉ በአንዴ ካሉበት ደረጃ የደረሱ እንዳልሆኑ የታወቀ ነው። ወደበለጠ መልካምነት ደግሞ ያድጋሉ። ብዙ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ግን አስፈላጊነቱ ስለማይታየኝ አንድ ብቻ ልጥቀስ። ስለሕንጻ ብንመለከት የድሮና የአሁን ወደፊትም በጣም ይለያያሉ። የድሮው ብዙ ገንዘብ ብዙ ማቴሪያልና ጉልበት እንዲሁም ጊዜ ፈጅቶ ከአሁኑ ጋር ሲወዳደር ብዙ ጉድለት አለው። አሁን ካለውም ለወደፊት ሊገነባ በሰዎች አዕምሮ ያለው ይበልጣል። ምክንያቱም አሁን ካለው ምን ጉደለው እየተባለ ጉድለት የሌለውን ለመገንባት ስለሚጥሩ ነው። እንዲሁም በሃይማኖት በኩል በተለይ በኢትዮጵያው መሐል ድሮ ምን ይመስል እንደነበረና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ምን እየመሰለ እንደመጣና አሁን ምን እንደሚመስል ወደፊትም ምን መልክ እንደሚኖረው ነገሮችን ከተመለከትን ብዙ የእድገት ለውጦች እየታዩበት ነው። ምሳሌ ልጥቀስና እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስርዓት የሚደረገው በአጠቃላይ በግዕዝ ቋንቋ ብቻ ስለነበር ሰምቶ የሚረዳው ከመቶ አስርም አይሆንም ነበር። ይህም የሚያሳየው አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዳይሆን ቋንቋው ትልቅ ተጽዕኖ ማድረጉ ሲሆን እንዲሁም የበዓል ብዛት ሰው በሃይማኖት በዓል ሰበብ እንዳይሠራ ስለሚሆን ድህነትን ከማፍራቱ ባሻገር ሰው ያልገባውን ስለ ሃይማኖቱ ጠይቆ እንዳይረዳ አትመራመር በመባል የሃይማኖት ዕውቀት መሐይማን በብዛት ለማፍራት ተበቅቶ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በመጀመሪያ ደረጃ ከበዓላት አስራት መፈታቱን ሰው ሰርቶ እንዲበላ በር የከፈተ ሲሆን ከግዕዝ ሌላ ደግሞ በየቋንቋውም በመሰበኩ ድሮ ያላገኘውን የሃይማኖት የእውቀት ጭላንጭል እንዲያገኝ እየረዳው ነው። አሁን ደግሞ በበለጠ ሁሉም ሊገባው በሚችል ቋንቋ እየተማረ የክርስትና እምነት የእውቀት ምንጭ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ከመቼውም በተሻለ መንገድ ሰዎች ማጥናትን ተያይዘውት እናያለን። ከዚህ የምንረዳው ቢኖር አሁን ካለው እጅግ በበለጠ ለወደፊት መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እንደሚያጠኑትና እንደሚለማመዱት ነው። እንግዲህ ይህ እንዲህ እንደሆነ ከተረዳን በማንኛውም አይነት መንገድ ለመልካም ተግባር የሚንቀሳቀስ ፍጡር ሁሉ ብዙ ትክክለኛ ተግባራትን እንደሚያደርግ ሁሉ በአኳያውም ሊሳሳት ይችላል እንጂ ከመጀመሪያው ፍጹም ደረጃ ሊደርስ አይችልም። ነገር ግን ከዕለት ዕለት ስህተቱን እያረመ ወደተሻለ ደረጃ በማደግ ያልፋል። የማይሳሳት የሚመስለውና የማይሳሳት የሚመስል ግን ራሱን ሳያሳትፍ ሁልጊዜ ተመልካች ብቻ የሆነውን ነው። በየቦታው ለትዝብትና ለአቃቂር ብቻ እንደሚመላለሱት ማለቴ ነው። ሆኖም የበለጠ ስህተትን እየሰሩ እንደሆነ ራሳቸው አያውቁም። ሰዎችም አያውቁባቸውም። አንድ ህፃን ልጅ ጠርተን ብርጭቆ እንዲያመጣ አዘነው እሺ ብሎ ታዞን እያመጣ እያለ ብርጭቆውን አጥብቆ ለመያዝ አቅም አጥቶ ቢወድቅበትና ቢሰበርበት ምን ያክል ያልጠነከረ ጉልበት እንዳለው ቢያሳይም ታዛዥነትን አሳይቷልና ሊመሰገን ይገባዋል እንጂ ብንቆጣው አግባብነቱ ለማንም የሚታይ አይመስለኝም። ዛሬ ባለመጠንከሩ ቢሰበርም ሁሌ ባለበት አይኖርም ሲጠነክር የበለጠ ያደርጋል። እየቻለ እምቢ አላደርግም የሚለው ግን እጅግ አጥፊ ነው። በመሆኑም ራስህም ስለራስህ እንደገለጽከው የራስህ ግንድ እያለህ ስለሌላው ስንጥር ማውራትህ በጌታ ፊት ከተጠያቂነት አያስመልጥህም። ከሌላ እሻላለሁ ማለትህም መሻልህን በፍሬ ይሁን እንጂ በቃላት አይሁን። ለሁሉም ሌሎችን ሁሉ መውደድ የምትችልበትን ፍቅር ይስጥህ። እንደገናም በፍቅሩ ይገናኝህ።

አለምነሽ–(ከአትላንታ)





Open 7:30 pm
Show Time
9:30 pm
Close 2:00 am; Sat. 3:00 am

LIVE REGGAE
AND
WORLD MUSIC
7 Nights a Week

Experience
the music
the groove
the culture
the fun!!

# እንዲህ ሆነ !

## ከዜና ማኅደር

### ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ በጥይት ተገደሉ



<u>በግፍ የተገደሉት ባህታዊ አባ ፈቃደ ሥላሴ</u>

ጥር 1 ቀን 1989 ዓ.ም. አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ በሚገኘው ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የንግሥ በዓል ይካሄዳል። በመጀመሪያ ታቦቱ በ"ፓትሪያርኩ"፣ በጳጳሳትና በካህናት ታጅቦ መጥቶ ሁለት ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ዞሮ እንደቆመ ያሬዳዊ ዜማና የሰንበት ተማሪዎች ዝማሬ ተሰምቶ እንዳበቃ የደብሩ አለቃ ንግግር በማድረግ የዕለቱን ትምህርት እንዲያደርጉ ፓትሪያርኩን ጋብዘው አቡኑ ለንግግርና ለስብከት ሲዘጋጁ አራት ባህታውያንና ሕዝቡም አብሮ እጅ በማውጣት «ያቀረብነው 21 ጥያቄ ይመለስልን» ሲሉ ይጠይቃሉ። በበዓሉ ላይ የተገኙትን አቡነ ጳውሎስን የኦርቶዶክስ እምነት መሪነትን የሚቃወሙና የማይቀበሉ ባሕታዊያን በወቅቱ በኃይማኖቱ ላይ እየደረሰ ያለውን መከፋፈል ለመግታት፣ እምነታችን ላላ ኃይማኖታችን እየተደፈረ ነው በሚል «በማህበረ ሐዋርያት» በሚል ስም የተቋቋመው አዲስ ማህበር ያዘጋጀውን 21 ነጥብ ያለው የጥያቄ ጽሑፍ ለመስጠት ባህታዊያኑ ቀረብ ለማለት ይሞክራሉ።

በዚህን ጊዜ አንድ ፖሊስ «ጥያቄውን በፅሕፈት ቤታቸው እንጂ በዚህ ቦታ መጠየቅም መመለስም አይቻልም ብለዋል» ሲል መልስ ይሰጣቸዋል። ከዚህ በመቀጠልም የማህበረ ሐዋርያት በአቋም ደረጃ ያስተላለፉትን 10 ገጽ የያዘ ወረቀት ለፖሊሱ ወርውረው ለፓትሪያርኩ ስጥልን እንዳሉትና እንደተቀበላቸው ባህታዊ ኃ/ሚካኤል የተባሉ ገልጠዋል። ወዲያው ግርግርና ጫጫታ ተፈጥሮ በዚህ ጊዜ ስለተፈጸመው ነገር የተለያዩ ነገሮች ተሰምተዋል። በአንድ በኩል ፓትሪያርኩ ከጉናቸው ሽጉጥ በማውጣት በታቦቱ ትክክል ወደ ሰማይ አንድ ጥይት እንደተኮሱና ከዚያም በመቀጠል አጠገባቸው የነበሩ ሊቀ ብርሃኑ የተባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቅርብ አለቃ ሽጉጣቸውን አውጥተው ሲተኩሱና ሌሎችም ከየነጠላቸው ስር ሽጉጥ በማውጣት እየተኮሱ ሳለ ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ መውደቃቸው ሲወራ በሌላ በኩል ደግሞ የአባ ጳውሎስ ጠባቂ የሆነ ፖሊስ ተኩሶ እንደመታቸው ተወርቷል። ። በዚህ መሃከል ባህታዊ አባ ፈቃደ ሥላሴ ፓትሪያርኩ አጠገብ በቅርብ ዕርቀት ተመትተው ራሳቸው በፅላቱ ስር እግሮቻቸው በፓትሪያርኩ ስር ሆነው ወድቀው መንጋለላቸውን ያዩ መሆኑን እኚሁ ባህታዊ ገልፀዋል።

እንዲሁም ይህን ጥያቄ በአሁኑ ጊዜ ለማቅረብ ለምን አስፈለገ ተብሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ባህታዊው ሲመልሱ በመጀመሪያ ጥያቄአችንን በሰላማዊ መንገድ በተለያዩ ወቅት ለፓትሪያርኩ አቅርበን ነበር ነገር ግን በጥያቄው ምክንያት ባህታውያን ቤተክርስቲያን እንዳንገባ እንዳንሳለምም ታግደናል። ፓትሪያርኩ ጽ/ቤትም ስንሄድ እያባረሩ ይደበድቡናል። ስለዚህ ጥያቄ ለማቅረብና መስተካከል ያለበትን ለመጠቆም አማራጩ ፓትሪያርኩ የሚገኙበትን ክብረ በዓል መጠቀም ብቻ ስለነበረ ነው ሲሉ መልሰዋል። በመጨረሻ ላይ ምዕመናን እንዳይንቀሳቀሱ ተደርጎ አባ ጳውሎስ ("ፓትርያርኩ") በጸጥታ አስከባሪ ፖሊሶች ታጅበው ከቤተክርስትያኑ መውጣታቸው ተስተውሏል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም በቅርቡ በአሜሪካና አውሮፓ ጉብኝት አድርገው የተመለሱት ባህታዊ ገብረ መስቀል በፖሊስ ተይዘው በእስር ላይ ያሉ መሆናቸውን ዘግይቶ የደረሰን ዜና ገልጿል። ባህታዊ ገብረ መስቀል በእስር ቤት እያሉ መታመማቸውንና አለመፈታታቸውን አንድ የኢትዮጵያ ጋዜጣ ዘግቧል።

### 16 የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች በሮም የፖለቲካ ጥገኝነት ጠየቁ

ሞሮኮ በሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ለመሰለፍ ወደ ሞሮኮ በመሄድ ላይ የነበሩት 16 የኢትዮጵያ ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን ተጫዋቾች ጃንዋሪ 22/1997 ትራንዚት ለማድረግ ባደሩበት ጣልያን አገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጠየቁ።

"አገሪቷ ውስጥ እየደረሰ ባለው የጎሣ፤ የፖለቲካና የሃይማኖት ችግሮች ሳቢያ የምንወደውን አገራችንን ለቀን ለመውጣት ቀደም ሲል የአሰብነው ነገር ነው፡፤" በማለት የፖለቲካ ጥገኝነት ከጠየቁት ተጫዋቾች መሐል መሐመድ ተማም ለሮም ፖሊሶች መግለጹን አሶሺየትድ ፕሬስ የተሰኘው የዜና ምንጭ

## አፄ አምሐ ሥላሴ አረፉ

አፄ አምሐ ሥላሰ ዓርብ 17/1997 በተወለዱ በ81 ዓመታቸው ለረዥም ጊዜ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በ81 ዓመታቸው ማረፋቸውን ለማወቅ ተችሏል። አፄ አምሐ ሥላሴ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የቀ.ኃ.ሥ. የመጀመሪያ ልጅና አልጋወራሽ በቅርቡም በስደት ባሉበት በውጭ አገር ንጉሠ ነገሥት መባላቸው የሚታወቅ ነው።

አስከሬናቸውም ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ የቀብር ሥነሥርዓቱ ብዙ ሕዝብ በተገኘበት በደመቀ ሁኔታ መደረጉን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና ይጠቁማል።



አፄ አምሐ ሥላሴ ከልዕልት መድፈርያሽ ወርቅና ከልጃቸው ጋር

ገልጿል። የእግር ኳስ ተጫዋቾቹ በአሁኑ ወቅት ጥገኝነት በጠየቀበት በሮም ከተማ ጥያቄአቸው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በእስር ላይ እንዳሉ ይነገራል። በሮም የኢትዮጵያ ኤምባሲ አማካሪ የተባሉ አቶ በቀለ በንገሣ "በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነት ያለ ስለሆነ ተጫዋቾቹ ለምን ጥገኝነት እንደጠየቁ ይገርማል" በማለት ለጋዜጠኞች መናገራቸው ተገልጿል።

እግር ኳስ ተጫዋቾች ትራንዚት ለማድረግ ኦስቲያ ከምትባል የጣልያን ከተማ (የሮም ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ የሚገኝበት) ለአዳር ከተዘጋጀላቸው ሆቴል ከገቡ በኋላ በለሊት ተነስተው የእግር ጉዞ ካደረጉ በኋላ ሮም ከተማ ገብተው የፖለቲካ ጥገኝነት የጠየቁ መሆኑ ሲታወቅ በሆቴሉ የቀሩትና የጥገኝነት ጥያቄ ያላቀረቡ 2 ተጫዋቾች፣ 1 አሰልጣኝና ሌሎች 4 ሠራተኞች ብቻ መሆናቸው ሲታወቅ እነሱም በሚቀጥለው አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ የተላኩ መሆናቸው ተገልጿል።

## ሱዳን በኢትዮጵያ ላይ የክተት ዘመቻ አወጀች

### የካርቱም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትምህርት አቋርጠው ዘመቻ ገቡ ተባለ

በአልበሽር አስተዳደር ላይ የተነሳውና በደቡብ ሱዳን የሚንቀሳቀሰው የሱዳን የተቃዋሚ ኃይሎች ግንባር በጆን ጋራንግ አስተባባሪነት ጥር 4 ቀን በከፈተው ዘመቻ ኩርሙክ ኬይዘንና ሌሎች ሶስት ከተሞችን በሁለት ቀናት ውስጥ በመያዝ የመንግሥት ጦር ይዟቸው የነበሩትን ቁልፍ ቦታዎች በማስለቀቅ በአሁኑ ጊዜ ግስጋሴውን ወደፊት በመቀጠሉ የአልበሽር መንግሥት የክተት ጥሪ ለሕዝቡ በማወጅ ወጣቱ በየቦታው እንዲመዘገብ በማድረግ ላይ ነው።

አልበሽር ለጥቃቱ ተጠያቂ ያደረገው ኢትዮጵያን ሲሆን ዘመቻውም በኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠረ ነው ብሏል። ጥር 4 ቀን አልበሽር ለህዝባቸው ባሰሙት ንግግር ከእንግዲህ መፍትሔው ጠመንጃ ብቻ ነው ብለዋል።

የሱዳን ሬዲዮና ቴሌቪዥን ቀስቃሽ የሆኑ ንግግሮችን ሲያሰሙ፣ ጥር 7 ቀን የካርቱም ቴሌቪዥን ሕዝቡ ሠላማዊ ሰልፍ ሲያካሂድና በቁጣ ዛሬውኑ አዝምቱኝ ሲል ያሳየ መሆኑንና የዘመቻውን ኃይል ለማጠናከር ሲባልም የካርቱም ዩኒቨርስቲ ተዘግቶ ተማሪዎቹ ወደ ዘመቻ መሄዳቸውም ፎክስ የተባለው የዜና ድርጅት አስታውቋል።

## በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳደር ኤርትራ ውስጥ ቤት ለመከራየት 10 ሺህ ብር ለደላላ ከፈሉ ተባለ።

በኤርትራ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆኑት አውዓለም ወልዱ ለደላላ 10 ሺህ ብር ከፍለው በወር 20 ሺህ ሂሳብ ቤት መከራየታቸውን «አማራጭ» የተሰኘው የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ልሣን አጋለጠ።

አማራጭ በየሁለት ሣምንት አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ሲሆን ታህሣሥ 7 ቀን በወጣው የመጀመሪያው እትሙ በድለላ ስለተገኘው የአምባሳደሩ መኖሪያ ቤት ሲዘግብ በአሥመራ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አማካሪ አክሊሉ ገ/ሚካኤል ለውጭ ጉዳይ በጻፉት ፕሮቶኮል በያዘ ደብዳቤና አባሪ አድርገው ባቀረቡት የሁለት ዓመት የኪራይ ውል 490 ሺህ ብር በአስቸኳይ እንዲላክላቸው የጠየቁበትን በማስረጃነት አስፍሮአል። የምክር ቤቱ ልሣን በሌላ በኩል በኢትዮጵያ የኤርትራ ኤምባሲ የያዛቸው 3 ትላልቅ ቪላዎችና 5 ከፍተኛ አፓርታማዎች፣ አንድ መለስተኛ 18 መኖሪያዎች ያሉት አፓርትማ የኪራይ ተመን ያልተሰጣቸውና ኪራይ የማይከፍልባቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ውል እንኳ የሌላቸው መሆኑ እየታወቀ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከፍተኛ ኪራይ እንዲከፍል መጠየቁ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ እየጐዱ

ኤርትራን ለመጥቀም የሚካሄደው ደባ አንዱን ፈርጅ ያሳያል ብሎአል።

## ስለ አቶ ታምራት ላይኔ የተወካዮች ምክር ቤት ውይይት አያስፈልገውም ተባለ

የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ዳዊት ዮሐንስ ባለፈው የተከበረውን የሕገ መንግሥት አፅዳቂ ጉባኤ ሁለተኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል ምክንያት በማድረግ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ አቶ ታምራት ላይኔ ምግባረ ብልሹነታቸውን ስላመኑ ዝርዝሩን ለመመርመርም ሆነ የመረጣቸውን ሕዝብ ለመጠየቅ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም ሲሉ ያስታወቁ ሲሆን፣ አቶ ታምራት የምክር ቤት ወንበራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ ስለሆነ የለቀቁበትን ዝርዝር ሁኔታ መጠየቅ አስፈላጊ አለመሆኑን፣ አንድ የምክር ቤት አባል የወከለውን ሕዝብ በፈቃደኝነት እንደሚያገለግለው ሁሉ ላለማገልገል ሲወስን የመረጠው ሕዝብ እስኪያውቀው ተብሎ በአባልነት ቆይ ሊባል እንደማይቻል ተናግረዋል። ከዚህም በተጨማሪ አቶ ታምራት የተወካዮች ምክር ቤት አባል ባለመሆናቸው ምክር ቤቱ ጥበቃ ስለማያደርግላቸው በግለሰብ ደረጃ ተከሰው በወንጀል ሊጠየቁ እንደሚችሉ የጠቆሙ ሲሆን ምክር ቤቱም በምትካቸው ሌላ መምረጥ መብቱ መሆኑንም አፈ ጉባኤው ተናግረዋል። በሌላም በኩል ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በቅርቡ ለሮይተርስ በሰጡት መግለጫ አቶ ታምራት ላይኔ ለፍርድ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ገልፀዋል።

## የጦቢያ ጋዜጠኞች አሁንም እየታሰሩ ነው።

በቅርቡ ሶስቱ የጦቢያ ጋዜጣና መጽሔት ዋናና ምክትል አዘጋጆች ከታሰሩ በኋላ የተተኩት አራተኛው አዘጋጅ አቶ አረጋ ወልደቂርቆስ ታህሣሥ 28 ቀን ታስረዋል።

ከዚህ በፊት የታሰሩት የሶስቱ ማለትም የአቶ ጉሹ ሞገስ፣ አቶ ታዬ በላቸውና አቶ አንተነህ መርዕድ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዳይታይ ዳኞች አልተሟሉም በሚል ሰበብ ከአንድ ወር በላይ ከሕግ ውጪ በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ የሚገኙ መሆናቸው ሲታወቅ እንደሌሎቹ ሁሉ አቶ አረጋም የታሰሩበት ምክንያት ያልተገለፀ መሆኑ ታውቋል። አሳታሚ ድርጅቱ የደረሰበትን በደል ከዚህ በፊት ለተወካዮች ምክር ቤት፣ ለፍትህ ሚኒስቴር፣ ለጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ አግባብ ላላቸው የመንግሥት ባለስልጣኖችና ለውጭ አገር አምባሳደሮች አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የተገኘ ተጨባጭ ውጤት ባለማግኘቱ በድጋሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመላው ዓለም ለማሳወቅ ከጥር 8 ቀን 1989 ጀምሮ የታሰሩ አዘጋጆች እስኪፈቱ ድረስ በተቃውሞ መልክ ሣምንታዊውን የጦቢያ ጋዜጣ ህትመት እንደሚያቆም ታውቆአል።

## የአሜሪካ ወታደራዊ ቡድን ኢትዮጵያን ጎበኘ

6 አባላትን ያቀፈ አንድ ከፍተኛ የአሜሪካ ወታደራዊ ቡድን ባለፈው ሣምንት አዲስ አበባ መግባቱን በኢትዮጵያ የአሜሪካው አምባሳደር ሚስተር ዴቪድ ሺን አስታወቁ።

ይህ የአሜሪካ ወታደራዊ ቡድን በአፍሪካ ስለሚቋቋመው ወታደራዊ ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር ዓላማ ከኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አመራር ሰጪዎች ጋር በመወያየት መግባባት ላይ መድረሱንም ተናግረዋል። ኢትዮጵያ አሜሪካ እንዲቋቋም ለምትፈልገው ለዚህ ጦር ሁለት ባታሊዮን እንደምታዋጣ አስቀድማ ያስታወቀች ሲሆን ዩጋንዳ፣ ማሊና ቱኒዝያም ቃል ሲገቡ ብዙዎች የአፍሪካ አገሮች ግን የዚህን ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር መመስረት አዝማማያ ጤናማነቱ አይታያቸውም።

## የአውሮፕላኑ ጠላፊዎች ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የፌዴራሉ ፖሊስ ቢሮ አስታወቀ።

ባለፈው ህዳር ወር ወድቆ በተከሰከሰውና ለ125 ሰዎች ሞት ምክንያት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን የጠለፉት ሶስቱም ኢትዮጵያውያኖች መሆናቸውንና ሶስቱም በአደጋው መሞታቸውን የፌዴራሉ ፖሊስ ኮሚሽን አስታወቀ።

የሶስቱ ጠላፊዎች ስም ማትያስ ሰለሞን በላይ፣ አለማየሁ በቀለ በላይና ሱልጣን ኑር ሁሴን መሆኑንና ጠላፊዎቹ ምንም ዓይነት የፖለቲካ አቋም ያልነበራቸውና በፖሊስም ሆነ በሌላ አካል የተመዘገበ የወንጀል ሪኮርድ እንደሌላቸው የታወቀ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የጠላፊዎቹ ቤተሰቦች ለምርመራ በእስር ላይ እንደሚገኙም ተነግሮአል። ቀደም ሲል በኮሞሮስ መንግስት የታሰሩት ሁለት የጅቡቲና የኬንያ ዜጎች የሆኑ ተጠርጣሪ ጠላፊዎችን የኮሞሮስ መንግስት እስካሁን አለመልቀቁና የጠለፋው ድራማ ዝርዝር ገጽታው ይፋ ባለመሆኑ አያሌ አጠራጣሪና አከራካሪ ሐሳቦች እየተሰነዘሩ ናቸው።

## በአትላንታ ከተማ ታዋቂ ራጯ የሆነው አረጋ አብርሃ ሰው በመግደል ወንጀል ታሰረ

በፕሮፌሽናል ራጯነት በአትላንታ የሚታወቀው አረጋ አብርሃ ባለፈው January /1997 የአክስቱ ልጅ የሆነችውን ወጣት አስቴር ኃይሌን ገድሏል ተብሎ በእስር ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል። እንደ ሪፖርተሮች አገላለጽ አረጋ የአክስቱን ልጅ ሊገድል የቻለው ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው ተብሏል። የሟቿ አስከሬን አትላንታ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አስተባባሪነት በተደረገ መዋጮ ወደ ኢትዮጵያ የተላከ መሆኑ ታውቋል።

# አልሰሙ እንደሆነ !

**ያልሰሙት ዜና ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ትንሽ ዘግየት ያሉ ዜናዎችን አሳጥረን የምናቀርብበት አምድ፣**

★ ቢሮው አሜሪካ የሆነው የጋዜጠኞች መብት ጠባቂ ኮሚቴ (ሲፒጄ) በኢትዮጵያ ውስጥ በእስር የሚንገላቱት ጋዜጠኞች በአስቸኳይ ይፈቱ ዘንድ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በድጋሚ በደብዳቤ ማቅረቡንና የዚህን ደብዳቤ ግልባጭ 40 ለሚሆኑ በኢትዮጵያና በውጭ አገር ለሚገኙ ለተለያዩ ድርጅቶችና የመንግሥት መልእክተኞች መላኩን አስታውቋል። (ጥር /1989)

★ ከአሥመራ ወደ ምፅዋ በሚወስደው መንገድ ላይ 5 የቤልጅግ ዜጐች የሆኑ ቱሪስቶች እና 1 ኤርትራዊ ሹፌር ምንነታቸው ባልታወቁ ሽማቂዎች አንገታቸው በስለት ታርደው ተገኙ።

★ የሻዕቢያ ንብረት የሆነው የቀይ ባህር የንግድ ኮርፖሬሽን ኃላፊ አቶ ብርሃነ ኃይለ ባለፈው ሳምንት ራሳቸውን ገደሉ። በዚሁ ኮርፖሬሽን ላይ ተፈፀመ በተባለው ንቅዘት ሳቢያ 40 የሚሆኑ ኤርትራውያን ነጋዴዎች ከአዲስ አበባ ተይዘው አሥመራ ተወስደዋል። (ታህሳስ/1989)

★ የኢህአዴግ ሠራዊት በከባድ መሣሪያዎችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች በታገዘ ጦር ወደ ሶማሊያ ግዛት ዘልቆ በመግባት ከኢል-አትሀድ አል-ኢስላሚያ ከተባለው ቡድን ጋር ጦርነት ገጠመ። (ታህሳስ/1989)

★ የሱዳን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ዶክተር መሐመድ አልቱራቢ በኤርትራ በኩል የተቀሰቀሰባትን ጦርነት ለመመከት ከጦሩ ጐን የሚሰለፍ ሕዝባዊ ሠራዊት እንዲከት ጥሪ አቅርበዋል። (ጥር/1989)

★ ታዋቂው አትሌት መሐመድ ከድር ስፔን በተደረገው የታዳጊ ወጣቶች የቼዝ ሻምፒዮና ላይ ተሳታፊ የነበረውን የኢትዮጵያ ቡድን ለመምራት በሄደበት አጋጣሚ ሆላንድ ውስጥ ጥገኝነት መጠየቁ ታውቋል። መሐመድ ከዚህ በፊት በ1995 እንግሊዝ አገር በተደረገው የሩጫ ውድድር በአሰልጣኝነት ተመድቦ በተጓዘበት ጊዜ ከእሱ ጋር የነበሩ 4 አትሌቶች በመጥፋታቸው ወደ ሀገሩ ሲመለስ ክስ ተመስርቶበት በዋስ እንደተለቀቀ የሚታወቅ ነው። (ታህሳስ/1989)

★ ወያኔ የቀበሌ አፋኞችን በአዲስ መልክ እያደራጀ መሆኑ ይነገራል። የአፋኞቹ ዋና ግዴታቸው የቀድሞ የኢሕአፓ አባላትን፣ አመራርና በአጠቃላይ በኢሕአፓነት ታስረው የነበሩትን ስም እንዲያቀርቡ ነው። ከታምራት ላይኔ ከስልጣን መወገድ ጋር በተያያዘ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት በነበሩ በፎረም 84 እና በኢሕአዴን (ብአዴን) አባላት የሚጠራ ዘመቻ ለማካሄድ እቅድ ጋር በኅብረት ለመፍጠር ንግግር ጀምረዋል።

★ ከ300 በላይ የሚሆኑ የመቀሌ የዲፕሎም የንግድ ሥራ ተማሪዎች ሊመረቁ አንድ ዓመት ሲቀራቸው ሁሉም ከ3.4 በላይ አጠቃላይ ውጤት ይዘው አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ገብተዋል። እንዲሁም 260 የሚሆኑ የመቀሌ መምህራን ማሰልጠኛ ምሩቃን የመጨረሻ ዓመታቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ እንዲጨርሱ ተልከዋል። የዚህ ጉዞ ዋና ዓላማ የተማረ የሰው ጉልበት ያንሳቸዋል የተባሉትን ክልሎች ቢሮክራሲ በእነዚህ ምሩቃን ለመያዝ ነው ተብሏል።

★ ስለ ብሔር ተዋጽኦ ወያኔ በቅርቡ ባዘጋጀው 80 ገጽ የጥናት ጽሁፍ ቢሮክራሲው 70 ፐርሰንት ያህል በአማራ የተያዘ ስለሆነ መመንጠር አለበት ይላል።

★ በቅርቡ በሥራ ላይ የሚውለው የወያኔ ትምህርት ፖሊሲ 11ኛ ክፍል በወር 6 ብር፣ 12ኛ ክፍል በወር 8 ብር፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ደግሞ ለ4 ዓመት የትምህርት ጊዜ በብድር 24,000 ብር እንዲከፍል ወስኗል።

# እንወያይበት !

## «መከራ ሲመጣ አዋጅ አያስነግርም!»

ሰብለወንጌል – ከሆላንድ

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ውስጥ እየታየ የመጣው ወደ ኋላ የመሄድ ፈጣን «ዕድገት» የነገይቱ ኢትዮጵያን ህልውና አጠያያቂ እንዳደረገው የአደባባይ ሚስጢር ነው። የአገር ህልውና ሲያሳስበን አብሮ የሚታየን ደግሞ ይህች ድኃና ምስኪን እናት አገር ያቀፈቻቸው አብረዋት የመከራዋና አበሳዋ ገፈት ቀማሾች፣ የወቅቱ የኢህአዴግ የጥፋት ዒላማ የሆኑት ወገኖቻችን ትውስ ይሉናል። ባሕር ማዶ ያለን ወገኖች በሥጋ ብንለያቸውም እንኳ በመንፈስ ግን ስቃያቸው ሁሌ የመንፈስ ዕረፍት ነስቶን አብረናቸው እንዳለን ይገባኛል። ካገር ተለይቶ ስለአገር ሲታሰብ ናፍቆቱ ያንገበግባል፣ ሁሌ አገር ነክ ወሬ ይናፍቃል። በተለይ ትግራይ ታሽቶና ተፈጭቶ ኤርትራ ተቦክቶ 4 ኪሎ በዘመኑ ዕዳዎች ይሁንታ አግኝቶ በአገርና ሕዝብ ህልውና ላይ ተጋግሮ እየበሰለ ያለው የጥፋት «እንባሻ» ሲታሰብ እንዴት አእምሮ ይረፍ? ሁሌ ወገንና አገርን አስበን እህህ! ማለቱ፤ ነገስ ምን ይሆን የሚፈጠረው በማለት ከበር ፍለጋ በቅርብ ካሉት ጓደኞች ጋር በቀጭኑ ሽቦ «ሀሎ» መባባሉ የግድ ነው። አገር ሲታመስ እንዴት ያስችላል? ታዲያ አንድ ቀን ጥዋት አንዱ የቅርብ ጓደኛዬ የተለያዩ ዜና ያካተተ ቡለቲን ደርሶኛልና ጊዜ ካለሽ ብቅ ብለሽ ጥለፊው «ለመደበሪያ» አይከፋም ሲለኝ፣ «መደበሪያ» ያለው ጓደኛዬ በቡለቲኑ ይዘት አለመርካቱን በተዘዋዋሪ መንገድ ጠቆም ቢያደርገኝም እኔ ግን ጊዜ ሳላጠፋ ቤቱ ከች ብዬ የተባሉትን ቡለቲኖች እጄ ውስጥ አስገባሁ። ነገሩ በውጭ ለሚኖሩ «የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባላት» የአገራችንን የወቅቱን ሁኔታ እንዲከታተሉ ተብሎ በመንግስት ሥር ከሚፈበረኩ የተለያዩ ጋዜጦች ኮፒ እየተደረጉ አልፎ አልፎ የሚታደላቸው አደንቋሪ የመንግሥት ተብየው ኢሕአዴግ ቅዠት የተሞላቸው ቡለቲኖች ናቸው። የዜናው ሀተታ ምንጭ ኢ.ዜ.አ.ና ዋኢማ (ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል) ናቸው። መጀመሪያ ለንባብ ያስቀደምኩት የሳምንቱ ዐበይት ዜናዎች የሚል ርዕስ ያዘለውን «የዋኢማ» ዜና ነበር። ታዲያ «ዋልታ» ማን ነው ብላችሁ አትጠይቁኝ፤ የማውቀው የለኝም። አንድ ነገር ግን አውቃለሁ፤ ይኸውም ዋልታ ቃሉ ትግርኛ ሲሆን ትርጉሙም ጋሻ፣ መከታ፣ አለኝታ መሆኑን ነው።

ወደተነሣሁበት ነጥብ ልመለስ፤ «ዋልታ» ያተተው የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የሶማሌ፣ የደቡብ፣ የትግራይ ...ወዘተ ልማት ነክ ክንውኖችን ነው። ነገሩ ሕልም ባይሆን ኖሮ ቢነበብም አይጠገብም ነበር። ሕልም በመንገር ሕዝብን በተስፋ ዳቦ ማጥገብ፣ በገሀዱ ዓለም ደግሞ ሁሉንም ወደ ትግራይ ማጋዝ ሆነ እንጂ። የእከሌ ክልል በዚህ ያህል ሚሊዮን ብር ክሊኒክ፣ ት/ቤት፣ ንጹህ ውኃ፣ ምርጥ ዘር፣ ቁጠባ ቤቶች ሠራ፣ አለማ፣ አጥጋቢ የልማት ተግባር አከናወነ ነው ዜናው ሁሉ። ይህ «ፈጣንና አጥጋቢ የልማት ዕድገት» ሲታሰብ ከ4 ኪሎዎቹ አጋንንት ጋር በምኞት ዓለም ውስጥ ሰጥሞ ተመስገን ተብሎ ሊላኛውን ገፅ ገልበጥ ሲደረግ ደግሞ ጉድ ነው ዘንድሮ ያሰኛል። ለአብነት እንዲሆናችሁ ይህን ርዕስ ያገኘሁት በዋኢማ ከተዘገበ ዜና ነው።

1– በ18.8 ሚሊዮን ብር የውኃ ጉድጓዶች እየተቆፈሩ ነው።
ደቡብ– ጥቅምት 26/1989 (ዋኢማ)

2– በሃድያ ማዘጋጃ ቤት ከ11 ሚሊዮን ብር በላይ ባከነ ተባለ።
ደቡብ– ጥቅምት 25/1989 (ዋኢማ)

እንግዲህ ይታያችሁ ክንውኑ ሁሉም በደቡብ የሀገራችን ክፍል ነው። (የቦታ ልዩነት አለ።) ራሳቸው የካቡትን የልማት ክንውን ራሳቸው አፈራረሱት። የዝርፍያውን ነገር ካነሳን ጊዜውና ወረቀቱ አይበቃንምና እንተወው። እንዲያው እናውቃችኋለን ለማለት እንጂ፤ በቅርቡ የተፈጸመውን ታምራት «ብታምራት» አይተናል፤ ጉድ አላልንም ምክንያቱም «መለስ» ብለን ስናስብ ጉዱ ገና ነው። «ከቁራ ጋር የዋለች እርግብ ላባዋ ባይጠቁርም ልቧ ግን መጥቆሩ አይቀርም» ይላሉ አበው። ልማትና ወያኔ የጭድና እሳት ያህል እውቂያ ቢኖራቸውም ባንጻሩ አንድ ስመ ጥሩ ያገሬ ደራሲ እንዳሉት «ሽፍቶች መሪዎች ሲሆኑ ለሁሉም አይመቹምና» ዝርፍያና የ4 ኪሎ ሽፍቶች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸውና የልማቱ ዜናና የተዘረፈው ሀብት ዜና ሚዛን ላይ ቢቀመጥ እርቃናቸውን ያጋለጠ ሳያውቁት ያመለጣቸው ዜና ሆኖ ታየኝ።

«ጉድና ጅራት ...» አይደል! ዜና ክልል «አማራ» የሚለውን ላንዳፍታ ገረፍ አድርጌው ላልፍ ስል ዓይኔ አይቶ ሕሊናዬ መቀበል ያቃተው ዜና አጋጠመኝ። «የሳንባ ነቀርሳ ህሙማን ቁጥር እየጨመረ ነው» ጥቅምት 23/1989 (ዋኢማ) ይላል ርእሱ። አነበብኩት ዜናው ዜና ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን የመርዶ ያህል አንገብጋቢና መንፈስን የሚረብሽ ዘገባ ነበር። ብዕሬን እንዳነሳ የገፋፋኝም ይኸው ጉዳይ ነው። የተዘገበው ዜና መንግሥታዊ ኃላፊነት፣ ወገናዊነት አልያም ሰብዓዊ ርኅራሔ ያዘለ ሳይሆን እንደ ተራ ዜናና የተባለው ሕመም እንደ ቀላል ነገር በተራ ቃላት የተጻፈ ዜና ሆኖ ነው ያገኘሁት። ልብ ብሎ ላነበበው ኢትዮጵያዊ ወገኔ ግን፤ በእነ አቶ መለስ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ምን ያህል እንደተናቀ ቁልጭ አድርጉ ያሳየናል።

የዜናው ይዘት በአጭሩ እንዲህ ይነበባል፤

በደቡብ ወሎ ዞን ባለፉት 2 ዓመታት የሳንባ ነቀርሳ ህሙማን ቁጥር መጨመሩንና ህሙማኑ ሆኑ ህዝቡ ለበሽታው የሚሰጡት ትኩረት ሆነ ጥንቃቄ አናሳ መሆኑን፣ ባለፉት 2 ዓመታት 13 ሺ 118 የሳንባ ነቀርሳ ህሙማን መመዝገባቸውን፣ ባለፉት 3 ወራት ብቻ ደግሞ 952 ህሙማን መመዝገባቸውን ዜናው ያረዳናል። በሽታው እየተስፋፋ መምጣቱንና የጤና ተቋማቱም ተገቢ አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸውን፣ የበሽታው መከላከያ መድኃኒት ከፍተኛ እጥረት እንዳለ፣ ሕብረተሰቡ ደግሞ ቀድሞ በመከላከል ረገድ ሰፋ ያለ ትኩረት እንዲሰጠው ይገባል ያሉት የዞኑ የጤና መምሪያ የፕላንና ፕሮግራም ቡድን መሪ ነበሩ እንደ ዋኢማ ዘገባ።

እንግዲህ ይታያችሁ የሳንባ ነቀርሳን ያህል በሽታ በ2 ዓመት ውስጥ የ13 ሺህ እና ከዛም በላይ የሚሆኑ ወገኖቻችንን ያጠቃና ገና ከሚስፋፋበት ጊዜና ፍጥነት አኳያ ሲታይም የእልፍ አእላፍ ወገኖች ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥልና በዓለማችን አሉ ከሚባሉና የመስፋፋት ባህርዩ አደገኛ የሆነ ቀሳፊ በሽታ መሆኑ እየታወቀ እንደተራ ዜና ማስፈሩና ይባስ ብሎ (የንቀቱ ንቀት) ኃላፊነቱ በዚህ ምንም በማያውቀው ተራና የዋህ ሕዝብ ጫንቃ ላይ መጣሉና፤ ያውም ታማሚው ወገን «ኧግዚኦ» ብሎ ያመጣው ይመስል ተጠያቂ ማድረግ ተገቢ ይሆን? ይህች ባቄላ ካደረች ... አይደል የተባለው።

በሽታው የተስፋፋው (እንደዘገባው) በደቡብ ወሎ ዞን ሲሆን፤ በዚሁ ክልል የምናገኛቸው ወገኖቻችን የኑሮ ሁኔታና አጠቃላይ ሕይወቱን ብንዳስሰው በድኅነት እየማቀቀ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ጉስቋላ ኑሮ ውስጥ የሚገኝ ሕዝብ ነው። ያውም ከእኛ ይበልጥ ወያኔዎች ታውቁታላችሁ። የዛሬን አያድርገውና ያጉረሰ እጁን ብትነክሱትም፤ የበግ ለምድ ለብሳችሁ ስትጠጉት ያለችውን ያካፈለ፣ መንገድ የመራ ያ የትናንቱ ጓዳችሁ መደበቂያችሁ፤ ዛሬ የካዳችሁት ገበሬ ነው። ያ ለመሬት ሽንሽና፣ ለሕገ መንግሥት ለተለያዩ ሥልጣን ነክ ጉዳዮች እናውቅልሃለን የምትሉትን ገበሬ ነው ዛሬ በችግሩ ጊዜ የከዳችሁት። ታዲያ ይህ የበሽታ ሰለባ የሆነ ወገናችን ስለ ሳንባ ነቀርሳ ቀርቶ በየእለቱ ስለሚያጋጥሙት ተራ በሽታዎች እንኳ ቢሆን ግንዛቤ የሌለው ሁሌ ለተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ችግሮች የተጋለጠ ዜጋ ሆኖ ሳለ ለበሽታው የሚሰጠው ትኩረት ደካማ መሆኑንና በሽታውን ለመከላከል እንዳልቻለና ጥረት እንዳላደረገ ... ወዘተ ይነግረናል ዋኢማ። የሰው ያለህ! ብለን ስለምስኪኑ ወገናችን እምናለቅሰው እዚሁ ላይ ነው። የመንግስትነት ስያሜ ይዞ የተኮፈሰው ኢህአዴግ የት ነው ያለው? ሚናው ምንድን ነው? ምንስ ቅድመ ዝግጅት አደረገ? የተወሰደ እርምጃስ አለ ወይ? የጤና ጥበቃ ድርጅትስ ምነው ድምጹን አጠፋ? ለሚሉት ጥያቄዎች ለምን ራሱ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል (ዋኢማ) ይህንኑ ነጥብ አላነሳውም የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳት እንገደዳለን። ያውም እህ ባይና ሰሚ ጆሮ ቢገኝ።

ለአቶ መለስና የጥፋት ደቀመዝሙሮቻቸው ለሆኑ የዘመኑ የኢትዮጵያና የህዝቧ ዕዳዎች እስኪ በዓይነ ኅሊና ወደ ትናንቱ አረመናዊ ተግባሮቻቸውና ያከናወኑባቸው መድረኮች እንመልሳቸው፤ የበደኖ የአርባ ጉጉ፣ የዋተርሉ አሻራ ሳይጠፋ የጉንደሩን አከላችሁበት፤ በዚሁ እህህ ስንል የአንዋሩ መስጊድን አስከተላችሁ። በየገጠሩ ትናንትና ኢትዮጵያዊነትን ተንተርሶ በትዳር ጋብቻ ተሳስሮ ደስታና ሐዘኑን እኩል ተጋርቶ ሠላማዊ ሕይወት ይመራ የነበረው ወገናችን ለሥልጣናችሁ ዕድሜ ማራዘም ሲባል የማያውቀውን የጐሳ ልዩነት ፈጥራችሁ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ ትግሬ፣ ወዘተ እያላችሁ እርስ በእርሱ አናከሳችሁት ይኸው የእልፍ አእላፍ ወገኖች ሕይወት ሲቀጠፍ፤ የዚሁ እጥፍ የሆኑ ወገኖችም ከተወለዱበት ቀዬ ተባርረው ለተለያዩ አደጋዎች ተጋልጠው ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሠላም ሰፍኗል ብላችሁ ብታወሩም ባንጻሩ ግን እንኳን ሰላም ምልክቱም እንደሌለ ልቦናችሁ ያውቀዋል። ኢትዮጵያዊ በከተማውም በገጠሩም የወያኔዎች ጥይት መሞከሪያ ሆኗል፤ ትናንት የታየ ዛሬ ይሰወራል፤ በገዛ አገሩ በጥርጣሬ ተሞልቷል፤ ክብሩንና አገሩን አሳልፋችሁ ለባዕድ በመስጠታችሁ ኢትዮጵያዊ ያገሩ ባዕድ ሆኗል። ለተለያዩ መከራና እበሳ አጋልጣችሁታል። አሁንም የጥፋት ተልዕኳችሁን ረቀቅ ባለ ዘዴ ለመተግበር የሳንባ ነቀርሳን ያህል በሽታ ጥርሱን አግጥጦ በድኃውና ረዳት የለሹ ገበሬ ወገናችን ሕይወት ላይ ሲያንዣብብ እንደተራ የጉንፋን በሽታ በተራ የዜና ዘገባ ታጅቦ የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ ለሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ብላችሁ አቅርባችሁታል። ነገሩማ ምን ወቅታዊ ጉዳይ ሆኖ ወቅታዊ ጥፋት በሉት እንጂ። ዛሬ በከፍተኛ የበሽተኞች አሀዝ የቀረበልን ዘገባ አያድርገውና ነገ እነኚህ ወገኖቻችንን ስናጣቸው፤ የተፈጥሮ አደጋ ይህን ያህል ኢትዮጵያውያንን ቀጠፈ፣ ይህን ያህሉ ደግሞ አስጊ ሁኔታ ላይ ናቸው በሚል የእንካ ሰላንቲያ ጨዋታ ራስን ከተጠያቂነት ለማምለጥ ይሆን?

የ13 ሺ ኢትዮጵያዊ ወገን ሕይወት (የአሀዝ ቁጥር ይበልጥ ከፍ እንደሚል አትጠራጠሩ) ከመቃብር አፋፍ ላይ ሆኖ የወገን ያለህ ብሎ ሲጣራ፣ የአካባቢው የጤና ተቋማት የአገልግሎት ብቃት ካለመኖር ያልተሻለ ሆኖ እያለ፤ መድኃኒትም ፈጽሞ የለም ተብሎ እየተነገረን፣ ችግሩን በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚሰቃየው ወገን ራሱ ይወጣው ብሎ የወገናችን ሕይወት በውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ ትግል ላይ መሆኑን የቀልድ ብሎ የዘገበልን ዜና ጐን ለጐን ደግሞ እንካችሁ ጥሩ ዜና አለኝ ይለናል የኢዜአ (ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት)፦ «በ45 ሚሊዮን ብር ወጪ የመቀሌ ውኃ መስመር ሊሻሻል ነው» (ጥቅምት 22/1989 ኢዜአ)።

እኛም ወገናችን የሆነ የመቀሌ ከተማ ሕዝብ ይቅር የንጹህ ውኃ መስመር፣ የወተት መስመርም ቢዘረጋለት «ኧሰየው» እንላለን። ጥያቄአችን ግን የወቅቱ ዕዳችን ፕሬዚዳንት መለስና ለሆድ ያደሩ አሽከሮቻቸው የሚያካሂዱት መንግስታዊ ተቋማት ሁሉ ወደ ሰሜን ብቻ ለምን አቀና? ሌላው ቀርቶ በሁለት ዓመታት ውስጥ ከ13 ሺህ በላይ ሕዝብ አጠቃ የተባለው ቀሳፊ በሽታ (ያውም በደቡብ ወሎ ብቻ፣ የሌላውን የአገራችንን ክፍል የኢትዮጵያ አምላክ ይታደገው) የሞት ሠይፉን ይዞ እየገሠገሠ መሆኑንና መንግሥት ሚናው ምን እንደሆነ ግልጽ ባልሆነልን ዜና አንጀታችን እያረረ እያለ፣ ጐን ለጐን ከላይ የጠቀስኩት የ45 ሚሊዮን ዜና ተዘግቦልናል። የእንጀራ ልጆች በእንጀራ አባት ሲጠቃ፤ አጋሮችና ወገኖች የተባለላቸው ነገ ጉድ ሲፈላ መደበቂያ ጓዳ ይሆኑ ዘንድ ከአሁኑ አይን ያወጣ ውለታ እየተደረገላቸው ነው። ታዲያ አቶ መለስ የዛሬን እናልፋትና ነገ ሌላ ቀን ናት፤ ያች ቀን ደግሞ ዛሬ የልብ ጓደኛዎ አቶ ታምራት

እንደጨለመባቸው የነገይቱ ቀንም ለእርስዎ ጨለማ ናት። ዛሬ በንዋይ ብዛት ትግራይን አፈራርሰው ያለ ልክ ቢገነቡዋትም፣ የትግራይን ሕዝብ ልብ ግን በጥላቻ መገንባት ከባድ ነው። የደቡብ ወሎ ሕዝብ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ መታመም ለእርስዎና ለአሽከሮችዎ ያስደስት ይሆናል፤ የትግራይ ሕዝብ ግን ጮቤ እንደማይረግጥ እናውቃለን።

በአጠቃላይ ግን በደደቢት የጸደቀው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊን የማጥፋት ሴራ ገሀድ ወጥቷል ብቻ ሳይሆን ብሶበታል። ቻርተሩ ተግባር ላይ እንዲውል ስንትና ስንት ኢትዮጵያዊ ሕይወት ለማጥፋት እንደተሳሉ ባናውቅም የእስከ ዛሬ የጥፋትና ግድያ በትሮቻቸውን ስናስታውስ ግን በስለት መልክ የሚያቀርቡትና የሚያጠፉት የኢትዮጵያዊ ሕይወት ቀላል አይመስለንም። ታዲያ የኢህአዴግ ወያኔን የሞት ዘመቻ ሳስብ ትዝ የሚለኝ በሂትለር ዘመን የተመሠረተውና የብዙ አገር ዜጎችን ሕይወት የበላው የኦሽዊትዝ ግድያ ካምፕ ነው። የወቅቱ መሪ ሂትለር ለካምፑ ኃላፊ «የምንማርከው ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዛቱ እየጨመረ ስለሆነ ሰው የምንገድልበት ዘዴም በዛው ልክ ፈጣን እንዲሆን ...» ብሎ ትዕዛዝ እንደሰጠ ሁሉ አቶ መለስም ኢትዮጵያዊ የሆነን ዜጋ እንዴት ማጥፋት እንደሚችሉ አስበውና ተመራምረው የደረሱበት መፍትሔ በእርስ በርስ ጦርነት፣ በአፈናና ግድያ፣ ረቀቅ ሲልም በበሽታ ይሆን ዘንድ መሰለኝ። ይህም ይሁንታ አግኝቶ እየተተገበረ ነው።

ታዲያ ከወያኔ የጥፋት ፕሮግራም አንዱ በሽታ ነው ያልነው የ13ሺህ የደቡብ ወሎ ሕዝብ በሳንባ ነቀርሳ መሰቃየቱ ብቻ አይደለም። የሌላው ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ፣ ቀበሌ ሕዝብ የጤንነት ጉዳይ ድፍንፍን ማለቱ ነው ያጠራጠረን። ለመሆኑ የደቡቡ ወሎ 13 ሺህ ሕዝብ ብቻ ነው የሳንባ ነቀርሳ እያሰቃየው ያለው? ወያኔዎች እንደደበቁት ጌታ በታምራቱ ይደብቅልን። እውነታው ግን ኢትዮጵያውያን ነንና የወገናችን ስቃይ ይሰማናል፤ እንፈራለን። ፍርሃቱ ደግሞ ይኸው ብዕር ቀስረን ለመጻፍ አነሳሳን። መልዕክቱ የአበሳው ምንጭ ለሆነ ወያኔያዊ ቁሳር አይደለም። መልዕክቱ የአገርና የወገን ፍቅር ታቅፈን በየሰው አገር ለምንገኝ ዜጎች ነው። ኢትዮጵያ አገሬ፣ ኢትዮጵያ ቤቴና መቃብሬ፣ ኢትዮጵያዊነት ክብሬ፣ ጌጤና ማዕረጌ ነው ለሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነው።

ወያኔ የዘራውን የጥፋት ዘር ከሥሩ ነቅለን እናጥፋው። ዛሬ በተለያየ ግን አሳፋሪ በሆነ የጉሳ ፖለቲካ ስንቧቀስ «የገበያ ግርግር ...» ነውና እነ አጅሬ መለስ ጓዳችንን እየበረበሩ ናቸው። ኢትዮጵያዊ ዘር ለማጥፋት ሩጫ ላይ ናቸው። እና በተለያዩ ዓለማት የተለያዩ ፖለቲካዊ ፕሮግራም ነድፋችሁ የእኔ ይበልጣል እንካ ሰላንቲያ ውድድር ትታችሁ ለወቅቱ ጉዳይ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ነገ ልትሆኑት ልትመሩት የምትሹትን ሕዝብ ስቃይና አበሳው ዛሬ ተሰምቷችሁ ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች (WHO-IRC) የመሳሰሉትን በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገቡ የተለያየ ግፊት ብታደርጉ ደግ ነው ባይ ነኝ። በሽታው ቀላል ከሆነ እኛም እፎይ እንበል። ከባድ ከሆነም በሽታው ሳይስፋፋ ቀዳዳው የሚደፈንበትን ሁኔታ እንፈልግ። በተጨማሪም ራሱን በማን አለብኝነት ሥልጣን ላይ ኮፍሶ የመከራ ምርት አፍርቶ በገዛ ወገኖቻችን ሕይወት ላይ እየጋገረ ያለውን «መንግስት» በዚሁ ጉዳይ ላይ አገር አቀፍ መረጃ እንዲሰጥበት ለበሽታውም ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሕዝቡን እንዲታደግ ብታደርጉ እንመርጣለን። ዛሬ ያልደረሳችሁለት ሕዝብ ነገ እንሆንልሃለን ብትሉት ትናንት የት ነበራችሁ ብሎ እንዳይጠይቃችሁ ከወዲሁ አስቡበት።

እንዲሁም ወገን አለኝ፣ አገር አለኝ፣ ኢትዮጵያ ጉዳቷም ሆነ ከፉዋ ይሰማኛል የምትል ዜጋ ዛሬ እየተሰቃየች ያለችውን የወገን ጉስቁላ ሕይወት ለነገ እናሳድራት። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ዕዳችን በሽታ ብቻ አይደለም። ብዙ መከራና ስቃይ ከሁሉም ይበልጥ ነፃነት የማጣትና አገር የመበታተን ፈተናዎች ተጋርጠውብናል። መሰናክሉን እንዳንበጣጥሰው እኛው ራሳችን አልመች ብለናል። አንድ ደም ግን የተከፋፈለ ልብ ይዘን እንጓዛለን። ኢትዮጵያዊ ነኝ ብለን ዝም እንደማለት ፋንታ ቀዬና ወንዝ እናስከትላለን። ከዘመነኞች ወገን ከሆንን ደግሞ እንደ አውቶብስ አገር ትተን ክልል በቁጥር ሰይመን ከዚህ ክልል ነኝ ማለቱ ይቀናናል። ውርደቱንና አገር የመፈራረሷን ሁኔታ በፀጋ የተቀበልን እንመስላለን። አገር ቤት ያለው ወገናችንማ አበሳው ከመቼውም ይልቅ በዝቶበታል። እስራት፣ ግርፋት፣ አፈና ግድያ፣ ከሥራ መባረር፣ ጡረታ ከፍያ መታገድ ... የየዕለቱ ገጠመኞቹ ናቸው። ባሕር ማዶ ያለነውም የወገናችን ሕመም ተሰምቶን አገርና ወገን ለማዳን ኢትዮጵያዊ ግንባር ፈጥረን ሰላማዊ ትግሉ ላይ በይበልጥ እንሳተፍ። የወገን ያለህ ለሚለው ድሃው ዜጋችን ከየጉራው ተጠራርተን እንድረስለት።

ሰብለወንጌል ከሆላንድ





በኮምፒውተር
የአማርኛና የእንግሊዝኛ ሥራዎች
በተቀላጠፈ ሁኔታ

መጽሐፍት፤ መጽሔቶች ወይም የተለያዩ
የአማርኛ ጽሑፎችን በኮምፒውተር
ለማሠራት የምትፈልጉ በስልክ ቁጥር
(404) 508—4657 ገነትን ደውለው
ያነጋግሩ!!




## EthiO Systems

PO Box 36921
Houston, TX 77236
**(713)995-4360**
ethiosys@neosoft.com
http://www.neosoft.com/~ethiosys/ethiosys.html

ዋሸራ 2.0
በነዚህ መደብሮች ይገኛል

| | |
|---|---|
| **Maru Grocery**<br>Houston, TX (713)665-6608<br>Dallas, TX (214)373-6278 | **Ethio Sound**<br>Washington, DC (202)232-0076 |
| **Addisu Gebeya**<br>Washington, DC (202)986-6013 | **Queen of Sheeba**<br>Falls Church, VA (703)998-0180 |

**በኢትዮጵያ ቋንቋና ፊደል**

መፅሔት፣ መፅሀፍና ልዩ ልዩ ሰነዶችን፤
ስፕረድሽቶች፤
ዴታቤዝ፤
ንግግር ማቅረቢያ ዝግጅት፤
ኤሌክትሮኒክ መልክት፤
ዌብ ገፅ፤
ልዩ ልዩ ስዕላዊ ፊደላትና የመሳሰሉትን
ከታወቁ ሶፍትዌሮች ጋር ለማዘጋጀት
የሚያስችል ሲስተም።

**Supported Software**

Word Processing: MS Word, WordPerfect, WordPro, AmiPro,

Spreadsheets: Lotus 1-2-3, MS Excel, Quattro Pro,

Database: MS Access, Lotus Approach,

Publishing: PageMaker, QuarkXPress, Corel Ventura,

Illustration: CorelDRAW, Adobe Photoshop, Photoworks,

Internet: Eudora, Internet Explorer, Netscape Navigator,

Windows 3.1x and Windows 95 resident programs

# ማሩ ግሮሰሪ Maru Grocery

**ቅመማ ቅመሞች፣ ጥራ ጥሬዎች፣ የጤፍ ዱቄት፣ እንዲሁም እንጀራ፣...**

** በUPS (United Parcel Service) ለመላክ ዝግጁ ነን።**

| | |
|---|---|
| የገብስ ዱቄት | 1.29/lb |
| ሱፍ | 2.99/lb |
| ጤፍ | 1.89/lb |
| ተልባ | 1.99/lb |
| ቅንጬ | 0.99/lb |
| አተር ክክ | 0.99/lb |
| ሽምብራ ክክ | 0.99/lb |
| ምስር ክክ | 0.99/lb |
| ሽንብራ | 0.99/lb |
| አብሽ ድፍን | 2.99/lb |
| አብሽ የተፈጨ | 5.99/lb |
| የገንፎ ዱቄት | 4.99/lb |
| እጥሚት | 4.99/lb |
| እልበት | 4.99/lb |
| ጌሾ ለጠጅ | 7.99/lb |
| ጌሾ ለጠላ | 7.99/lb |
| ጌሾ ደቃቅ ለጠላ | 6.99/lb |
| እሻሮ የገብስ | 1.99/lb |

| | |
|---|---|
| የሀረር ቡና ጥሬ | 5.49/lb |
| የሲዳሞ ቡና ጥሬ | 5.49/lb |
| ቡላ | 9.99/lb |
| ብቅል | 1.99/lb |
| የባቄላ ዱቄት | 4.99/lb |
| ባቄላ | 0.99/lb |
| የሽምብራ ዱቄት | 2.99/lb |
| በሶ | 4.99/lb |
| ጦስኝ | 1.75/OZ |
| ሰናፍጭ | 1.75/OZ |
| ሰልጆ | 4.99/lb |
| ቅሩንፉድ | 0.69/OZ |
| ዝንጅብል የተፈጨ | 0.50/OZ |
| ነጭ ሽንኩርት የተፈጨ | 0.50/OZ |
| በርበሬ | 6.49/lb |
| ሚጥሚጣ | 7.99/lb |
| ያዋዜ በርበሬ | 6.29/lb |
| ምጥን ሽሮ | 4.99/lb |

| | |
|---|---|
| የቂቤ ማንጠሪያ | 1.00/OZ |
| መከለሻ | 1.00/OZ |
| ኮረሪማ ድፍን | 1.50/OZ |
| በሶብላ | 1.75/OZ |
| ኮሰረት | 1.75/OZ |
| እርድ | 1.29/OZ |
| ኮረሪማ የተፈጨ | 1.75/OZ |
| ጤና አዳም ፍሬ | 1.75/OZ |
| ጥቁር አዝሙድ | 0.89/OZ |
| የሻሂ ቅመም | 1.29/OZ |
| ጥቁር ቅመም | 1.75/OZ |
| ነጭ ቅመም | 1.75/OZ |
| ቀረፋ | 0.99/OZ |
| ነጭ አዝሙድ | 0.79/OZ |
| እንጀራ (15pc/pk) | 5.00/pk |
| ጤፍ 25 ፓውንድ | 37.25/bag |

**8353 Park Ln Dallas, TX 75231**
**(214)373-6278**
**6065 Bissonnet, Houston, TX 77081**
**(713)665-6662 (713)665-6608**

# ከትዝታና ከታሪክ ማህደር

## ሀ) እሰየው! ዩኒሴፍ (UNICEF) 50ኛ የልደት በዓሉን አከበረ።

ያ አንዳንዶቻችን ታዳጊ ወጣት ሆነን ሳለ በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚታደለንን የቫይታሚን ኪኒንና የዱቄት ወተት ታስታውሳላችሁ? በሰልፍ ከትባት ስንከተብስ ትዝ ይላችኋል? ወይ ግሩም! ያ የየዋህነትና የሰላም ጊዜ ማለፉ ያስገርማል ትምህርት ከመጀመራችን በፊት የምንዘምራቸው «ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ» (የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር - National anthem) እና ሌሎች መዝሙሮች ትዝ ይላችኋል። የግርማዊነታቸው ፎቶ ግራፍ ያለበት ደብተርና እንዲሁም እርሳስ እንኳ ሳይቀር ሲታደለን የነበረውን የሕፃናት ደስታ ረስታችሁት ይሆን? በመጨረሻም «አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ... አሜንን» ፀልየን ነበር ትምህርት የምንጀምረው። አብዛኛዎቻችን ጫማ እንኳ አልነበረንም። አይ ጊዜ ሲነጉድ! በጧፍና በኩራዝ እያጠናን በጥናታችን የዋዛ አልነበርንም። የ8ኛ ክፍል ተማሪ ሆነን በዓለምና በሀገራችን ታሪክ የሚደርስብን አልነበረም። ዛሬ የምናየውን የአሜሪካ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እጥፍ ድርብ ጊዜ እናስከነዳው ነበር።

አብዛኛው ለሦስተኛ ዓለም ለሕፃናት የተዋቀረው ተራድዖ ግቡን ሊመታ የቻለው በዩኒሴፍ ጥረት ነው። በእንግሊዝኛ UNICEF የሚለው አሕፅሮተ ቃል ሲተነተን United Nations International Children's Emergency Fund ይባላል። የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮምሲዮን (UNHCR - United Nations Higher Commisioner for Refugees) እና ዩኒሴፍ ለዓለም ድሀ ሕዝቦች ይህ ነው የማይባል ዕርዳታን አበርክተዋል። ከጥቂት ዓመታት በፊት የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮምሲዮን (UNHCR) የኖቤል ሽልማት አግኝቷል። በእርግጥም ይገባዋል።

ዩኒሴፍ በዲሴምበር 11፣ 1946 (እንደአውሮጳውያን አቆጣጠር) በተባበሩት መንግሥታት አጠቃላይ ጉባዔ ተመሠረተ። የመጀመሪያ ዓላማው በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ለተጐዱት የቻይናና የአውሮጳ ሕፃናት ዕርዳታ ማድረግ ነበር። ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የአሜሪካ የዩኒሴፍ ኮሚቴ ተቋቋመ። ዩኒሴፍም ዓላማውን በማስፋፋት የታዳጊ ሀገሮች ሕፃናትን መርዳት ጀመረ። ንጉሣችን ግርማዊ ጃንሆይም ለዩኒሴፍ ይህ ነው የማይባል ዓለምአቀፋዊና ሀገራዊ ድጋፍ በመስጠት መርሐ ግብሩ በሀገራችን ግቡን እንዲመታ አድርገዋል። ከዩኒሴፍ አበይት ዓላማዎች ውስጥ ትምህርት ለሕፃናት መስጠት፣ ለሕፃናት መብት ጥብቅና መቆምና እንደዚሁም ለሕፃናት ጥቅም ይውል ዘንድ የገንዘብ ምንጭ በመፈለግ ለዕድገታቸው መታገል ናቸው።

በተለይም በስደት ላይ ያለን ኢትዮጵያውያን እንደነዚህ ዓይነቶችን ረጂ ድርጅቶች ማለትም እንደ UNHCR፣ የዓለም አቀፍ የስደተኞች መብት ተሟጋች ድርጅት (Amnesty International)፣ የዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት (WHO)፣ የዓለም አቀፍ የባሕል፣ የሳይንስና የትምህርት ድርጅት (UNESCO) ሌሎችንም ረጂ ድርጅቶች መደገፍ አለብን። ሀገራችን ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ እየታገልን ዓለምን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት መሳተፍ ይኖርብናል። የላንዳፍታ የዝግጅት ክፍል ለዩኒሴፍ መልካም የልደት በዓልን በመመኘት በጐ ተግባሩን እንዲያስፋፋ እንዲቀጥልበት ያበረታታል። በጐ ፈቃድ፣ መረዳዳትና ሰላም ለዓለም ሕዝቦች!!

## ለ) የኖቤል ሽልማት፣ ታሪኩ እንዲህ ነበር።

የኖቤል ሽልማት ድርጅት ዓለምን ለበጐ ነገር በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሕብረተሰብና በልማት... ወዘተ በመለወጥ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ግለሰቦች በማክበር በየዓመቱ ሽልማት ይሰጣል።

የኖቤል የሰላም ሽልማቱ የሚሰጠው በኖርዌይ የፓርላማ ልዩ ኮሚቴ በኦስሎ ማዘጋጃ ቤት ነው። ኃላፊነቱን በአደራ የተቀበለው የኖርዌይ መንግሥት ነው። የታሪኩ መነሻ እንደዚህ ነበር። አልፈርድ በርናርድ ኖቤል ደማሚትን የፈለሰፈው የስዊድኑ የቅመማ ሊቅና መሐንዲስ ከገቢው (ከሀብቱ) $9 ሚሊዮን ብር በመመደብ በዲሴምበር 10፣ 1896 (እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር) ሲሞት በሽልማት መልክ ዓለምን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ግለሰቦች በየዓመቱ ተበቃቅቶ እንዲሰጥ ተናዘዘ።

ሽልማቱን ካገኙት ውስጥ የካልካታዋ እማሆይ እናት ተሬዛ፣ የደቡብ አፍሪቃው ኔልሰን ማንዴላ፣ የቀድሞው የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር ሜናኪም ቤጊን፣ የቀድሞው የግብፅ መሪ አንዋር ሳዳት፣ ...ወዘተ ይገኙባቸዋል። 5 ሌሎች ሽልማቶች ለፊዚክስ፣ ለሕክምና ሳይንስ፣ ለሥነጽሑፍ፣ ለኬሚስትሪና እንዲሁም ለኢኮኖሚ ጥናት በስቶክሆልም (ስዊድን) ይሰጣሉ። እነዚህም ሽልማቶች በዲሴምበር 10 በየዓመቱ በኖቤል ሙት ዓመት መታሰቢያ ይከበራሉ። አሸናፊዎች ከዚያ በፊት ዜናው ሊነገራቸው ይችላል።

አረ ለመሆኑ ለምንድነው የአፍሪቃና የሌሎች የሦስተኛ ዓለም ምሑራን በኖቤል ሽልማት ቁጥራቸው ያነሰው? አንዳንዱ የሦስተኛ ዓለም ምሑር እጅግ ያስደስታል። ከነአንስታይንና ከሌሎች ፊዚስቶች በኋላ በቲዎረቲካል ፊዚክስ ሽልማት ያገኘው የሊባኖሱ ተወላጅ አብዱሰላም ነው። (ጥናቱም በGUT-GRAND UNIFICATION THEORY ነው) ግን ስሙ ብዙውን ጊዜ በምዕራብ የዜና መገናኛዎች አይሰማም። ዘረኝነት፣ በኖቤል ሽልማት አሰጣጥ አለን? እስቲ ከወደ ስካንዴኔቪያ በኩል የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና የላንዳፍታ አንባቢዎች እውቀቱን አብሩልን። የላንዳፍታ የዝግጅት ክፍል ለኖቤል ሽልማት ቢታጩም ባይታጩም ዓለምንና ሀገራቸውን ወደ ቀና መንገድ ለመለወጥ አስተዋፅዖ የሚያደርጉትን የኢትዮጵያ ብርቅዬ ምሑራን ያከብራል፣ ሠላምታም ይሰጣል። ለእናት ሀገራቸው መፍትሔ ፍለጋ ግዳዊ የአእምሮ ብርኃዊነታችሁ (Inevitable Conscientizacion) ከእድገቱ እንደማይቆጠብ እንተማመናለን።

*ምንጭና አገናዛቢ ቅንብር (Reference)- Rudis Resident News, 1996፣ Encyclopedia Britanica (1995), Scientific American (1995)

# የግጥም ጉባኤ

## ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ!
### (እንዲያው ለትዝብት እንኳ!)
ከልሳኑ ስምረት

እኔም ወግ ደርሶኝ ወግ ደረስ
ልሁን ግለኛ ቢሻኝ በነቃሽ ሳልነቃቀስ
የእውነት ልጓም ሳይሸብበኝ አሻፍሮኝ ሳልመለስ
ላፍታም ትሁን ልረካከስ
እንደገናም ልመለስ፤
ክልል በክልል ዘልዝዬ
ፍቅር ጠምቶኝ ሳላሰልስ ጉሳዬን ሆኜ እንደጉሳዬ
ቀና ታሪክ ሳይነሽጠኝ ተለያይቶ ተፈጥሮዬ
ምዕራፌ እንኳ ሳያጥር ግብሬ ሳይተናነስ
እኔም ወግ ደርሶኝ ወግደረስ።
ጥርስ በጥርስ አሳብሬ
የቤት ምሥጢር መርምሬ
ቅራኔና ጠብ ፈርፍሬ
መጣፍ ቅዱስ አስቆጥሬ፤
ለምኞት እንኳ ሆኖ
ነፍሲ ዳግም ተኮንኖ
ዘረኛ በሆንኩ ዛሬ ክሮሞዞም ወጣጥሬ
ዋልታ ለይቼ ተሽከርክሬ
በሳንጃ ጂን ወድሬ ደብል ሔሊክስ ተርትሬ።
እንደአርቢ ባለጠጋ
ትዕቢተኛ ጠጋጋ፣
የቅርጫን ቤት አባዝቶ ጥቁሩን ከብጫ ገርቼ
ነፍስ ከነፍስ አራኩቼ ሕይወት ድባቅ መትቼ፤
ጌቶ የሞት ባድማ
የወንጀል ግሬሽ አውድማ
የቁም ሥቅል አፍርቼ
ከመሰሉቼ ጋር ዶልቼ።
ባይሆን ይቀናኝና
ለኔ ትምን ለኔ ዝና
ሀገር ባገር አፋልጨ
አድማስ ካድማስ አከርና
ሐቅብ እንደ ልጥ ልጩ
በወለድ–አገድ ደፍጥጨ፣
በመዋቅር ማስተካከል
በማባረርና በማገለል
የትውልድ ላብ መጥምጩ ቆዳን ገፍፌ መዝርጩ፤
ምነው ለደቂቃ እንኳ
ለጊዜ ንዉስ ታንኳ
ልቅሶ ያስደስት እንደሆን
አሽካኪ ቅመምነቱን
የሳቅ ጋዝ ንጥርነቱን፣
ሬሲስት ዘረኛ በሆንኩ
ኖራ ተቀብቼ ባጤንኩ
ጥቁርነቴን መመለስ ብችል
ለምፃም ሆኜ በተከዝኩ
ወረቀት እንኳ ብመስል
እንደገናም በጠኮርኩ
እንደጥቁር የራስ ቅማል
በደመኛነት በጠየምኩ።
ሥቃይ የፈካ እንደሆን
ሥጋ ፈርሶ ሲበታተን
ለደቂቃ በታዘብኩ
ለፋንታሲ ታህል እንኳ
ለጊዜ ንዉስ ታንኳ
ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ።
የቅፅበት ምኞቴ ተሳክቶ
ሕሊናዬ ሁሉን ዓይቶ
ወርስ ለወርድ አለካክቶ
ጉን ለጉን አስተያይቶ፣
እንደገናም ተገልብጦ
በእውነት ሰይፍ ተግጦ።
ስሜቴን ልቀይር ብችል
እንዴት ብካይ ያስለቅሳል?
ለቅፅበት ሬሲስት በሆንኩ
ዓይን አውጥቼ ባላፈርኩ
ከዳር ቆሜ በዘፈንኩ፣
እንደፋንቶም አፍ ዘኦፔራ
የበቀል ብቅል ደመራ
በማስክ ተሸፍኜ ባሾፍኩ
ለፋንታሲ ታህል እንኳ ...
ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ።
ስንቡላ ሆኜ ደጂ መሬት
ኩት ሰላይ ነገረ ኮትኩት
ቆጣሪ አስትሮሎጂስት፤
ምነው ለትዝብት ብዬ
ለጊዜውም ቢሆን ተሥዬ፣
ነማዊባ በለበስኩ
ራሴን ላፍታ አገርጥቼ
እምባ በመለኪያ ጠጥቼ
ጉርዶን ሻምፓኝ ነው ባልኩ
እንዲያው ለትዝብት እንኳ–
ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ።
ከነጩ ጋር ነጭ መስዬ
እስስት ሆኜ ተሳስዬ
ገበሎ ሆኜ በሠረሠርኩ
ለፋንታሲ ታህል እንኳ –
ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ።
ላንዳፍታ አሽካክቼ
ተፈጥሮዬን አኮላሽቼ
በዕብሪት በተወጠርኩ
እንደገናም ተፈትቼ
እንደሰውም ሰው በሆንኩ
ተመልሼም ባዘንኩ።
በምስለ–ፍቁር ወልደ ስም
በልባዊት ኪዳን ግጣም
ባማላጂ ባዳንኩ
ተፈጥሮንም ባጤንኩ
ለፋንታሲ ታህል እንኳ–
ለሴኮንድ ሬሲስት በሆንኩ
ዳግመኛም ተሠርቼ
እንደ አላዛር ተነስቼ
እንደ ሰው ሰው በሆንኩ።

## ላንዲት ጣልያናዊት

(ከዶ/ር ፍቅሬ ቶለሣ)

ባድዋው ጦርነት
በሺ ስምንት መቶ ሠማንያ ስምንቱ
አያቴ አያትሽን
አዎን ገድሎት ነበር ተዋግቶት በብርቱ።
በማይጨው ጦርነት
በሺ ዘጠኝ መቶ በሃያ ስምንቱ
አባትሽ አባቴን
አንድዶት ነበር እስኪያር ሰውነቱ።
ማሪያ እኔና አንቺን
እኛን ምን አገባን ጥንት በሆነ ጥል
አቀፊኝ ልቀፍሽ
ሣሚኝ በይ ልሣምሽ የኔዋ ቅምጥል።

## ወጣት ሰማዕታት

ታህሣሥ 26/1985 በህዝብ አደባባይ በግፍ ለተጨፈጨፉት የአ/አ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መታሰቢያ
ከግርማ ዘገየ ቺካጐ—ኢሊኖይ

ያገር ትንፋሽ የእውቀት በር
የነገ ቅርስ የአገር አድባር
አፍላ ለጋ ድፍን ድርሣን
ድንግል አካል የቁም ሙታን
ዳኛ ሳይቆም ክስ ሳይቀርብ
ጥፋታችሁ ሳይታወቅ ሳይነበብ
በባዶ እጅ ትጥቅ ሳይኖር
በአገር እምነት ላገር መኖር
ለነፃነት ለእኩልነት
ለአንዲት አገር ለአንድነት
ለአፈና ሞት ለጅምላ እሥር
በዚህ ደሃ ምስኪን ምዝብር
በአንድ ድምፅ በአንድ አቋም
በአገር ፅናት ሥጋና ደም
እምነት ነግሦ በውስጣችሁ
በአደባባይ ለሞኻችሁ
ለህዝብ እንባ ለቆማችሁ
ሠማዕታት ተማሪዎች ...

ሞታችሁ ሞታችን ነው
እምነታችሁ እምነታችን
መቼም ቢሆን ይታሰባል
ማህደር ነው በልባችን
ታህሳስን እንረሣውም ...
... የአፍላ በድን ውስጡ ቀብሯል
በቅጥረኛ በአምባገነን ...
... በምሁር ደም እጁን ታጥቧል
እናንት ወጣት ተማሪዎች ...
... ላገር መቆም ሳስቀጣችሁ
በሣንጃ ውግ በሰይፍ ምት
... በቀል መድፊያ ለሆናችሁ
ለሞታችሁ ክቡርነት
ለትግላችሁ ህያውነት
ለእናንተ ወጣት ሠማዕታት
ታህሣሥ 26ን እንከንነው ...
... አይዘንጋ ይህ ክፉ ዕለት
በሃዘን ልብ እናስበው ...
... ለእናንተ ወጣት ሠማዕታት።

# የጥቁር ታሪክ
# የዓለም ታሪክ ነው

በማርቪን ኤክስ
ትርጉም በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(ለፌብርዋሪ የጥቁሮች ወር መታሰቢያ)

በቅድመ–ዓለም የነበርኩትን
በቅድመ–ጊዜያት የኖርኩትን
አራት ሚሊዮን ዘመን ያለኝን
መሣሪያ ጉኔ የነበረኝን
የሰው የመጀመሪያው አዳሙን
ከኮንጐ እስከ ዴልታ (ግብፅ) ዐባይን
አራት ሺህ ማይልስ የሮጥኩትን
በቅርቡ አግኝተሽኝ
«ሉሲ» ብለህ ጠራሽኝ

የጥቁር ታሪክ የዓለም ታሪክ ነው
እኔ ከአብርሃም በፊት
ከእብራይስጥ መወለድ በፊት
በከንዓን የኖርኩኝ
ከነዓን የሃም ልጅ ነኝ።
ዐረብና ይሁዲዎች፦
በምድሬ ላይ ሲፋጩ የሳቅሁ
በሳባ፣ በሳውዲ አረቢያ የኖርሁ
ቀይ ባህር ላይና ውስጥ የተጫወትኩ
በፐርሺያ ስርጠ–ምድር የኖርኩ
ምልክቴን ከባቢሎን
እስከ ቱምበክቱ የተከልኩ
ባቢሎን ስትሞኝ የነበርኩ፣
ምኝ፡
ባቢሎን ስትወድቅ የነበርኩ፣
የወደቅሁ ነኝ።
እኔ የመጀመሪያው አውሮጳዊ የነበርኩ
ኔግሬቶ ወይም ግራማልዲ የተባልኩ
ሜዴትራንያንን፦
ነኝ! ከእስፔይን እስከ ግሪክ ያቋረጥኩ

አ! ግሪክ፣
ስለምን ሶቅራጥስን ገደልሽው?
ስለምንስ ሐምሎክን መርዝ አጠጣሽው?
በሶቅራጥስ የአቴንስን ወጣት ያሳመኑቱ
እነማን ነበሩ መጤ አማልክቱ?
የእኔ አማልክት ነበሩ
ጥቁር አማልክት ከአፍሪቃ!
አ! ሶቅራጥስ፣ ፕሌቶና አሪስታትል
የግሪክን ለግሪክ ያስተማራችሁት
የማንን ፍልስፍና ነው ያስጠናችሁት?
ፓይታጎረስን፣ ቅመራን ከየት ተማርህ?
ዴሞክራተስ ስለፈለክ ከየት አጠናህ?
ሳሎንና ሊኩረገስ ሕግን ከየት አጠናችሁ?
በግብፅ ውስጥ አይደለም?
ግብፅስ አፍሪቃ አይደለችም?
አፍሪቃም እኔም

ሆሜር በኢሊያድ ውስጥ የተረከላችሁ
የተቃጠለ ፊት፦
ኢትዮጵያዊው ነኝ እያጠራጥራችሁ
ሆሜር ስለ ዩሊሰስ ታሪክ ያወሳላችሁ
ከእኔ ዘንድ ነው ያገኘላችሁ

የጥቁር ታሪክ የዓለም ታሪክ ነው
የመጀመሪያው ቻይናዊ የሆንኩት
ዐይኖች የእኔን ያላት
ነኝ እስያዊ ቀዳሚት
ስለ እኔ በቪየትናም፣
በካምቦዲያና ታይላንድ ውስጥ ተመልከት
ዛሬም ቢሆን
እዚያው አለሁ በጥቁረትና በውበት

የጥቁር ታሪክ የዓለም ታሪክ ነው
ኮሎምበስ እኔ ዘንድ ከመምጣቱ
አቅጣጫ ከመጠየቁ
ቀድሞ አሜሪካ የምመላለሰው
አሜሪጎ ቬስፑቺ በአሜሪካ ጉዞው
በአትላንቲክ ውስጥ አየኝ በተመላላሽ ጉዞው
ከአዜቲክ በፊት፣
ከማያ በፊት፣ ከቶልቲክ በፊት
ከኢንካና አልሜክ በፊት
አሜሪካ ነበረ የእኔ ቤት
ምክንያቱም፦
ቀድሞ ስለነበርኩ
እኔው እዚሁ ነበርኩ
ከሃያ ሺህ ዘመን (በፊት)
ወደ ፔሩ መጣሁ
ሜክሲኮ ከተማን ደግሞ ቆረቆርሁ
በቫራ ኩሩዝና በዮካንቴ ሁነህ
ፒራሚዴን አየህ?
ካብዛ ካሎሳሌን አየህ?
ሜክሲካዊ የሆንኩ
ከሁሉ የተዳቀልኩ
ሁሉ የተዳቀለኝ
ሌት ከቀን፣ አፍቃሪ ሰላምን
ፍፁም ሰላማዊ እውነተኛ ሰው ነኝ።
አንዳንዴ ቀማኛ ጨቋኞች ይነጩኛል፥
ያጠፉኛል
አንዳንዴ በሃሰት ሰዎች ይወቅሱኛል፣
ወይ ደግሞ ያሙኛል
አንዳንዴም በመስቀል መስዋዕት ያደርጉኛል
ነገር ግን ፍፁም ተመላሽ ነኝ!
ዘለዓለማዊ ነኝና
ዓለም–አቀፋዊና ነኝና
አፍሪቃ አገሬ ነው!
እስያ ምድሬ ነው!
አሜሪካን ቤቴ ነው!
የጥቁር ታሪክ የዓለም ታሪክ ነው!!

**Allstate**
You're in good hands.

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978) FAX: (404)299-6266



AUTO
HOME OWNER'S
RENTERS
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO

THEODROS
HAILEGIORGIS
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allsttate Indeminity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You'r in good hands.

# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በጎደሉ ፊደላት ማንኛውም ፎንት የሚቀበል የዊንደውስ ፕሮግራም ውስጥ በማንም ፎንት ለመጻፍ ግዕዝኤዲት GeezEdit $99.00 ። ኢትዮወርድ/ግዕዝኤዲት EthioWord/GeezEdit $199.00 - for use in any Windows 3.1 and Windows 95 program which allow font substitution. ግዕዝን ከዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማተምና ለመፈለጊያ ኢትዮሳይበር EthioCyber $495.00 ። (Multi-lingual hyper linked documents) ምሳሌ:- ዐረብኛ/Arabic (جـثـجـرخـخـثـث) ግሪክ/Greek (Σ΄Ωϱ,ΰώεΰ) ሕብራይስጥ/Hebrew (ጘ"ኂ"ጔ) ጃፓን/Japanese (ムラモトメヤメトニ) etc. Type, publish and search Ethiopic documents on the Internet and enjoy it on Windows, Macintosh an UNIX platforms. Check out the Ethiopic pioneers at ***http://www.ethiopic.com*** and get **FREE** software.

**የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር**

**Ethiopian Computers and Software**
**9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA**

**Fettan Graphics 1209 U St. NW, Washington, DC 20009**
Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail:*Ethiopian@aol.com* – ዶ/ር አበራ ሞላ ኢ-ሜል በግዕዝ (Ethiopic E-Mail)

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!!

ከአትናትዮስ

## ክፍል 10

"You asked for it?" ብላ ተስፈንጥራ ከተቀመጠችበት ተነሳች። ዓይኗ ተጎልጉሎ ወጥቶ ቁና ቁና እየተነፈሰች ስትወራጭ ሳያት አንድ አስፈሪ ሲኒማ የማይ ነበር የመሰለኝ።

«ጣልሽስ በሃሣቤም አልነበረ። የአንቺ ሁኔታ ነው የገፋፋኝ» አልኳት በድጋሚ። በጥፊ የምትለኝ ስለመሰለኝ ፊቴን ከእሷ ዘወር አደረግሁ። ይውጣላት ብዬ ነው እንዲህ ጠንከር ብዬ የተናገርኳት።

«ምንድነው የእኔ ሁኔታ?» አለችና ጣራው እስኪቀደድ ጮኸች። ዓይኗ የበለጠ ፈጠጠ።

«ቀስ በይ የእኔ እናት አትጩኺብኝ» አልኳትና አለችበት ቦታ ጥያት ቀደም ሲል ወደነበርኩበት ክፍል ሄድኩኝ። ቤቱን ለቅቄ ለመሄድም ወሰንኩ።

«የምትናገረውን ማወቅ አለብህ፤ ምንድነው የእኔ ሁኔታ?» አለች ከኋላዬ እየተከተለች ወደአለሁበት ክፍል እየመጣች። ድምጿን ስሰማ ጭራቅ የተከተለኝ መሰለኝ።

«ቢገባሽና አዕምሮ ያለሽ ሰው ብትሆኚ እኔ እንግዳሽ ነኝ። ካለሁበት ቦታ የመጣሁት ባንቺ ግብዣና እንግድነት ነበር። እንደዚህ እያበሻቀጥሽ ባልተነገርሺኝም ነበር። ግልፅ አድርጌ ልንገርሽና የፈፀምነው ነገር ሁሉ ሁለታችንም ተስማምተንበት ያደረግነው እንጂ እኔ ብቻ ፈልጌና ፍላጐቴን ጉልበት በመጠቀም የፈፀምኩት አይደለም። ጊዜው ስለመሸ እንጂ አሁኑኑ ልሄድልሽ በቻልኩም ነበር። ከፈቀድሽልኝ እዚህች ካውች (ሶፋ) ላይ ልደርና በጠዋት እሄድልሻለሁ። እባክሽ ልለምንሽ አልኳት።»

ትንሽ ፍርሃትም ቢጤ ያዘኝ። የተለማመጥኳት ወድጄ አይደለም። ሁኔታዋ በጣም አስፈራኝ። ፖሊስ ጠርታም የምታስይዘኝ ዓይነት መሰለኝ። ከልቤ ነው የምላችሁ ያለሁበትን ሁኔታና የማይባትን ነገር እዚህ አጠገቤ ሆናችሁ ብታዩ ኖሮ ይህም ሲያንስ ነው ትሉኝ ነበር። በትዕግስቴም ሳትደነቁ የምትቀሩ አይመስለኝም።

አነጋገሬ ተሰማት መሰለኝ ከቁጣዋ ትንሽ መለስ አለች። ተጉረጥርጠው ሊወጡ የነበሩት ዓይኖቿ ወደ አፎታቸው ገቡልኝ። ነፍሴ መለስ አለ። ትንሽ የመደናገጥ ሁኔታም ያየሁባት መሰለኝ።

‹‹እኔ ሂድ አላልኩህም።›› አለች ምንተእፍረቷን።

«ከዚህ በላይ ምን ልትይ ነው። ለማንኛውም አሁን ብዙ ባናወራ ይሻላል። እኔ እዚህ ጋ አድራለሁ፤ አላስቸግርም። ከላይ የምደርበው ነገር ካለ ብትሰጪኝ በጣም አመሰግንሻለሁ።» አልኳት ቁርጥ ባለ አባባል።

«ላይ አልጋ አለልህ። አይደል እንዴ?» አለች ለስለስ ብላ። ሁኔታዋ ገረመኝ። ትንሽ ቀደም ብላ እሳት ነብር የነበረችው ልጅ እንዲህ ከመቅፅበት ተለውጣ ለስላሳ ስትሆን ጭራሽኑ የበለጠ ፈራሁዋት።

«የትኛው አልጋ?» አልኳት። ሌላ አልጋ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ።

«የኔው ነዋ!» አለችና ትንሽ እንደመሳቅ አለች።

በጣም ተናደድኩ። የምታሾፍብኝና የምትቀልድብኝ ዓይነት ሆና ታየችኝ። ተራዬን ልገነፍል ነበር።

«Thank you!! በጣም አመሰግናለሁ። እኔ እዚሁ ነው የማድረው። የምደርበው ነገር ብቻ ስጪኝ» አልኩና ጋደም አልኩ ካውቹ ላይ።

«ልክ አይደለህም። አንተ ደግሞ ምንድነው በትንሽ ነገር ኩርፍ የምትለው?» አለችና ጋደም ካልኩበት መቀመጫ ዳር ቁጭ አለች።

እንዲህ ያለ ቅፅበታዊ የጠባይ መለዋወጥ የሚታይበትን ሰው መጠንቀቁ አይከፋም በሚል ምንም መልስ ልሰጣት አልፈለግሁም። ዝም አልኳት።

«ተነስና ላይ ተኛ፣ ነውር አይደለም እንዴ? አለችኝ።

ነገሯ ሁሉ እየገረመኝ መጣ።

«ይቅርታ አድርጊልኝ። ደከሞኛልና ጋደም ልበል። ፍቃደኛ ከሆንሽ የምደርበው ነገር ብቻ ስጪኝ። አበለዚያ ብትተይኝ ደስ ይለኛል ብዬ ዓይኔን እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገው ሰው ጨፈንኩት፤ እሷን ላለማየትም ነበር። ትንሽ ጊዜ ቁጭ አለችና

ተነስታ ወደ ክፍሏ ሄዳ አንድ ከላይ የሚለበስ ብርድልብስ ብጤ አመጣችልኝና ደህና እደር ብላ ሄደች። መልስም አልሰጠኋትም።

እንቅልፍ በዓይኔ አልዞር አለ። ንዴት አይሉት ድንጋጤ ብቻ ቅብዥርዥር አለብኝ። ጣራ ጣራውን እያየሁ የሃሣብ ማዕበል ይዞኝ ሄደ። በራሱ ከማይተማመን ሰው ጋር መዋዋል ትልቅ ችግር አለው። በጥርጣሬ ዓለም ውስጥ ካለንና ብሎም የዓለምን ቀጥተኛውን (ማለትም positive) ነገሮች የምናይበት ዓይናችን ከታወረና ሁሌ አሉታ (ማለትም Negative) በሆኑት ነገሮች ላይ ብቻ ዓይነ ሕሊናችን ከተገለጠ ችግር አለብን ማለት ነው። ሁሌ የምንኖረው በፍርሃት ነው ማለት ነው። ኑሮአችንን ወደፊት የምናይበትን ሕሊናችንን ሁሌ ወደ ኋላ ያለፈውን በመገላመጥ ብቻ የምንመለከት ከሆነ ሕመምተኞች ነን።

ትዝታ እስካየሁዋት ድረስ አንዱ ችግሯ ይህ ነበር። በራሷ ስለማትተማመን በጣም ተጠራጣሪና ፈሪ ናት። ቀደም ሲል በጻፈችው ታሪኳ ላይ እንደገለፀችው ጥንት የነበረው ኑሮዋ በተለይም አዲስ አበባ በነበረችበት ወቅት ማለትም በወጣትነት ጊዜዋ በወንዶች ላይ ትሠራ የነበረቻቸውን ተንኮሎችና ብልጥነት አሁን በተራው በእሷ ላይ የሚደርስ ስለሚመስላትም ነው በፍርሃት የታጠረችው። ራሷ ያደረገችውን ነገር እንኳ ካደረገችው በኋላ ለማድረጓ ትጠራጠራለች። ስለዚህም ለዚያ ምክንያት ትፈልጋለች። ምክንያቷ ደግሞ በአጠገቧ ያለ ሰው ይሆናል።

በራሷ ግፊት ያደረግነውን የፍቅር ጨዋታ እኔ በእሷ ላይ ጥቅም (Advantage) ለመውሰድ እንዳደረግሁት አድርጋ የተናገረችኝ አባባል ይህን በራሷ ያለመተማመን ባህርይዋን ያጋልጣል። ቀደም ሲል ላደረገችው ነገር ስህተት ከሆነ ከስህተቷ ለመማር በመፈለግ ፈንታ በሌላው ማለትም ቅርቧ ባለው ሰው ላይ የምታላክክ ሰበበኛ ከሆነች ችግር አለባት ማለት ነው። ስለዚህ ከዚህች ልጅ ጋር ምንም ዓይነት ግኑኝነት ሊኖረኝ አይገባም በማለት ወሰንኩና በነጋታው ሆቴል ሄጄ፣ አገሩን በራሴ ጉብኝቼ ወደመጣሁበት እስቴት ለመመለስ ወሰንኩ።

እንቅልፍ ሸለብ ያደረገኝ ሊነጋጋ ሲል ቢሆንም በጠዋት ተነሳሁ። መቼም አዳር አይደለም ያደርኩት። ምነው እግሬን በሰበረው። ገላዬን ተጣጥቤ ልብሴን ከቀየርኩ በኋላ ዕቃዎቼን መልሼ በሻንጣዬ ከታትቼ የእሷን መነሳት እጠብቅ ጀመር። በዚህ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለብኝ ወስኜ ጨርሻለሁ። ቶሎ አልተነሳችም። ወደ 10:00AM ገደማ ላይ ካለችበት ክፍል እኔ ወዳደርኩበት ክፍል መጣች።

«እንደምን አደርክ?» አለችኝ።

«እግዜር ይመስገን» አልኳት።

«ከተነሳህ ቆየህ እንዴ?» አለች። የድምጿ ቃና ከማታው ትንሽ ለስለስ ብሏል።

«አዎ፤ ... እና እባክሽ ታክሲ ጥሪልኝ።» አልኳት። የወሰንኩትን ነገር በተግባር ለመተርጐም።

«የምን ታክሲ?» አለች።

«ታክሲ ነዋ! ሆቴል የሚያደርሰኝ» አልኳት ደረቅ ብዬ።

«የምን ሆቴል?» አለች። አነጋገሯና አጠያየቋ ለስለስ ያለ ይምሰል እንጂ የፌዝም መስሎ ተሰማኝ።

«ዛሬን እዚያው ሆቴል አድርናና ነገ ወደ አገሬ እመለሳለሁ።»

«ምን አስቸኮለህ?» አለች

«የችኮላ ጉዳይ ሳይሆን እዚህ የምቆይበት ሁኔታ አልታየኝም። ስለመስተንግዶሽ በጣም አመሰግናለሁ።» አልኳት።

«ሶስት ቀን ልትቆይ አልነበር እንዴ አመጣጥህ?»

«ነበር ግን ሃሣቤን ቀየርኩ። አሁን በዚህ ነገር ላይ ብዙ ማውራት አልፈልግምና እባክሽን ያልኩሽን ታክሲ ጥሪልኝና ልሂድ» አልኩኝ።

«ምነው ያስቀየምኩህ ነገር አለ እንዴ? አለች።

ግራ ገባኝ። ሳቄም መጣ።

«ምንም ያስቀየምሺኝ ነገር የለም። አመሰግናለሁ አልኩኝ እኮ። መሄድ ስለምፈልግ ብቻ ነው።» አልኳት።

«ቆይ ቁርስ ላቅርብና በልተን እንነጋገራለን» አለች።

«ምንም የምንነጋገረው ነገር የለም። ቁርስም አልፈልግም። አሁን ያምፈልገው መሄድ ብቻ ነው» አልኳትና ተነሳሁ።

መጣችና ፊት ለፊቴ ካለው አንድ ወንበር ላይ ቁጭ አለች። «እንዴ ልክ አይደለህም። ሶስት ቀን እዚህ ቆይተህ ለመሄድ ነው የመጣኸው አይደል እንዴ?» አለችና ድምጿን በማለስለስ ለማሳዘን ሞከረች።

እኔ አንጀቴ እንዴ ብጥስ ብሏል። በየደቂቃው ለሚለዋወጠው ባህርይዋ የምመች ዓይነት ሰው ደግሞ አይደለሁም። እና እዚህ ቤት ከዚህ ሁኔታ በኋላ እንኳን ላድር አንድ ሰዓትም ልቆይ አልፈለግሁም። ከመሄዴ በፊት ግን ልነግራት የፈለግሁትን ሁሉ መንገር ነበረብኝ። ቢገባት ለእሷም ለወደፊቱ እንደ ምክር ይሆናል በሚል።

(በሚቀጥለው እትም የዚህ ገጠመኝ ታሪክ የመጨረሻው ክፍል ይቀርባል)

# የክርስቶስ ተከታዮች ወይስ የሬሣ ዶክትሪን ጠያቂዎች?

(ከእያዩ በልልኝ)

በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሁሉ በሕዝባችን መካከል በጴንጤ ስም የሚካሄደው መንፈሳዊ ወንጀል ከምንጊዜውም በበለጠ እየከፋና እየተባባሰ በመሄድ ላይ ይገኛል። ዛሬም እንደትናንቱ እውነት ከውሸት ተቀይጦ እንደሸቀጥ በየመንደሩ እየተሸጠ ከመሆኑም በላይ የሰውን ሚዛናዊ አእምሮ በማናጋት ፍፁም ወደሆነው እብደትና ድንዛዜ እያስገቡ ነው።

ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ አመነ ማለት፤ ከጥፋት ዳነ፣ እግዚአብሔርን አገኘ፣ ጥበበኛና ማስተዋል ያለው ሆነ፣ ፍቅርን አወቀ ማለት ነበር። ነገር ግን ዛሬ በየስፍራው የተነሱት የክርስቶስ ደቀመዝሙሮች ነን ባዮች ሰውን በዚህ ጥበብ ነፃ የሚያወጡ ሳይሆኑ አንድነትን የሚያፈርሱ፣ ታሪክን የሚያበላሹ፣ የፍቅርም ትርጉም ያልገባቸው በብርሃን ሳይሆን በጨለማ የሚመላለሱ አታላዮች ናቸው። በመድረክ ላይ ቆመው ሲያለቅሱ የሰው ፍቅር ያላቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን ምጥ እንደያዛት ሴት የሚያስጨንቃቸውና ታስሮ እንደሚገረፍ ውሻ የሚያስለፈልፋቸው የጥቅም ጉዳይ ብቻ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ በዚህ አጋጣሚም ሁሉም የጴንጤ አማኝ እንደዚህ ዓይነቱን ሥራ ይሠራል ማለት ሳይሆን እንደዚህ ያሉትን ለማጋለጥ ነው።

የአንድ ሕብረተሰብ ትልቁ የውድቀት ምልክት በየጊዜው የሚፈፀመው ስህተት ብቻ ሳይሆን የስህተትና የውሸት አሠራሮች እንደ እውነት መቆጠር መቻልና አልፎ ተርፎም እንደመመሪያ መውሰድ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው የፖለቲካ እብደትና የሃይማኖት ቅዠት ከዚህ አኳኋን የመጣ እንደሆነ ግልፅ ነው።

የሥልጣኔያችን ብዛትና የእውቀታችን ዓይነት ወዴት እየወሰደን እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ሰው ትኩር ብሎ ሊያስተውል የሚገባው አንድ ነገር አለ። ይኸውም "እምነት ከመስማት ነው። መስማትም የእግዚአብሔር ቃል ነው" የሚል ጥቅስ በመፅሐፍ ቅዱስ አለ። ይህ ጥቅስ በጣም ሰፊና ጥልቅ የሆነ ሀሳብ ያለው በመሆኑ ለመግለፅ ሳይሆን አጠቃላይ ግንዛቤው ምን እንደሆነ ብንረዳው ጥሩ ነበር። ሰው መስማት ያለበትና ማመን ያለበት የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ሲሆን ነው እምነቱ እምነት ወይም ትክክለኛ እምነት ሊሆን የሚችለው። ዛሬ ብዙዎቻችን እኛ የፈጠርናቸውንና የወለድናቸውን ሀሳቦች የእግዚአብሔር ቃል ነው እያልን እናምናለን። ስለዚህ የምናምነው ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ነው ብለን ብናሞጋግሰው በንፁህ ልብም ብናስተናግደው ዞሮ ዞሮ ምንጩ እኛ ራሳችን ስለሆንን የቃሉ ባለቤት እኛ ነንና የምናምነው ራሳችንን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳልሆነ ልናጤነው ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ከሆነ ቃሉ ከእግዚአብሔር ከራሱ የመጣ መሆን አለበት ማለት ነው። ስለዚህ ሰው አንድ ቀን አስተማሪ ሆኜ ገንዘብ አገኝበታለሁ ብሎ በስዊድንና በመሳሰሉት የአውሮፓና የአሜሪካ ከተሞች እየዞረ በመማሩ የሚያገኘው ጉዳይ ሳይሆን ባለበት ሥፍራ ሆኖ መታደል መቻል አለበት።

እምነት ከላይ ሲመጣ ብቻ አዳኝ ይሆናል። አብርሃም ምንም ት/ቤት ሳይገባ የ80 ዓመት ዕድሜ ሆኖት ነው "እግዚአብሔርን ሰምቶ አመነ" የሚል ጥቅስ የተፃፈው። ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ ከባርነት ነፃ ያወጣ ዘንድ የታዘዘው በእግዚአብሔር ነበር። ትዕዛዙንም አምኖ ሲቀበል በተግባርም ሲፈፅም ከአንዲት ብትር በቀር ት/ቤት ገብቶ እንደዘመኑ መንፈሳውያን እብደትንና ጩኸትን ሲያስተጋባ አላየነውም። ባህሩን በእምነት ከፍሎ መናን ከሰማይ ያገኘው ማንን ሰምቶ እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ አይሆንም። በባርነት መልክ ተይዞ ላለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም የእግዚአብሔርን በትር ይዞ የሚነሣና ነፃ የሚያወጣ እግዚአብሔር ይስጠን። ቀድሞ እንደነበረው እንደእነ ማርቲን ሉተር የመሳሰሉትን የመንፈሳዊ አብዮተኞች ዛሬም ያስፈልጉናል። በዘመናችን የተነሱ ብዙ የውሸት ደቀመዝሙሮች አሉን። እነሱንም ጭምር ነፃ የሚያወጣ እግዚአብሔርን የሚፈራ እውነተኛ ሰው ሊነሣ ያስፈልጋል።

አንዳንድ የዘመናችን ጴንጤዎች ነን ባዮች የእግዚአብሔርን ስም በየመንገዱ እያሰደቡ ናቸው። አንድነትን ሳይሆን ክፍፍልን፣ ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻን፣ ብርሃንን ሳይሆን ጨለማን፣ ጥበብን ሳይሆን አፍዝ አደንግዝ የሆነውን የጥንቆላንና የቃልቻን ወሬ ያናፍሳሉ። አተኩሮ ለሚመለከት በቴክሳስ ከተማ በእሳት ከተቃጠለው የኮሬሽ የጣኦት አምላኮ ጋር በይዘትም ሆነ በዓይነት አንድ ነው። የሚያስተውል ቢኖር በሕግ የሚያስጠይቃቸውን ሥራ በመሥራት ላይ ናቸው። የመወለድም፣ የማደግም፣ የመኖርም ትርጉም የጠፋቸው በመሆናቸው ወጣቱ ትውልድ በወጉና በሥርዓቱ መሠረት ተጋብቶ የልጅ ልጅ እንዳያይና የእምነቱ እሥረኛ እንዲሆን በመደረግ ላይ ነው። በሕልም ወይም በእኔ በኩል መልዕክት እስካልተገለጠልህ ድረስ እገሊትን ወይም እገሌን ማግባት ጥሩ አይደለም እየተባለ ስንቱን ባል ወይም ሚስት አልባ እንዲሆን ከማድረጋቸውም በላይ በእነሱ መንፈሳዊ ትርኢት ውስጥ ዘልቆ ላለመግባት ያፈገፈገውን ትዳር በመከፋፈልና በመለያየት በቤተሰብ ላይ ብዙ ችግር በመፍጠር ላይ ናቸው። የቤት ራስ ባል መሆኑን መፅሐፍ ቅዱስ በውል ያስጠነቅቃል። ሆኖም ግን ባል ሌላ ቤተክርስቲያን ሲሄድ ሚስት አንደኛው ቤተክርስቲያን ስትሄድ እያዩ ከጐን ሆነው ሲያጨበጭቡ ይታያሉ። ሕይወት ለሁሉም ነውና እኩል ፍቅር ለሰው ቢኖራቸው አንድነትን ማስተማር ሥራቸው በሆነ ነበር። "ይህ ሕዝብ በአፉ ያመልከኛል፤ ነገር ግን በሥራው ይክደኛል" የተባለውን ቃል በውል የሚያሳዩ ፍጥረታት ቢኖር ጴንጤ አንደኛውን ሥፍራ ይዟል።

ከሶስት ወር በፊት በአትላንታ ከተማ አንድ ኢትዮጵያዊ ይሞታል። ጓደኞቹና የቅርብ ዘመዶቹ የአስከሬን መላኪያ ገንዘብ ማሰባሰብ ነበረባቸው። በመሆኑም አንዲት እህት የዕርዳታው ሁኔታ ይበልጥ ተስፋ ያለው በጴንጤዎቹ ዘንድ ሳይሆን አይቀርም በሚል

እምነት ወደ ቤተክርስቲያናቸው ትሄዳለች። ጉዳዩንም ለሚመለከተው ክፍል ታሳውቅና ሀሳቡም በጉባኤ ላይ እንዲቀርብላት ትጠይቃለች። ሆኖም ግን የገንዘብ እርዳታ አናደርግም ቢባል መልካምና የተሻለ ሆኖ ሳለ የተሰጣት መልስ ፍፁም አሳዛኝና አስደንጋጭ ነበር።
መልሱም እንዲህ ነበር፡-

"ለመሆኑ የሟቹ እምነት ምን ነበር? ክርስቲያን (ጴንጤ) ወይስ ሌላ? የሚል ጥያቄ ቀረበላት። እሷም እምነቱስ ያው ክርስቲያን የኦርቶዶክስ ተከታይ ነው አለቻቸው።

"እይ እኛ ልንረዳ የምንችለው ጴንጤ ሲሆን ብቻ ነው ብለው እርፍ።" የገንዘብ መገኘት ወይም አለመገኘት ሳይሆን የመልሱ ይዘት የሰሚውን ልብ የሚሰብር ይመስለኛል። የእምነቱስ ጉዳይ ቢቀር ኢትዮጵያዊ መሆኑ ብቻ በቂ ነበር። ሬሣ ያውም የሚጣል ነገር እንኳንስ ከእምነትና ከአገር ልጅ ጋር የሚያያዝ ሳይሆን ሰብስቦ የመጣሉ ጉዳይ ላይ ጠላትም ተባባሪ የሚሆንበት ሥራ ነበር።

ክርስቶስ የሞተው ለዓለም ሕዝብ ሙሉ ነው። ኦርቶዶክሱ፣ እስላሙ፣ ጴንጤው፣ ... ሌላም ሌላም ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት የእምነት ወይም የዶክትሪን ስም ሳይሆን የልብ ጉዳይ ብቻ ነው። አንዱም ከአንዱ የማይሻለውን የምድርን ግሳንግስ ብናወራ ለምንም ለማንም የሚጠቅም ነገር አይሆንም። የዘርና የሃይማኖት ጉዳይ ምድራዊ እንጂ ሰማያዊ ጥበብም አይደለም። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ይህን መንፈሳዊ ጥበብ እናስተምራለን እያሉ "የሬሳ ዶክትሪን" ጠያቂዎች ምን ሊባሉ እንደሚገባ ነው። እንኳንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያስተምሩ ቀርቶ ክርስቲያን ነን ብለው ራሳቸውን መጥራታቸው ያሳዝናል። እንዲያውም ቃሉን "ክርስቲያን" የሚለውንም መጥራት የማይገባቸው ከሃዲዎች ናቸው። ይሁን እንጂ አንተ በሰው የምትፈርደው ማን ነህ ተብሎ ተፅፎአልና እኔም ምህረትን እሻለሁ።

ዳሩ ግን የዚህ የክህደት ሰዎች ሥፍራውን ለእግዚአብሔር ሰዎች መልቀቅና እነሱም ክርስቶስ ያስፈልጋቸዋልና ቁጭ ብለው እንዲማሩ ከበደላቸውም ነፃ ለመሆን ንስሐ ቢገቡ መልካም ነበር። የእግዚአብሔርን ስም አሰዳቢ ሆነው ከሚኖሩ ሞት ይሻላቸዋል። በዚህ ማንነታቸውና ህልውናቸው ኪሳቸው ዘር የሚዘራበት የእርሻ ሥፍራ መሆኑ ያሳዝናል። የስንቱን ላብና ድካም አታለዋል። ይህን ብትናገር እንዲህ ዓይነት ይሆንብሃል እያሉ የጥንቆላንና የቃልቻን ትምህርት ከማስተማር አልተቆጠቡም። የፈውስንና የሃብት ምንጭ አስተማሪዎች በመሆን የክርስቶስ ኢየሱስን የሕይወትና የምሳሌ ሥራ ሁሉ አራክሰዋል።

በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞችና በኢትዮጵያም ምድር ምንም የማያውቁትን የዋህ ሕዝብ በነፍስ ስጋው ይጫወታሉ። በተለይ በዚህ በአሜሪካ በቺካጎ ከተማ በየዓመቱ ወደ አንድ ሺህ የሚሆኑ ተሳታፊዎች የሚካፈሉበት የመንፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ ይደረጋል። እያንዳንዱ ተሳታፊ ቢያንስ ቢያንስ $225 እስከ $300 ዶላር ይከፍላል። በትንሹ ብንገምተው ወደ $200,000 ዶላር ማለትም አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ይሰበሰባል። ይህም ትርኢት ለአሥር ዓመታት ያክል ተከናውኗል። "ፀጋ ለሁሉም" በማለት ገና ት/ቤት እያለ ትምህርቱን በማቋረጥ ለሕፃናት መርጃ ሲል ወደ ኢትዮጵያ ምድር ተመልሶ ዛሬ ክሊኒኮችን በማሠራት የተቸገሩትን ህፃናት በመርዳት ላይ የሚገኘው ወጣት ዮናስ ከበደ (ከዚህ በፊት በዚሁ በላንዳፍታ መጽሔት ተዋውቋል) የእነሱን ያክል መንፈሳዊ እውቀትም ሆነ የገንዘብ እርዳታ የለውም። ታዲያ እነዚህ እንኳንስ ክሊኒክ የአንድን ሕፃን ጉሮሮ ለመድፈን እጃቸውን የማይዘረጉ ነገር ግን የአሜሪካንና የአውሮፓን ቪዲዮና መኪና መሸመቻ ለመሰብሰብ በእግዚአብሔር ስም ሲነግዱ እጅግ ያሳዝናል። ዳሩ ግን የገደልናቸው በቁም ደርቀው በገንዘብ ረሃብ እንዲያልቁ ያደረግናቸው እኛው ምዕመናንም ጭምር ነንና ራሳችንን እንመርምር። ነፍሰ ገዳይነታቸው፣ ራሳቸውንም በመካብ እንዲጠወልጉና ከሕይወት መሥመር ውጪ ያደረግናቸው እኛው ተከታዮች ነን።

መንፈሳዊ መሪነት ምንም እንዳልሆነ ነገር ግን ማንም ቢሆን ማንም ነገ ጧት እንደጨርቅ ከመጠቅለል የማይተርፍ መሆኑን አለመገንዘብ ለመንፈሳዊ መሪዎች ድካምና ከንቱ ውዳሴ ምዕመኑ ተጠያቂ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ መንፈሳዊ አባቶቻችን ከሰማይ የወረዱ መለኮታዊ ኃይልን የጨበጡ ሳይሆኑ ከማንኛውም ሰው የማይሻሉ ደካሞችና ስጋውያን መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዘመናቸው ሁሉ ያካበቱትን መልካም መንገድ ቢያስተምሩን የአባትነታቸውና የዕድገታቸው ውጤት እንጂ መለኮታዊ ባህሪ እንደሌላቸው ማወቅ አለብን። ዳሩ ግን ሰው በሰውነቱም ሆነ በዕድሜው ባለፀግነት ሊከበር ይገባልና ልናከብራቸው ከሁሉም በላይ ደግሞ ከልብ ልንወዳቸው ይገባል። ይሁን እንጂ ፍቅር አያዳላምና ማንኛውንም ሰው እኩል መውደድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና እንደማንኛውም የህብረተሰብ አካል እኩል መወደድ ይገባቸዋል።

ከሁሉም በላይ በመድረክ ላይ ቁሞ መንፈሳዊ ስብከትን ማካሄድ ብቻ መንፈሳዊ አባት ሊያሰኝ አይችልም። ብዙዎች ለግል ጥቅም የሚሮጡ ሙያተኞችና ሌባ እረኞች መሆናቸውን ፈትነን የማወቁ ጉዳይ የየራሳችን ኃላፊነት ነው። ስለሆነም እንደፈሪሳውያን አጉል ግብዞች እንዳይሆኑና በስሜትም ተወጥረው በህይወት እንዳይጠወልጉ ሁሉም በጥበብና በማስተዋል ቢሆን ይመረጣል። አዳኝ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር እንጩህ። ከአስመሳዮችና ከተኩላዎች ራሳችንን ለመጠበቅ በጥበብ እንደግ። እኔም በበኩሌ ለዚህ ወረቀት መሞንጫጨር የገፋፉኝና አንዴ ወደ መንፈሳዊ አንዴ ወደ ፖለቲካው የምሮጠው ሁሉም ውጥንቅጡ ስለጠፋና ፖለቲካውም ሆነ መንፈሳዊ ጉዳዮች ለአንድ ህብረተሰብ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች በመሆናቸው ነው። "<u>የማያስተውል ሕዝብ ይገለበጣል</u>" ተብሎ እንደተፃፈው ሁሉ ይኸው ከእናት ጉያ የተለየንበት፣ ከአገር የተሰደድንበት፣ ዘመናችንን በመንከራተት የጨረስንበት፣ የሰውን መሠረታዊ አንድነትና ፍቅር ያጣንበት ምክንያት የማናስተውል ሕዝብ በመሆናችን ብቻ ነው።

እውነተኛ የወገን መሪና ከእግዚአብሔር የተላከውን ቃል የተቀበለ መንፈሳዊ አባት ስለሌለን

ካለጥበብና ካለማስተዋል እንድንሆን ሆኗል። ከጥፋት የሚጠብቀንን ምክር ለጋሽ አጥተናል። ድንዛዜ እንጂ ማስተዋል የሌላቸው፣ ጥላቻ እንጂ ፍቅርን የማያውቁ፣ ብልጠት እንጂ ጥበብን ያልተማሩ፣ ጦርነትን እንጂ ሠላምን የማይወዱ፣ መቀበልን እንጂ መስጠትን ያልተማሩ በየዘመናቱ የተነሱ ድፍን ቅል የሆኑ መሪዎችና መንፈሳዊ አባቶች ዛሬ ፍሬያቸው ምስክር ነው። ምስክሩም የኑሮአችን ይዘት ብቻ ነው። አገራችንን ብቻ ሳይሆን የረገጥናትን ምድር ሁሉ እያረከስን የምንገኝ ይመስለኛል። በዓለም ዙሪያ የተበተነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ቀና ሲል ጥቁር ሰማይ፤ ጉንበስ ሲልም ከምድር በቀር ሌላ የማይታየው ግራ የተጋባ ሆኖ ሲንከራተት በምድሪቷ ክልል የቀረውም ወገን የሚይዘውንና የሚለቀውን በማጣት በደንቆሮዎች አመራር ወደ ገደል በመጓዝ የሚሄድ የዕለት እስረኛ ነው። በዘመድ አዝማድና በሥልጣን መከታ በየሥፍራው ያውም ምሁሩ ክፍል ህክምና በማይገኝለት የፖለቲካ በሽታ ይዞ በመታመም ላይ ይገኛል። እርስ በእርስ መባላት እንጂ መስማማትን የማያውቁ ተበዳዮች ሆነዋል። በጠረጴዛ ዙሪያ ካለው ከወገናቸው ጋር መስማማት ተስኖአቸዋል። ነገር ግን ኑሮውንም ሆነ መልኩን ያላዩት በሩቅ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳበዳቸው ይመስላል። ትግሉስ መልካም ነበር ነገር ግን ማስተዋል የላቸውምና ከአንድ ውድቀት ወደ ሌላ ውድቀት መሻገር ብቻ እንዳይሆን እፈራለሁ። በጉናቸው ያለውን ወንድም የማይወዱ ከሆነ በሩቅ ያለውን ያላዩትን ሰው እንዴት ሊያስተዳድሩት ነው? ወይስ ተረኛ ዱለኛ ለመሆን መፈለግ እንዳይሆን።

እውነተኛ ፍቅር ካለ ጥበብ አለ። ፍቅር ካለ አንድነት አለ። ፍቅር ካለ ስምምነት አለ። ፍቅር ሁሉን ይታገሣል፤ የማይገባውንም አያደርግም። ስለዚህ ከትግል በፊት ፍቅርን እንማር። እንደ እኔ በድካም የምትመላለስ ወገን ሆይ እንግዲህ በርታ። የሚሻለውንም ለይተህ ታውቅ ዘንድ በፍቅር እደግ። ፍቅርም እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርንና የተፈጥሮን ፈቃድ ብናውቅ ከዱር አራዊት ባነሰ ሁኔታና ነፃነትን አጥቶ የሚንከራተተውን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት በቻልን ነበር። እውነትን ፈልጌ ፈላልጌ አጣኋት። ስለሆነም አለማወቄን አውቃለሁና በምንም እንዳልታበይ ተስፋ አደርጋለሁ። እናውቃለን ብለው በነፍስገዳይነት ራሳቸውን የሾሙት አለማወቃቸውን አውቀው ቢመለሱ መልካም ነገር ነበር። እውነትን አውቀናል እያሉ የስንቱን የዋህ አሮጊትና ሕፃናት ሲደልሉ ደካማውን ብርቱ ነህ እያሉ ሲያታልሉ፣ የረሃብተኛውን መጠውለግ እያዩ እጃቸውን መዘርጋት ያልቻሉ ነገር ግን በእጁ ላይ የቀረውን ፍርፋሪ ወስደውበት የቪዲዮና የተለያዩ ቁሳቁስ መሸመቻ በማድረግ ምድራዊ ደስታን ሲሰበስቡ እጅግ ያሳዝናል። አማኝ ነን ይላሉ ነገር ግን የእምነት እስረኞች እንጂ አማኞች አይደሉም።

ስለሆነም እስቲ ቆም እንበል። በስህተት መንገድ በአይሮፕላን ከመብረር ይልቅ በእውነት መንገድ በዝግታ መጓዝ እጅግ እጅግ ይበልጣልና። ደህንነታችንም ፅድቃችንም እምነታችንም ቢሆን መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁንልን። በሌላ ዝግጅት እስክንገናኝ መልካም ጊዜ ለሁላችንም። የሠላም አምላክ ከሁላችን ጋር ይሁን።

እያዩ በልልኝ–ከአትላንታ

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በጠየቁን መሠረት በብዕር ስማቸው በእያዩ ቢልልኝ ነው ያወጣነው። የሚኖሩት በጆርጂያ ነው። በዚህም ሆነ ቀደም ሲል በአወጡዋቸው ጽሑፎቻቸው የዘገቡት ከራሳቸው ልምድና ገጠመኝ በመመርኮዝ መሆኑን ገልጸዋል። እኔ ያልኩትን ልክ አይደለም የሚል ካለ በዚሁ መድረክ ልክ ያልሆነውን ሊጽፍልኝ ይችላል ብለዋል።


# የሥራ ማስታወቂያ

## ከኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማኅበር
## ሴንት ሉዊስ

ጽሕፈት ቤታችን የሚከተሉትን ነጥቦች የምታሟላ

**ኢትዮጵያዊት የሴቶች ጉዳይ አስፈጻሚና ፀሐፊ ይፈልጋል።**

1) ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀች፣
2) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋን (አማርኛን) መናገር፣ መፃፍና ማንበብ የምትችል፣ ሌሎችንም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መናገር ብትችል ለመቅጠር አስተዋፅኦ አለው።
3) ለማስተርጐም እንግሊዝኛ በማዕከላዊ ደረጃ መናገር፣ መፃፍና ማንበብ ችሎታ ያላት።
4) ማንኛውንም ሕዝብ በሰብዓዊነትና በፈቃደኝነት ለማገልገል የፀና እምነትና ፍላጐት ያላት።
5) የኮምፒውተር ልምድና የፅሕፈት ተግባር ተመክሮ ያላት።

Resume (የሥራ ትንታኔ) ካለ በአድራሻችን ላኩልን፣

ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION OF MISSOURI
2336 Tennessee Avenue
St. Louis, MO 63104
Telephone: (314) 776-7464
Fax: (314) 776-0401

# በአትላንታ ከተማ
# “የኢትዮጵያ ቅርሳ ቅርስ ኤግዚቢሽን”

ፍሬሰንበት ላቀው (ከአትላንታ)


ባለፈው ኖቬምበር 1996 የፈረንጆቹ ዓመት ማለቂያው አካባቢ “የኢትዮጵያ ቅርሳ ቅርስ ኤግዚቢሽን” በአትላንታ የሚል ማስታወቂያ በአትላንታ ከተማ ይበተንና እጅ ይገባል። “በክላርክስተን ባፕቲስት ቤተክርስትያን . . . ኤግዚቢሽኑ ለኢትዮጵያውያን ልዩ የአገር ፍቅር ስሜት፤ እንዲሁም ስለአገራችን ታሪክ ለማያውቁና ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ ደግሞ ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል ተብሎ ይገመታል።” የሚል ማስታወቂያ ነበር። “መግቢያ በነፃ ይልና ለወጪ መሸፈኛ ርዳታ እንጠይቃለን፤” የሚል ጎላ ያለ መልዕክትም ከላዩ ይነበባል። “በአቶ አማኑኤል ጣህር በአውሮፓና በአሜሪካ ሲታይ የቆየ የአገራችን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የሚገልፅ . . . ” የሚል የመግቢያ መግለጫም አለው። በጀርባው በእንግሊዝኛ African Arts & Books Exhibition በሚል ርዕስ ስር ዘርዘር ተብሎ ከተጻፈ በኋላ Sponsored by Amanuel & Tegga የሚል አለው። አቶ አማኑኤል የመጡት ከታምፓ ፍሎሪዳ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ የተገለጸ ሲሆን ሌላኛው አዘጋጅ ፓስተር ተጋ የአትላንታ ነዋሪ የባብቲስት ቤተክርትያን ካህን መሆናቸውን የአትላንታ ነዋሪዎች ያውቃሉ።



አቶ አማኑኤል ጣህር

ኤግዚብሽኑን ለማየት ከጓደኞቼ ጋር በሄድንበት ወቅት ከአዘጋጆቹ በስተቀር ሌላ አልነበረም። አቶ አማኑኤል ስለ ኤግዚቢሽኑ መግለጫ ሰጡን። ዓላማውና ዝግጅቱ ታሪክንና ባህልን ለማስተዋወቅ ስለተደረገ (ነው ተብሎ ተነግሮናልና) ጥሩ ነው እላለሁ። ጥያቀዬና ግራ ግብት ያሉኝ ነገሮች አሉ።

አክሱም ትግራይ ነው ተወልጄ ያደግሁት የሚሉት አቶ አማኑኤል በአብዛኛው ውድ የሆኑትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያናት ቅርሶች (ውድ የጥንት የብር መስቀሎች፤ የጥንት የብራና የጸሎት መጽሐፎች) በእጃቸው እንዴት ለያገቡ ቻሉ? ከየአድባራቱ እየጠፉ ናቸው ከሚባሉት ጋርስ ግንኙነት ይኖራቸው ይሆን? እሳቸውም ሆኑ ሌላው አዘጋጅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ተከታይ አለመሆናቸው እየታወቀ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያናት ቅርሶችን በምን መልኩ ሊያስተዋውቁ እንደተነሱ ሊገባኝ አልቻለም። በዚሁ ከተማ የታወቁና ብዙ ተከታይ ያላቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያናት እያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያናት ቅርሶች እንዴት በሌላ ቤተክርስትያን ሊታዩ በቁ? እንግዲህ በቂ መልስ የሚሰጠኝ ሰው እፈልጋለሁ።



ውድ የጥንት የብር መስቀሎች፤ የጥንት የብራና የጸሎት መጽሐፎች

## ከዝግጅት ክፍሉ

በወቅቱ በቦታው ተገኝተን ከአቶ አማኑኤል ተነጋግረናል። እንደ አመላለሳቸው ከሆነ ዕቃዎቹን ለመሰብሰብ ብዙ ወጪ አውጥቻለሁ ባይ ናቸው። ለማንኛውም ከሳቸው መልሱን እንጠብቃለን። ካነሳናቸው ፎቶዎች መሐል ከጥያቄዎ ጋር ግንኙነት አላቸው ያልናቸውን አውጥተናል።

በኤግዚቢሽኑ ላይ ከታዩት ቅርሶች በከፊል



በተለያዩ ጊዜያት የነበሩ የኢትዮጵያ ገንዘቦች

# አጭር ልቦለድ ታሪክ

## የተራበች ሕይወት

(ባሕል ቀመስ ፈጠራ)

በሰይፉ አዳነች ብሻው

© ፲፱፻፹፰ ዓመት

ድራሲው ከደቡብ ኢትዮጵያ አንዱን ባሕል በቁንፅል ከመውሰዱ በስተቀር ስሞቹም ሆነ የታሪኩ ሂደት ፍፁም የፈጠራ ሥራ ነው። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማንንም ህይወት አይጠቅስም።

ሰዓሊ በደረቀ ብሩሽ ያዋሀደው የሸራ ላይ ስዕል የመሰለው አመሻሽ ላይ የፀሀይዋ ቅርፅ ፈፅሞ አይታይም። ተሰውራ ከምታድርበት ጎጥ መግባቷ ቢታወቅም ብርሃኗ እንጂ እርሷ አትታይም። የደበዘዘው ብርሃን ሀዘንተኛ ይመስላል። ሙሾ እንዲሞሸለት አቤት አቤት በሚል መንፈስ አየሩ ተሞልቷል። ምናልባትም የጦራ መንፈስ አየሩን አፍኖት ይሆን? ፀሀይ በጠለቀችና በጋራና በሸንተረር ሥር ባሽቆለቆለች ቁጥር ለመሬት የቀረበች ወይንም በርቀት የቀረበች እየመሰለው ብዙ ምሽት ጦሩን ሰብቆ በማነጣጠር ወርውሮበታል። የወረወረው ጦር ግን ደቂቃም ሳይራመድ ሄዶ ከሚያነሳበት መስክ ላይ ተቸንክሮ መሬቱን ለመቦርቦር ውን ውን ሲል ያገኘዋል።

ጦራ ከፀሀይ ጋር ክፉኛ ቂም አለው። በእርግጥ ፀሀይ እሱን ብቻ አይደለም። ያስቀየመችው የበደለችው። ግን በእሱ ላይ ይብልጥ አተኩራበታለች። ሌሊትም ስለእሷ ሲያስብ ስለሚያድር የሌት ከቀን ጠላቱ ሆናበታለች። ዛሬም በከንፈሯ መሬትን ላም ስታደርግ ሲያያት እንደ ሚዳቋ ሮጦ ባለ በሌለ ጉልበቱ ጦሩን ወረወረባት። በነፀብራቋ ውስጥ ጦሩ መሬት ላይ ተቸንክሮ ሲመለከት የፀሀይዋ ልብ ላይ የተሰካ ይመስል ነበር። የጦሩ ጥላ ረዝሞ ከእግሩ ስር ለመድረስ ምንም አልቀረውም። እያጉተመተመ ከቋጥኝ ላይ ቁጭ አለ። ፀጥ ያለውን ምሽት የሚያደፈርሱት የዱር አራዊት እንደሱ የሚያማርሩ መስሎት ብቸኝነት ለቀቅ አድርጎታል።

በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት ምድሪቱ በቂ ወይንም የረባ እህል አልሰጥም ብላ ከተቸገረ ይኸው ሦስተኛ ዓመቱ ተገባድዷል። በተነቀሉ ሁለት የታችኛው የፊት ጥርሶቹ ማረፊያ ድድ ውስጥ ምላሱ እየሾለከ እየወጣ ለምቦጩን ገፋ ገፋ ያደርገዋል። ይህም ባህላዊ የጥርስ ነቀላ ሰው በድንገት ቢታመም ምላሱ ታጥፎ መተንፈስ እንዳይሳነውና በዕርዳታ ጊዜ ምግብ ወይንም መድሃኒት በቀዳዳው አሾልከው ለመስጠት እንዲቻል አስቀድሞ የሚወሰድ የጤንነትና የህይወት እርምጃ ነው።

የምርት መጥፋትም በህይወቱ የሚፈልገውን ለማግኘት እንዳይችል አድርጎታል። ሚስት የለውም፤ ላጤ ነው። ሚስት ለማግኘት ጥሎሽ መጣል አለበት። ጥሎሽም የቀንድ ከብቶች ማቅረብ ነው። ሀብት ስለሌለው የቀንድ ከብቶቹን ለመግዛት ለሌላ ሰው እያገለገለ ማደር አለበት። በቂ ገንዘብ አግኝቶ ከብቶቹን እስኪገዛ ድረስ። ይህም ችግሩ በግብርና እንዲተዳደር አድርጎት ፀሀይ ክፉኛ ጎዳችው። እህሉን፣ ምድሩን ብቻ ሳይሆን ዕድሜውንም እያቃጠለችበት ተቸገረ።

ጦራ ከብት ስለሌለው እህቱን እንደ ደንቡ በለውጥ ሰጥቶ ሚስት ማግኘት እንዲችል በዚህም አልታደለም። ለቤተሰቦቹ አንድ እሱ ብቻ ነበር። እህት ብትኖረው ኖሮ እህቱን አማቾቹ ከሌላው ላግባሽ ባይ ጥሎሽ ስለሚያገኙባት እንደ ጥሎሽ ተቀብለው እንደ ልጃቸው በተራዋ ይድሯት ነበር። አለመገረዝና ሱሪ አለመልበስ ብዙ ልጆች ለመውለድ ያስችላል ተብሎ በወንዶች ዘንድ ቢታመንም ለወላጆቹ አንድ እሱ ብቻ መወለድ እንቆቅልሽ ሆኖበታል።

ቁጢጥ ብሎ ከተቀመጠበት ስፍራ እግሩም ብልቱም የአፈሩን መደብ ተንተርሰውታል። አንዲት ዝንብ ስትበርር መጥታ ምንጭሩ ላይ ስታርፍ አፍንጫዋን ጭምር በጥፊ ብሎ አበረራት። ሆኖም ከሃሳብ አልገላገለችውም፤ ከሀዘንም አልመለሰችውም። የትዝታ ጉዞ ምዕራፉን ከፍታ ሰጠችው።

***

አትላን ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠች ሸጋ ልጃገረድ ነበረች። የሌሎቹ ለምቦጣቸው ተሰንጥቆ ገል ወይንም ሰፌ እንጨት ተደርጎላቸው የተዋቡ ቢሆኑም የእሷ በስፋትና የላስቲክነት ባህሪው ወደኋላ ስባው ጭንቅላቷን በውስጡ ታሾልከው ነበር። ይህን አስደናቂ ውበቷን ያገኘችው በቀላሉ አልነበረም። ለምቦጯን ከሰነጠቁላት በኋላ እስከሚደርቅላት ድረስ በደንብ ተጠብቃለች። የገሉ ጠርዝ ለምቦጯን እንዳይበላው በሚገባ አለስልሰው መጀመሪያ በትንሹ ተጀምሮ የለምቦጯ የመሳብ መጠን እየጨመረ በሄደ ቁጥር ሰፋፊ የከንፈር ጌጥ እያሰራች በማጥለቅ ይበልጥ አሳድጋዋለች። ይህም የውቦች ሁሉ ውብ እንድትሆን አደረጋት።

ገና ወንዝ ወርዳ ውሃ ማምጣት ስትጀምር የከንፈር ጌጧ የአንዲት ጣትን ውፍረት ያህል አታህልም ነበር። ይህም የመታጫ ወቅት በመሆኑ የጦራ ወላጆች ሽማግሌዎች ልከው ለጥሎሽ ይደርሳሉ። አቅማቸው የማይፈቅድላቸው ቢሆንም ቀስ በቀስ በየጊዜው የቀንድ ከብቶቹን ማቅረብ ስለሚችሉ የተቻላቸውን እያደረጉ ነበር። በመሃሉ ለጥሎሽ ከተሰጡት ሁለት ፍየሎች አንደኛዋ ስለወለደች እንደ ደንቡ እንደ ጥሎሽ ተቆጠረላቸው። ውበቷም ጥሎሿም እየበረከተ መጣ። የጋብቻ ጊዜአቸው በደረሰም ወቅት ጦራ በእንግድነት ከአማቾቹ ቤት እየተጋበዘ ይሄድ ነበር። በዚህ እውቂያቸው ወቅት አትላን ጥላቻ እንዳደረባት ለወላጆቿ ብትነግራቸው ጋብቻው ሊፈርስ ይችላል። ምክንያቷን የማይቀበሉት ከሆነም ከወደደችው ልጅ ጋር ለመኮብለል አማራጩ ነው። አስኮብላዩም ቀድሞ ያጣትን ጥሎሽ ያህል መተካት ይኖርበታል። ይህም

ከተሟላ ቀድሞ ያጫት የጣለው ጥሎሽ ይመለስለታል። በዚህም ንብረቱ ሌላ ለማጨት ዕድል ይኖረዋል። ጥሎሽ መጣል እስከቻለ ድረስ ወንድ ብዙ ሚስት ማግባት ይችላል። ሴቷ ግን ካገባች በኋላ ለባሏ ታማኝ ሆና እስከ ዕለተ–ሞቷ ድረስ በሚስትነት ትፀናለች። ጦራ ደስታዬን የሚነጥቅብኝ ምንም ነገር የለም ብሎ በዕድሉ የተማመነ ነበር።

ምንም እንኳን አንዲት ሴት ብትታጭ በአጫት ሰው ቁጥጥር ስር ትሆናለች ማለት አይደለም። ከፈቀደችው ወንድ ጋር መዳራትና በመወዳጅነትም መያዝ ትችላለች። ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ሀፍረተ–ስጋቸውን ከህፃንነት ጀምረው ስለሚሸፍኑ አትላን በዳሌዋ ላይ በጠፍር የተያያዘ ተንጠልጣይ የቀለህ ዝናር ላይ ቆዳ አገልድማለች። ከደንቢ ጋር መሽኮርመም ስትጀምር ፍቅራቸው የሚጠነክር አልመሰላትም ነበር። ደንቢ በጣም ስለወደዳት በአንገቷ ላይ የምታስረው ጨሌ ገዝቶ ሰጣት።

«ፍቅር ነው፣ ቃልኪዳን!» አላት ደንቢ ጨሌውን ለአትላን ሲሰጣት።

«የት ያደርሰናል? መንገዱን ታውቀዋለህ?» አለችው ግራ በተጋቡ ዐይኖቿ በመውደድ እየተንገበገበችለት።

«ህይወቴ ትርጉም የለውም።» *አንቺን አጥቼ ልኖር አልችልም፤* ማለቱ ነበር።

«ይህን ጨሌ ባጠልቅልህ ጦራን መጥላቴን *መግለጼ ነው።»*

«የወደድሽውን ባርያ ይበልጥ ታስሪዋሽ እንጂ *አታነግሽውም።»* ሲል ተቀኘባት። *እድሜዬን ሙሉ አገልጋይ ልሆንሽ የምችለው እኔ ነኝ ለማለት ነበር።*

«የእስረኛ ሰንሰለት እንደምትሰጠኝ ይገባኛል።» ካገባት በኋላ ነፃነት እንደማይሰጣት ለመጥቀስና የአሁኑ ወርቃዊ ማባባሉ ልቧን እስከሚያሸንፍ ድረስ መሆኑን ለመግለፅ ነበር።

«የወደዱትን ምራቅ አይተፉትም።» *አንቢ ብለሽ እንደማታሳፍሪኝ አውቃለሁ* ለማለት ነበር።

ጨሌውን እንደያዘች በመሮጥ ከደኑ ውስጥ ተሰወረችበት። ለመዳራት የዘረጋችው ግብዣዋ ነበር። ደንቢ አደኑን በስልት ያዘው። ድምፁን አጥፍቶ ነፋሱን ያዳምጥ ጀመር። የቅጠል መንሿሿት፣ የዱካ ድምፅ፣ የሩጫ አየር ቀዘፋ የሚፈጥረውን ድምፅ ይከታተል ነበር። አንዱን የግራር ግንድ ከለላ አድርጎ በጀርባው በመደገፍ ትንፋሹን ውጦ አደፈጠባት።

አትላን ቅጠሎችን ተገን አድርጋ አካል በአየር ውስጥ ሲጓዝ አልሰማ አላት። የዱካ ድምፅ የሚፈጥር እርምጃ የለም። ቅጠሎች ተገፋን ብለው አቤቱታ አላቀርብም አሏት። አድፍጣ ጠበቀች። እሷን ልፈልግ ብሎ የሚንቀሳቀስ ምንም ነገር አልሰማ አላት። ግራ ተጋባች። ቀስ ብላም በጣቶቿ እየረገጠችና ዐይኖቿን ግራና ቀኝ እያንከራተተቻቸው ደንቢን ትታው ከሄደችበት ስፍራ መመለስ ጀመረች። ደንቢ የተደበቀበትን ግራር እንዳለፈች ወደኋላዋ ገልመጥ ብላ አየች። ከማይንቀሳቀሰው ግራር በስተቀር ምንም ነገር አላየችም። ከወደምትሄድበት ስፍራ ኮሽታ ስምታ ፊቷን አዞረች። የተወረወረች ጠጠር የፈጠረችውን ድምፅ ነበር የሰማችው። በዚህ የማደናገሪያ ወቅት ደንቢ ቀድሞ ከነበረበት ግራር ስር ተመልሶ ቆሞ ከኋላዋ ያያታል።

«አትላን!» ሲል ጠራት በለዘበ ድምፅ። ከሩቅ የመጣ ድምፅ መስሏት ዞር አለች። የደንቢ ግራር ተደግፎ ቆሞ ማየት በምትሃት የተፈፀመ መስሏት በጣም ደነገጠች። በድንጋጤም ሁለት እጆቿን በአየር ላይ አንስታ እንዳለች ዘልሎ ያቅፋታል። የደረት አጥንቱ ሀዲዶች ላይ ያረፉት ጡቶቿ መስመር እንደያዘ ብዕር የፍቅር ታሪካቸውን ይፅፉ ጀመር። አካሏ ባረፈበት መሬትና በደንቢ የፍቅር ግለት መካከል ከፍ ዝቅ እያለ ያማርጥ ጀመር። ጀርባዋ ያረፈበት መሬት ሳርማነት ቢመቻትም ቅዝቃዜው ይሰማት ነበር። ብር አምባሯን አስረክባ የፍቅር ጨሌዋን በማሰር ወደ ቤቷ ተመሰሰች።

***

ጦራ አትላን ለመጎብኘት ሲመጣ አንገቷ ላይ ጨሌ አስራ ያገኛታል።

«*መቼ ነው ገበያ የወጣሽው?» ፍቅሬን በማን ነው የለወጥሽው? ለማለት እንጂ ለሽያጭ የቀረብሽው መቼ ነው ለማለት አይደለም።*

«ገላዬን የሚያሞቀው ሳገኝ!» *የፍቅር እሳቱን የለኮሰብኝ ሳገኝ* አለችው።

{ቋንቋ በቋንቋ ከመተርጎም ይልቅ ደራሲው በቀጥታ በአማርኛ አባባል ታሪኩን ይገልፀዋል።}

«ይህችን ይወዳል ጦራ! እንዴት ብለሽ?»

«ኳንዳሻኝ ብዩ! አጨሽኝ እንጂ አላገባኸኝ! ምን ሊውጥህ?» ስትል ተውገረገረችበት። ስጦታዋን ከማን እንዳገኘች አልጠየቀም። የሰጣት ወንድ እንደተበጠሰበት ሲያውቅ ይመጣል በሚል እምነት በንዴት ጨሌውን ከአንገቷ ላይ በጥሶ ጣለው። አትላን ዕንባዋን እየዘራች ወደ ወላጆቿ ዘንድ በረረች።

«አጭቶሻል፣ ይወድሻል፣ ሰርጋችሁ ደርሷል፤ ወንድ ልጅ ነው። ያስ ቢሆን እስካሁን ዝም ብሎ ከርሞ አሁን ምን ሲደረግ ይደፍርሻል?» አሉ አባቷ አቶ ጊፊቾ ለጦራ በማድላት። እናትዋ በባላቸው አነጋገር አልተደሰቱም። «ፍቅር ጊዜ አይመርጥም እኮ!» አሉ ወይዘሮ ኢሉ።

«ሴት ያመጣችው ችግር ሴት አትፈታውም። አሁን ችግር ማምጣቷ ለምንድነው?»

«ሴት ልጅ ካላደባደበች፣ ካላፋናከተችና ካላዳማችማ ምን ክብር አላት!?» አሉ ወይዘሮ ኢሉ የወጣትነት ጊዜአቸው ትዝታ በሽውታ በህሊናቸው ውስጥ እንደ ጉም እየተተነተነ። ይህም የአቶ ጊፊቾ ትዝታንም ቀስቀሰባቸው። ወይዘሮ ኢሉን እንዲሁ በከንቱ አላገኟቸውም። የተገጣጠበ አካላቸው ወንድነታቸውን ያሳወቁበትና በአዛውንት ዕድሜአቸው ደግሞ ያስከበራቸው እንደሆነ አላጡትም። ግን አሁን ዕድሜአቸው እየገፋ ሲሄድ በጎልማሳነት ጊዜአቸው ያልተሰማቸው ጉዳት እየበረታባቸው መሆኑን እየተረዱት መጥተዋል። ይህንን ደንብና ስርዓት የጠሉት ቢሆኑም በህብረተሰቡ ያስገኘላቸውን ክብርና ስም እንዳያዋድቅባቸው ውስጣቸው አፍነውት ተቀምጠዋል።

«ሴት ልጅ ስታለቅስ ደግ አይደለም። የሴት ልጅ ዕንባ ደም ያፋስሳል።»

«ጣሳ ነዋ! ካሳ! የሴት ዕንባ እንዲሁ ፈስሶ አይቀርː ይሄ ሁሉ ገና ለገና አጨኋት ብሎ እኮ ነው።»

«ምነው ጦራን የምትወጂው አልነበርሽም?»

«ወንድነቱን እጠራጠራለሁ።»

«ለመሆኑ ማን እንደሰጠሽ ጠይቆሻል?» ብለው አትላንን ጠየቋት አባቷ አቶ ጊፌቾ።

‹‹እኔ አልነገርኩትም፣ ጠንክሮም አልጠየቀኝም፤ ብቻ ጨሌውን ካንገቴ ላይ ብጥስ አድርጎ ጣለብኝ።» ስትል አትላን በዕንባዋ እየታጠበች መለሰችላቸው።

«ምርጫሽ ማንን ነው?» አባቷ ነበሩ የጠየቋት።

«ምርጫሽ ማንን ነው? ጉድ አፈሉ እርስዎ ዘንድሮ! ዕውነትም እየጃጁ መጥተዋል ልበል? ምርጫዋ ባይሆን ስጦታውን መቼ ትቀበለው ነበር? ያውም ታጭታ! ለመሆኑ ማነው እሱ?»

«ደንቢ ነው ስትል።» ስል መለሰች ለእናቷ።

«ደንቢ!» በቁጣ ነበር። «ምነው ልጄ ምን ትንሽ አስወደደሽ? ምን አለውና ምን ሊጥልልሽ?» አትላን ትታቸው ወደውጪ ሮጠች። እንደተለመደው ወደ ጓሮዋ ሄዳ ድንጋይ ለድንጋይ እያፋጨች ትተክዛለች። አባቷ ባለቤታቸውን ወይዘሮ ኢሉን የሀሳብ ቅብጥብጥነታቸውን በሚተች አስተያየት ገላምጠዋቸው ወደ ደጅ ወጡ። ጦራ የሰጣቸው ፍየሎች ከሌሎች የቀንድ ከብቶች ጋር ወደ በረታቸው እየተነዱ ይገቡ ነበር።

***

ጌሾ ሳይገባበት ማሽላና በቆሎ ተፈጭቶና ተገንፍቶ መሬት ውስጥ ከቀበሩት በኋላ በአምስተኛ ቀኑ ተከፍቶ ከድፍድፉ እየተቆነጠረ ለብ ባለ ውኃ ተበጥብጦ የሚጠጣውን ቦርዴ በያዘው ቅል ደጋግሞ እየሞላ በንዴት በተከተፈ ጉሮሮው ይለቅቀው ነበር፤ ጦራ፣ የጨሰ አንጀቱን የሚያበርድለት ይመስል። ጅማት ስሮቹ ሳይቀሩ ከለገዳዲ እንደተዘረጋ ቧንቧ ከፊቱ ሁሉ ይነበቡ ነበር። ቅናት ናላውን አዙሮታል።

ደንቢ የጦራን አድራጎት ሲሰማ አትላንን በማፅናናት ሌላ ጨሌ በመግዛት ተካላት። እሷ ግን እንቢ አልቀበልም ብላ ድርቅ አለች። ደንቢ ጦራ አብዶ ከንፎ እንዲመጣና ዶንጋ ‹ምክቶሽ› እንግጠም እንዲለው በንቀት ነበር ችላ ያለው። አትላን ግን የፍርሃት ነው የመሰላት። ደግሞ ወንዶች የእሷን ውበት አይተው አለመተራከክ ክብሯን የቀነሰበት አድርጋ አይታዋለች።

«ምን ሊሰራልኝ ትሰጠኛለህ? በሌላ ወንድ ክብሩን ሊያጣ።»

«ክብር የሚጠብቀው ክብር ስትሰጪው ነው። ክብር ስትሰጪው ደግሞ ዓለም እኔን እንደመረጥሽኝ ይረዳል።»

«አትፈላስፍብኝ»

«መጀመሪያ የረገፈው ድሪ የኔ ክብር ነው። አይቆረቁረኝም። ይሄ ግን ያንቺ ክብር ነው። ክብርሽን እሰሪ። ክብርሽን የነካ ክብሩን ያጣል። ክብርሽ በደሜ ይጠበቃል።» ብሎ አሰረላት።

ፈገግታ ፊቷ ላይ አይነበብም። ደንቢ ሽለብታ የያዘው ህፃን እንደሚያስተኛ ሰው ቀስ ብሎ መሬት ላይ አጋደማት። አጠገቧ ከተንበረከከበት እግሮቿን ዘርግቶ የቆዳ ግልድሟን ሰበሰበ። እሷም የዝናር ቀለህ ትጥቅ አጥርነቱን አፈረሰችለት። ልዩ ስሜት እስኪሰማት ድረስ ተዋሃደችው።

***

ወይዘሮ ኢሉ በልጃቸው ስም ዶንጋ መጋጠሙን በጣም ነበር የፈለጉት። ውብ ልጃቸው አገሩን ብታፋጅላቸው ደስ ባላቸው ነበር። «ሁለት ፈሪ ወንዶች እንዴት በኛ ጎሳ ይፈጠራል? ሱሪ የታጠቀ የወለደው እንኳን ልብ አለው። ወኔ ቢሶች!» እያሉ መነጫነጭ ጀምረዋል። ግጥሚያውም ሳይቀር ጦራም ሳይሸነፍ ልጃቸውን ለመዳር ቢችሉ የኮሩ የቤት እመቤትና እናት ይሆኑ ነበር።

ጦራ አትላን በድጋሚ ሌላ ጨሌ አንገቷ ላይ አስራ አገኛት። «ነፋስ ከጠላት ድንበር አልነፍስ አለ። በድን ላይ ነው ልብሽ የወደቀው!» አላት ለማናደድ ብሎ።

«ደንቢ ሙት አይደለም።» አለችው ንዴት እንደያዛት።

«ሬሳው ላይ ጨሌ ይበተናል!» ጨሌዋን ከላይዋ እንደበጠሰ ሲሮጥ ከደንቢ ጎጥ ሄደ። ይህ ወሬ ከወይዘሮ ኢሉ ጆሮ ሲገባ «ልጄ ወግ ደረሳት» ብለው እልል አሉ።

ጦራ ከደንቢ ቤት ሲደርስ መፎከር ጀመረ። ና ዶንጋ ግጠመኝ ብሎ ጋበዘው። ደንቢ ከየት መጣህብኝ? እንዴት ደረስክብኝ? ብሎ ደነፋ። ረዥም ዱላውን ይዞ ወጣ። የአካባቢው አዛውንት መሃከላቸው ለግልግል ባይገቡ ይጠብቅ የነበረው ነገር ስለነበር ነርቶ ሊለቅቀው ልቡ መተንፈሻ አጥቶ ነበር።

«ልክ አይደለም አንተ! ውሻ የምታባርር መስለህ ባዶ እጁን የመጣን ሰው እንዴት በዱላ ትገጥማለህ? ወይስ የፍራት ነው?» ብለው ተቆጡ አቶ ቶራኸ።

የፍርሃትስ አልነበረም። እንደ ዱላ ድብደባ አንጀት የሚያርስ አይኖርም። ደበኛ መመከት አቅቶት ዱላው ሲያርፍበትና ሲቅሽመደመድ መሬቷም እንኳን አትቀበለውም። የረገጣትን ስፍራ ሁሉ ነፋስ መጥቶ በጠረገልኝ ብላ ትመኛለች። አሸናፊን ወድዳ ደካማን በመጥላት።

***

ከሁለቱም ወገን በዕድሜ ከገፉት ለሽምግልናና ለዳኝነት ከተመረጡ በኋላ ጊዜና ቦታ ተወሰነ። በተባለውም ወቅት ደንቢ በከፍተኛ ወኔ ቀስቃሽ ዜማዎችና ጭፈራ እየታጀበ ከቦታው ሲደርስ ጦራ አልመጣም ነበር። አጃቢዎቹም የማንኳሸሻ ዜማቸውን እንደፉከራ እየቃጣቸው ይሉት ጀመር።

*የፈሪ ሽንታም፣*
*የፈሪ በድን፣*
*ወድቆ ቀሪ ነው፣*
*ሞቶም አያሳዝን።*

ግጥሚያው የሚደረግበት ስፍራ በተመልካቾች ተከብቦ ይጠበቅ ነበር። ሴቶቹም ፈንጠር ብለው ሊመለከቱ ተዘጋጅተዋል። አትላንም በሚያደንቋት የሴት ጓደኞቿ ተከብባ ትርዒቱን ለማየት ትጠባበቅ ነበር። ጦራ ብቅም አላለ። አትላን አንጀቷ ቁስል፣ እርር አለባት። እንዲያው ከማይወዳትና ከማይፋለምላት ወንድ ጋር ተጋብታ ልትኖር ነበር። በሱ መታጪቷ ሲታሰባት ማልቀስ አማራት። ጠባሳና ስብራት የሌለውና ከወንድ የማይቆጠር የሀገር መሳቂያ ጋር እንዴት ልትኖር ነበር? እንዲያው ሌላ ጊዜ ቢያገጣጥማት ራሷ እያሳደደች ብትነርተው አንጀቷ እንዴት እንደሚርስ በሃሳብ ታያት። ባህሉ የማይፈቅድላት ሆኖ ነው እንጂ ለዶንጋ ልትጋብዘውም ሽቷት ነበር። አገር ጥሎ ካልጠፋ ወይንም ካልሞተ ደብቃ በምታስቀምጠው ዱላ በአደባባይ አደባይታ ልታሳፍረው ልቧ አደመበት። *ዋሴትን ከብር አስወቃሽ! ፈሪ፣ አሰዳቢ፣ ወኔ ቢስ፣ ...ሱሪ ከሚታጠቁት የማይሻል።* በማለት በሀሳብ አዋደቀችው። የስሟ መሞገሻ ቀኑን አሰናክሉባት እሱ እዚች ምድር ላይ በህይወት መገኘት አይገባውም።

***

ጦራ በላብ እንደተነከረ ከእንቅልፉ ባንኖ ተነሳ። በጎጆው ወጋግራ ከምትገባው የጨረቃ ብርሃን ሌላ ምንም ነገር አይታይም። በድንጋጤም ልቡን ጭብጥ አድርጎ ያዙኝ ልቀቁኝ ከሚል ሩጫው ሊያስታግሰው ሞከረ። ከላ ከላይም ይተንፍሳል። ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ እንደገና ከመደቡ ላይ ጋደም አለ። ስጋቱና ሃሳቡ በሰመመን እየተሸሸጉ ሄደው እንቅልፍ አሸለበው።

*“ጓዴ! በል እንግዲህ የጀመርነውን እንጨርስ። ታዲያስ ጓዴ! እንዴት ነው? በርታ፣ በል እንጂ ጓዴ። አይዞህ ጓዴ! ና ና ተከተለኝ። ከዚያ ከሜዳው ላይ ይሻለናል ጓዴ!”* ጣረ–ሞት የሞት ጥሩርን እንደታጠቀ በፍየል ቀንዱ እሳት እየተፋና በዝሆን ጆሮው ላይ የገዳይነት ምልክቱን ሎቲ እንዳንጠለጠለ ደም የለበሱ ዐይኖቹንና እንደዱር የገጠጡ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገበት ሊያግባባው ሞከረ። ጦራ ፍራቱን አልደበቀም። ከሞት ጋር ዝምድናን ሆነ ወዳጅነት አይፈልግም። በዐይኖቹ ቀዳዳዎች ዙሪያ በሰባት ጦሮች ተከብቦ ነበልባል የሚተፋውን የፊት መሸፈኛውን አጥልቆ ከዝንጀሮ ቆዳና ከአንበሳ ጭራ የተሰራ የገዳይነት ልብሱን ለብሶ እንዲርቀው አስፈራራው። ጣረ–ሞትን። ሞት ሞትን ሲያይ እንዲፈራ!

ጣረ–ሞት ከስርጉድ ዐይኖቹ ውስጥ መቅሰፍት የሆነበትን ነበልባል በሰባት ጦሮች ተከብቦ ሲመለከት ብርክ ያዘው። ጉልበቶቹ እንደቅቤ ቀለጡ። በፍርሃትም ምድሪቷን ያደባልቃት ጀመር። አካሉን ወደ ሽረሪት ቀይሮ ድሩን ከመሬት ላይ በማጣበቅ ድሩን እየተለተለ ጭልጥ ካለው ገደል ውስጥ ገብቶ ተሰወረ። መቀመቅ ወረደ። ህይወቱን ለማትረፍ። ሞት የሞትን ምስል አይቶ በመፍራት።

*ሃካስ ሞትም ህይወት አለውና! ሞት ሞትን ይፈራልና!! ዘራፍ ሞትን ገዳይ!! ዘራፍ የገዳይ ገዳይ!* እያለ ጦራ ከገደሉ አፋፍ ላይ የጦር ልብሱን በድል አድራጊነት አውልቆ በመዝናናት ሲፎክር ጣረ–ሞት ባለ ሰባ ክንድ ክንፎቹን አጥልቆ በአየር ውስጥ እያርገፈገፈ ከወረደበት መቀመቅ የሌሊት ወፍ ተመስሎ ድንገት ደረሰበት። የእግሩ ጥፍር ትልቅነት የጦርን ክንድ ያህል ነበር። በነዚያም ጣቶቹ አንስቶት እንደ አገዳ ከሁለት ላይ ሊሰብረው ሲል ህይወቱን ለማትረፍና የጦር ልብሱን ለመልበስ ጊዜ እንዲያገኝ ጦራ ተማፀነ።

*“ታላቁ ያለም ዳኛ! የሚቋቋምህና ወደር የሌለህ! በህይወት ውስጥ ተሰውረህ ለዘላለም የምትኖር! በቅፅበት ህይወትን እንደመጋረጃ ገልጠህ እንደጉድፍ የምትጥል ሆይ! ለመሬቷ አዝኜላት እንጂ ካንተ ጋር አልጨፍርም አላልኩም። ኃያሉ እግሮችህ መሬቱን ሲያረባይዱት ልቤ የማይችል ስለሆነ ነው። በቀስታና ዐይን የሚያስጨፍን ዜማ ካለህ እሺ እጨፍራለሁ።”* ብሎ እየተርበደበደ ተማፀነው።

*“ስራዬ ዐይን ማስጨፈን ነው።”* አለው ህይወትን ሲነጥቅ የዐይን ብርሃንም አብሮ መስለቡን ለመግለፅ።

*“ብሱ መልክ አላልኩም። እኛ ስንጨፍር ፊታችንን ሸፍነን ነው። ከፈለግህ የእኔን ልትጠቀምበት ትችላለህ።”*

*“ያ የሚያስፈራውን ነገርህን?”* አለው እየተርበተበተና እያማተበ።

*“እኔም እኮ ሌላው ላይ ሳየው እንደዚያ ነው የምፈራው። የተሰራውም ሌላውን ለማስፈራራት ነው። አንተም ብታደርገው ሌላውን ታስፈራራበታለህ እንጂ አንተን አይጎዳም።”*

እውነት ይሆናል ብሎ አሰበ። ልቡ ግን በፍርሃት ተሞልቷል። ያንን በድን የመሰለ የፊት ሽፋን ፊቱ ላይ ሊያደርግ ተጠራጠረ። በእግሩም ረገጥ አደረገው። ምንም አላደረገውም። ቀስ ብሎ አንስቶ እየፈራ እየቸረ ወደፊቱ አቀረበው። ከፍርሃቱ የተነሰ በአንድ እጁ ጦራን ትንፋሽ አሳጥቶ ነበር የጨበጠው። ጦራ ስቃዩን ደብቆ በፈገግታ ከወጥመዱ እስኪወድቅለት ተቻኩሏል። ጣረ–ሞትም የፊት ሽፋኑን ከፊቱ ላይ ሲያደርገው እንደ እሳት ተቃጠለ። በጩኸቱም አገሩን አደበላለቀው። ምድሪቱም ትርበደበድ ጀመር። የሞት ሞቱን ጦራን ሲለቅቀው ጀርባው ከመሬቱ ላይ ተቀንጥሶ እንደ ጠጠር ተበታተነ።

ጦራ እየሮከ ከቅዠቱ እንደገና ባነነ። የዛሬውን ዶንጋ መሰረዝ አለብኝ። መደበቅ አለብኝ ሲል ከራሱ ጋር ሙግት ገጠመ። በመጨረሻም መሰወሩን በመምረጥ ከግጥሚያው ቀረ።

ከዶንጋው ሜዳ ፉከራው፣ ዘፈኑ፣ ማን አለብኝ ባይነቱ ተጧጡፏል። የግጥሚያው ሰዓት አልፏል። ተጋጣሚውም፣ ተመልካቾቹም ሆነ ዳኞቹ ግራ በተጋባ ሁኔታ ትዕግስት አጥተዋል። የሁለቱም ተፋላሚ ወገን አዛውንቶች አጭር ምክክር አድርገው

ውሳኔ ላይ ደረሱ። ተጋጣሚው በወቅቱ ስላልተገኘ ምክንያቱ እስኪጣራ ድረስ ዶንጋው የተሰረዘ መሆኑን ለሁሉም አሳወቁ።

«ከወንዶች ሜዳ ያልተገኘ ሴት እንዴት ክብር ይሰጠዋል። ይሄ ለሱ ክብር ለኔ ውርደት ነው። ድሮስ ከፈሪ ጋር መግጠም ውርደት ነው።» ሲል ደንቢ ቁጣውን አስተጋባ።

«ታሞ ሊሆን ይችላል።» አሉ አቶ ቶራኸ ደንቢን ከቁጣ ለማብረድ።

«በፍርሃት ሞቶ ነው! ሙትቻ እሱን ብሎ ወንድ!»

«ምክንያቱን አጣርተን በተስማሚ ቀን እንዲሆን እናደርጋለን።»

«ተጠርቶ ይምጣ!» አለ ደንቢ አቶ ቶራኸን አቋርጧቸው። «ይህንን ዕድል እሰጠዋለሁ። አልያም ካለበት ሄጄ ይዋጣልናል!»

«እኛ ሽማግሌዎች ነን። እንደወጣትነት ጊዜአችን አንሮጥም። ባይሆን ይላከበትና ሁኔታው ይታወቅ።» ሲሉ አቶ አሊቋ ድምፃቸው ለመጀመሪያ ጊዜ አሰሙ። አቶ ቶራኸን በክፉ ዐይኖቿ ታያቸው የነበረችው አትላን አቶ አሊቋ ባሉት በመስማማት በወዳጅነት ዐይን አየቻቸው። ገና ውሳኔ ላይ ሳይደረስ የደንቢ አጫፋሪዎች ሆ! ብለው ጦራን ለማደን በህብረት ተሰማሩ። ከቤቱ ጀምረው መንደሩን፣ ደኑን፣ ገደሉን አዳረሱ። ይኖራል ብለው ከገመቱበት ስፍራዎች አጥተውት መርዶውን ለአዛውንቱ ለመንገር በትንሽ ደን ውስጥ ሲያቋርጡ ከዛፍ ቅርንጫፍ ተቀምጦ ያገኙታል። ገሚሱ ዛፉን እያወዛወዘ እንደ ትርንጎ ፍሬ ሊጥለው ሲሞክር ሌሎቹ እንደ ዝንጀሮ እየዘለሉ ሲመጡበት ከዛፍ ዛፍ እየዘለለ ደኑን አቋርጦ ጨረሰ። ከመጨረሻው ዛፍ ላይ ሲደርስ ዘልሎ በመውረድ ከሜዳው ሩጫውን ተያያዘው። መሬት ላይ የነበሩት ከዛፍ ዛፍ እየተሽሎከሎኩ ደርሰውበት ስለነበር ከጣረ–ሞት ጋር በህልሙ ከተፋለመበት የገደል አፋፍ ዳር ደረሰ። አዳኞቹ እየቀረቡት በመጡ ቁጥር ወደ ገደሉ ወደኋላው ማፈግፈጉን ያዘ።

ፈሪ ተብሎ ለመኖር መንፈሱን አጠንክሮ ወስኖ ነበር። አሁን ግን የገደል አፋፍ ላይ ተረከዙ እየተንሸራተተ ነው። የግብረ–ሞት ጭፍረኞችም ጉዞውን ለማፋጠን እየተጋፉት ናቸው። የመጡበት የተቃዋሚ ጭፍረኞች ስለህይወቱ ደንታ የላቸውም። ወኔ ኖሮት ከአፋፍ ላይ እንደማይዘል ገምተዋል። በህይወት ከያዙት ውርደቱን ከሚከናነብበት ሜዳ በያዙት መረብ ጠፍረው ይዘው ያደርሱታል። የገደል ጉዞውን ከመረጠም ቦታው የፈሪ ገደል ተብሎ ተሰይሞበት ሲተረትበትና በዘፈን ሲዋረድበት ይኖራል። በድኑ፣ አፅሙ፣ መንፈሱ ለዘለዓለም፣ በውርደት።

ጦራ ከመቃብሩ አፋፍ ላይ መቆሙ ታወቀው። የመኖር ፍላጎቱ፣ በአሸናፊነት የመወጣት መንፈሱ እሱነቱን የማስመስከሩ ፍላጎትና የጠላቶቹን ውርደት መረጠ። ሳያስቡትም በመሃላቸው ጥሶ እንደደነበረ በሬ የሚደርስበት ጠፋ።

ከመጋጠሚያው ሜዳ አዛውንቱ ይህ ሁኔታ አገር የሚያናጋና ከባድ ልዩነትንና ብጥብጥን የሚፈጥር ሆኖ ስላገኙት በሁለቱ ተፋላሚዎች መካከል እንዲያልቅ ተመልካቹን አረጋግተው ይጠብቁ ነበር። ጦራ ከሩቅ እየሮጠ ሲመጣ ሲያዩት አስጥሉኝ እንጂ ግጠመኝ ለማለት የመጣ አይመስልም።

አትላን ስታየው በጥላቻ ምራቋን ከመሬት ላይ ተፋች። ጦራ እንደደረሰ ደንቢ ሲያይ ድንፋታው በዛ። ሽማግሌዎቹ ድንገተኛ ግጥሚያ እንዳይፈጠር ብለው ደንቢን በሀገር ደንብ መሰረት አስጠንቅቀው እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን በዐይነ ቁራኛ ይጠባበቁ ጀመር።

ደንቢ የመከላከያ ልብሱን በሚገባ ለብሷል። ራሱን በአቡጀዲ ጠምጥሞ ከሰንበሌጥ የተሰራ ቆብ ደፍቶበታል። ደረቱን በሸማ ድግ አስሮ ከሽንጥ እስከ ዳሌው የአንበሳ ቆዳ ታጥቋል። የአንበሳው ጅራት ከወደኋላው ስለሚውል ከመከላከያነት አልፎ የአንበሳ መልክ ሰጥቶታል። በቅልጥሞቹ ላይ ጠንካራ የቆዳ ገንባሌ ጠምጥሟል። የእጆቹ መጋጠሚያና አንጓ ላይ በጨርቅ ጠበቅ አድርጎ አስሮታል።

በአንፃሩ ጦራ ዕርቃኑን ነበር የቀረበው። ዱላውንም እንኳን አላሰናዳም ነበር። ሽማግሌዎቹ ለመጋጠም ፈቃደኛነቱን ጠይቀው ትጥቅ እንዲኖረው ሲሞክሩ የጠየቃቸው በትር ብቻ ነበር። ደንቢ እየተቁነጠነጠና እየፎከረ ይጠብቃል። ስርአት አስከባሪዎችና አጫዋቹ ሽማግሌ ወደ ሜዳው መሀከል ገቡ። አጫዋቹ አቶ አሊቋ ልምጭ ይዘው ዶንጋው እንዲጀመር ምልክት ሰጡ።

የረገጡት መሬት አቧራውን በአየር ውስጥ ወደ ሰማይ ሲተፋው ነፋሱ ተቀብሎ በአየር ውስጥ እያጥመዘመዘ ወደየአቅጣጫው ያቦነው ነበር። በሁለት እጆች ተጨብጦ የተሰነዘረው በትር ከመካቹ በትር ጋር ሲጋጭ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ድምፅ እያሰማ በፀሀይ ብርሃን የተዋጠ እሳት ይረጭ ነበር። እያንዳንዱ በትር ሲሰነዘር ለጥቃት፣ እያንዳንዱን ጥቃት ሲመክቱ ህይወትን ለማዳን የሚደረግ ጥረት ነበር።

ለአናቱ የተሰነዘረውን በትር ጦራ እከላከላለሁ ብሎ ያደረገው ሙከራ ጭብጥ እጁን ስላገኘው የበትሩ ኃይል ከትከሻው ጀምሮ በቁመቱ ቆዳውን ቢላዋ እንደበላው የድንች ቆዳ ገሽልጦት ወረደ። ከሰል የመሰለው ቆዳው ወተት የመሰለ መስመር አወጣ። በዚህም በተቀየሰለት ቦይ ደሙ ግድቡን እንደጣሰ ድንገተኛ ውሃ ይኾጎደጎድ ጀመር። መከላከያ ባለማጥለቁ ጉዳት ደርሶበት ከመሬት ላይ በህመም እንደታየዘ ወደቀ። ተጋጣሚ መሬት ላይ ከወደቀ መምታት ደንብ ባይሆንም ደንቢ ጡንቻውን አጠንክሮ ዱላውን ከጦራ ግንባር ላይ እንደመጥረቢያ ሊሰካበት ተዘጋጀ። በስቃይ ያለው ጦራ ማምለጫ መንገድ የለውም። በመሀከል ገብቶ የሚመክትለት ካልመጣ ወይንም የግጥሚያው ስርዓት ካልተከበረ ከወደቀበት እንደ እባብ ሊቀጠቀጥ ነው።

ደንቢ አመታቱን በማስተካከል አንድ እግሩን ከጦራ ጭን ውስጥ ከተተ። ጦራም የደንቢን አሰነዛዘር ፍጥነት በሚገባ ለከቶ አመጣጡን በጥንቃቄ ጀመር። የደንቢ በትር ለፈለጣ አንዲት ጭብጥ ሲቀራት ጦራ አካሉን መሬት ለመሬት አንከባለለው። በዚያ ወቅት የደንቢን እግር ከቋንጃው ላይ መትቶ ስለጠለፈው

በአየር ላይ ተጉኖ ከመሬቱ ላይ ተዘረጋ። የደንቢ በትር ከጦራ እጅ ስለገባ በደረሰበት ህመም እየተሰቃየ ባለ ጉልበቱ ከደንቢ አናት ላይ አሳረፈው። በጠለፋ ጥሉ በቅፅበት ተነስቶ ተጋጣሚን ማጥቃት ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ በመሆኑ ተመልካቹና ዳኞቹ በመሳቀቅና በማድነቅ ነበር የተመለከቱት። የደንቢ ደም፣ የአትላን ዕንባና የወገን ዋይታ አገሩን በሀዘን አጥለቀለቀው። የአትላን ዕድል ጦራ ነፍስ እንዲያጠፋ አደረገው።

***

የደንቢ በዶንጋ መሸነፍ ብቻ ሳይሆን በግጥሚያው ላይ መሞቱ አትላን ከፋኛ ሀዘን ውስጥ ጥሏታል። ጦራ ከመሬት ላይ የወደቀ ተጋጣሚውን መምታቱ ሳያንስ በእጁ የሰው ህይወት ስላጠፋ ተጠያቂ አደረገው። አትላን ብቻ አልነበረችም አጥብቃ ያዘነችበት። ኩሪያም አዝናበታለች። በጣም የምትወደውን ወንድሟን ነበር የገደለባት።

የደንቢን መሞት ጦራ እንዳረጋገጠ ሸሽቶ አመለጠ። ስውር መድኃኒት ወስዶ ነው የሞትን ኃይል የተቆጣጠረው ተብሎ ተጠረጠረ። የሟች ወገኖችም በኀብረት የገዳዩን ንብረት በሙሉ ዘርፈው ቤቱን አቃጠሉበት። በዚህ ሁኔታ ስለሞተባቸውም ቤተሰቦቹ ደንቢን ሊቀብሩት አልቻሉም።

ሉቃሮ ሀብት ንብረት ወይንም እህት ስለሌለው ሚስት ለማግኘት ሳይችል ቀርቶ ቆሞ-ቀር በመሆን ዕድሜውን የገፋ ነው። ይህ አስቃቂ አጋጣሚ በተዓምር ነበር የመጣለት? ወይንስ ፀሎቱን የሚሰማ እግዚአብሄር ተገኝቶ ነው? አሁን የምርምር ጊዜ አይደለም፤ የስራ ነው። የሩጫ፣ የእሽቅድምድም። ሌላው የእሱ ቢጤ እንዲቀድመው አይፈልግም። በተቻለው ፍጥነት የደንቢን በድን ለመቅበር ተዘጋጀ። የደንቢን ሬሳ በእንቁጢጥ አሰረው። ሦስት ቀናት ጠብቆም ክብ ሆኖ በቆፈረው መቃብር ውስጥ ቀበረው።

በዚህ አድራጎቱ የደንቢ ወላጆች በደንቡ መሠረት ኩሪያን ለሉቃሮ ሸለሙለት። የእናንተን መከራ ቀብሬአለሁና እኔም ከዚሁ የነፃሁ እንድሆን እጄን በደም የምታጠብበት ከብት ስጡኝ ብሎ ጠየቃቸው። የሟቹ ቤተሰቦችም ፍየል ሰጡት። ፍየሉንም አርዶ እጁን በደም ታጠበ። የዚህ ዓይነት መከራ እንዳይደርስበት በመመኘት ፈርሱን በገበቴ አቅርቦ እግሩንም ግንባሩንም ተቀባው። በከርስ-መቃብሩ ዙሪያ እየዞረና በላዩም ላይ እየጨፈረ አዜመ። ከዚህም ሂደት በኋላ ያረደውን ፍየል በላ።

ሉቃሮና ኩሪያ ሲጋቡም ሥነ-ስርዓቱ የተካሄደው በእሱ ቤት ውስጥ ነበር። ቤተዘመድ በሙሉ ተሰብስቧል። ራሳቸው በትንሽ ደላጎ መሳይ ነገር ተሸፍኖ በተዘጋጀላቸው ቆዳ ላይ ሁለቱም ተቀምጠዋል። የጋብቻውን ስርዓት ለማስፈፀም ከዘመድ መሀከል በእድሜ ገፋ ያሉት አንዲት ባልቴትና አንድ ሽማግሌ ተመርጠዋል።

ባልቴቷ ሉቃሮን ሽማግሌው ኩሪያን በደንብ አሳምረው ይገርፏቸው ጀመር። ይህም የምርቃት ግርፊያ ከጋብቻ በፊት ለፈፀሙት ድርጊት ይቅርታ የሚያስገኝላቸውና ከትዳር በኋላም ወልደውና ከብደው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ነው። ዱላው እየባሰባቸው ሄደ። ምንም እንኳን ሉቃሮን በባልቴት ቢገረፍም ስልት ባለው አመታታቸው አንገብግበውት ነበር። ደግሞስ ባልቀኔው ፀጋዬ ገብረመድኅን ‹ወንድ ልጅ ብቻውን ነው የሚያለቅሰው› እንዳለው ከኩሪያ ቀድሞ በቃኝ ማለት ክብሩን ስለሚያዋድቅበት እንደምንም ቻለው።

ኩሪያን ግርፋቱ ሲብስባት ወደተዘጋጀላቸው ልዩ ክፍል ተነስታ በረረች። ባልቴቷም ተከትለዋት ገቡ። በነጭ ጭቃ የተለወሰ የለጋ ቅል ፍሬ አካላቷን እየቀቡ ‹ሆንቡሯ ነሽና ብዙ ፍሬ ለመስጠት ያብቃሽ› ብለው መረቋት። ከህፃንነት ጊዜዋ ጀምራ ሃፍረተ-ስጋዋን የሸፈነችበትን በጠፍር የተያያዙትን ቀለሆች ከዳሌዋ ላይ ፈቱላት። ብር-አምባሯ ተሰበረ! ልጃገረድነቷ ቀረ! ከእንግዲህ ወዲያ የቤት እመቤት ሆነች።

ሉቃሮ ትንሽ የፍየል ቆዳ በሽንጡ አካባቢ ጣል አድርጎና ረዥም ነጭ በትር ይዞ በየስፍራው ሲዘዋወር ከረመ። ለአንድ ወር ሙሉ ኩሩ ተመልካች እንጂ በዶንጋ ጨዋታ አልተሳተፈም። ወሩ እንዳለቀ የፍየል ቆዳውን ጥሎ ሴቶችን ማሽኮርመሙን ቀጠለ። ዶንጋ ባለበት ሁሉ የዱላ ምክቶሽ ችሎታውን ለማሳየት ይተራከክ ጀመረ። ጠረኗ እየጋበዘ የሰማያት የመሰለ ቅርጿ ልቡን የምትጋብዝ ወጣት ስላየ ለጥሎሽ የሚሆኑ የቀንድ ከብቶች ለማግኘትም ተግቶ ይሰራ ጀመር። በድብቅ እየተከተላትም ያጠናት ጀምሯል።

ሉቃሮ የታዳጊቷን ውበት እያደነቀና ሁለተኛ ሚስቱ ለማድረግ እያሰበ ተቀምጦ በድብቅ ከሚያይበት ስፍራ ከኋላው ኮሽታ ይሰማና ዘወር ይላል። ጦራ እንደ ስልክ እንጨት ረዝሞና ቀጥ ብሎ ታየው። ድንጋጤም ሰውነቱን ወረረው። ጣረ-ሞት ከንፋን ዘርግቶ የመጣበትም መሰለው። *‹መርዘኛ ነው፣ መድኃኒተኛ ነው፣ የምት ጉደኛ ነው፣ ...›* ያልተሰጠው ስም አልነበረም፣ ለጦራ።

በድንገተኛ የፍልሚያ ስልቱና በጨካኝነቱ ስሙ ገንኗል። መድኃኒት ወስዶ ራሱን ያልተከላከለ ዕርቃኑን ከእሱ ፊት የቀረበ ሁሉ እሳት የተወው አመድ መሆኑ እየተጋነነ ተወርቷል። በድንገት ቢያዩት እንኳን በርቀት እያማተቡ መሰወር ነበር ጊዜአዊ መፍትሄ ይሆናል ብሎ አገር የመከረው። የሟች ቤተሰቦች ሌት ከቀን በሰቀቀን መኖር ጀምረዋል። ንብረቱን ስላቃጠልንበት ድንገት መጥቶ ይበቀላል የሚል ፍርሃት ተሰምቷቸዋል። ከግቢያቸው በር ላይ የከብት ግንባር ሰቅለውና የቤታቸውን ዙሪያ በፈርስ፣ በሮቻቸውን በደም ቀብተው ያረዱትን ከብት ልብ ከጎጆአቸው አውታር ላይ በሲባጎ አስረዋል። የጦራን ኃይል ለማርከስ። መንፈሱን ለማድከምና ብቀላውን እንዲረሳ።

ጦራ ሉቃሮን የሚያህል የዶንጋ ጀግና እሱን አይቶ ሲበረግግ ያለግጥሚያ አሸናፊ በመሆኑ ደስ አለው። ለልመና ሲያድነው እንዳልከረመ ያህል በሙሉ ልብ ተባባሪነቱን ሊጠይቅ ወሰነ።

"ሉቃሮ፣ ምድር እንጂ ሰማይ አይከድም። የረገጡት እንጂ የበረሩበት ምን ይከፋል ብለህ ነው" አለው መሬቱንና ሰማዩን እያሳየው። በቅኔ አባባሉ *ሰማይ ሁነህልኝ በነፃነት ልብረር፤ ልኑር።* እንደመሬት ከጂ አትሁነኝ ማለቱ ነበር፤ በማስጠንቀቅ መልክ። ሉቃሮ ተነስቶ እጅ ነሳው። ፍርሃቱ ግን አልለቀቀውም።

"የረጋ መሬት ቢረግጡት ግርማ ነው የሚሰጠው።" ሲል ሉቃሮ ተባባሪትን ገለፀለት።

"ፍጠን፣ አጣራልኝ፤ መልክቴን መጀመሪያ

ለአትላን ቤተሰቦች ቀጥሎም ለደንቢ ቤተሰቦች አድርስልኝ። እርቅና ሰላም ለሁላችንም ይበጀናልና የሟች ወገኖች ለጥሎሽ የሰጠሁትን ከብቶች ይውሰዱ። አንስም ካሉ ያቃጠላችሁትና ያወደማችሁት ንብረቴ ቀላል አይደለም ብለህ አስማማልኝ። ይህ ጉዳይ እስኪፈፀም ድረስ ጥላ ነኝ። እየ ታየሁ እሰለባለሁ።»

«እሰለባለሁ» የሚለው ቃል የቃሮን ልብ እንደ ማዕበል መታው። እውነትም ይሄ ልዩ ኃይል የተጎናፈፀ ልዩ መድኃኒት በምስጢር የቀመሰ ነው ብሎ አመነ። አነጋገሩ ሁሉ የሚያስፈራ ኃይል አለው።

***

ጦራ እህት ቢኖረው ኖሮ ለጥሎሽ ሰጥቷት ትዳር ይመሰርት ነበር። ወይንም ላደረሰው አደጋ በካሳ ሰጥቷት ነፃ መሆንና እርቅ መፍጠርም ይቻለው ነበር። ብቻውን ነው የተፈጠረው። ለጥሎሽ የሰጠውን ከብቶች ለእርቅ ለመክፈል መወሰኑንም እህቱን ለካሳም ሆነ ለጥሎሽ ቢሰጥ የተሰጣቸው ቤተሰቦች በተራቸው ጥሎሽ ሊቀበሉባት ስለሚችሉ ነው። በተዘዋዋሪ ወይንም በእቋራጭ የሚፈልጉትን ስለሚያገኙ ተስፋ ጥሎ መልሱን ይጠባበቅ ጀመር።

ሎቃሮ ለሦስቱም ወገን መልዕክት እያመላለሰ መፍትሄ ይሆናል የሚለውንም እየጠቆመ ለእርቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረጉ በጦራ ዘንድ መውደድን አተረፈለት።

«ወዳጄ ሎቃሮ!» አለ ጦራ የደንቢን ቤተሰቦች የደም ካሳው በቂ አይደለም ብለው ማንገራገራቸው ጭንቀት ስለፈጠረበት። «ያጠፉት ንብረቴ በበቀል የወሰዱት ካሳ ነው። አሁን ልስጣችሁ ብዬ የእርቅ ካሳ መስጠቴ ሰላም ፈላጊ በመሆኔ ነው እንጂ ዱር ከወጣሁኝ ከርሜአለሁ። ከአራዊት ጋር ማደር ብዙ አስተምሮኛል። አውሬነት እያጠቃኝ መጥቷልና ጥላና አውሬ መሆን ለሰው ልጅ ጥሩ እንዳልሆነ አሳውቅልኝ። ካንተ ጋር ያለኝን ወዳጅነት የሚለውጠው ነገር ግን አይኖርም።» ብሎት በገደሉ ውስጥ ተሰወረበት።

***

እንደ እባብ እየተሳበና እንደ ጥንቸል እየዘለለ በተዘናጉበት ወቅት ከከብቶቻቸው አንዱን በነፍሱ እንዳለ ልቡን ብቻ ቆርጦ አውጥቶ ከበረንዳው ላይ ጣለባቸው። ይህም በአደንዛዥ ኃይሉ አፍዝዞን ከብቱን ሳይገድል ልቡን የሰረቀው ጦራን የሚመልሰው ኃይል አይኖርም ብለው በፍርሃት ተዋጡ። አገር በሙሉ ሰምቶ ጉድ አለ። ልቡን የተሰረቀው ከብት በረቱን አተራምሶና ጥሶ ከአጥሩ ላይ ተንጠልጥሎ መገኘትም ያላስደነገጠው ሰው አልነበረም። የደንቢ ቤተሰቦችም ወዲያውኑ ወደ ሎቃሮ ቤት ለመማጠን ሮጡ።

«እንቢ ብላችሁ ያመጣችሁት ችግር ነው። እኔ ምንም ልረዳችሁ አልችልም። በኋላ በኔ ላይ ቢዞርብኝስ?» ብሎ አሻፈረኝ አለ።

«እርቁን ብቻ ነው የምንፈልገው። የሱን ከብቶች አንፈልግም። እባክህ እርዳን።» ብለው ተለማመኑት።

«የምጠይቃችሁን ካደረጋችሁ እሞክራለሁ።» አለ ሎቃሮ ጥቂት ካሰበና ሁኔታዎች የተስተካከሉለት ሆኖ ስላገኘ።

«የጠየቅኸውን እናደርጋለን!» የደንቢ እናት ተስማሙ። ባላቸው ግን የሚመጣባቸው ግዴታ የሚያስጨንቃቸው መሆኑ ከፊታቸው ላይ ይነበባል።

«ለእርቅ የሚሰጣችሁን ከብቶች ወስዳችሁ ለኔ ትሰጡኛላችሁ።»

«ይሄማ እንዴት ይሆናል?» አባት ነበሩ የተቃወሙት።

«እርቅ መደረጉን እርሱ የሚያምነው እናንተ ካሳውን ስትቀበሉ ነው። ስለድካሜ ካሳችሁን ባማችነት በስጦታ ታስረክቡኛላችሁ። ይህም የስምምነቱን ከታብ ያስረዋል።» አላቸው በተረጋገጠ አባባል። ከሚደርስባቸው ጭንቀትና አደጋ ለመዳን በብርቱ ያሰቡበት ስለነበር የተባሉትን ወዲያውኑ አደረጉ። ሆኖም ሎቃሮ ጦራ ካለበት ስፍራ ቢመላለስ ሊያገኘው አልቻለም።

አንድ ምሽት ከበረት ውስጥ የገቡትንና ውጪ የቀሩትን ለመቁጠር ሲገባ ከጎኑ አንዳች ነገር ጎሸመው። የከብት ግፊ እንዳልሆነ ስላወቀ የሞት መንፈስ በላዩ ላይ ያንዣበበት መሰለው። ጦራ መሆኑን ሲያውቅ ትንሽ ረጋ አለ።

«ላገኝህ ፈልጌህ ነበር! ግን አልቻልኩም። እንዳልከው ከስምምነት ላይ ደርሰዋል። እንግዲህ የእርቅ ድግሱን ደግሰን ቦርዴአችንን እየለጠጥን እንጨፍራለን!» አለው። ማረጋገጫ መልስ እየተጠባበቀም «ለሰላም መልከተኛነቴ ወሮታ አማቾቼ አንተ የካስካቸውን ከብቶች ሰጥተውኛል። ከፈለግሃቸው ግን ያው ያንተው ናቸው። ቅሬታ አለህ?» ያጠናው ጀመር።

«ቅሬታ ቢኖረኝ ውይይት አያስፈልግም ነበር። አንተ የህይወት ወዳጄ ነህ።» ብሎ አቀፈው። ሎቃሮ ህይወቱ በጦራ እጅ መውደቁ ታወቀው። ጠላት ቢነሳበት ከሚከላከልለት ይልቅ ጠላቶቹ ሳይገድሉት በፊት እሱ ቀድሞ እንደሚገድለው አወቀ። የጓደኝነት ፍቅራቸውን የሚገልፁበት ባህላቸው ነውና።

***

ከሰላም እርቅ በኋላ ጦራ ልጃገረድ ለማጨት የተረፈ ሀብት ንብረት ስላልነበረው ጥሎሽ ለመጣል አልቻለም። ለሰው በመስራትም ከብቶች ለመግዛት ያለ ድካም መጣር ከጀመረ ጀምሮ የአየር ንብረት ለውጥ በዕድሉ ላይ ጠመመበት። ከፀሀይ ጋር ሊሊት ከቀን ጠብ ሆነ። አሳድዶ አላገኛት አለ። ጦር ሰብቆ ወርውሮ ሊያደማትና እንደ እንቁላል ሊያፈርጣት አልቻለም። ስቃ አቃጥላ፣ በደመና ተሸሽጋና ስልምልም ብላ መጥፋት ዕለታዊ ተግባሯ ሆነበት።

አከንባሎ የመሰለው ቅርጿ በጋራዎቹ መሀከል ሾልኮ ሲደበቅ የጨለማው መጋረጃ መከፈት ጀመረ። ደብዘዝ እያለ የሚሸሸው ብርሃን ወደ ድቅድቅ ጨለማነት እየተለወጠ መጣ። ከጦራ አዕምሮ ውስጥ ግን ፀሀይዋ አትጠፋም። ብሩህ ፊቷን እያሳየችው ስትስቅበት ቆሽቱ እያረረ ያያታል፣ ያስባታል። በልቡም ከእድሜሱ ላይ ተለጥፎ ከሚታየው ትልቁ ጋራ ላይ ወጥቶ በመጠበቅ እንደለመደችው አሽቆልቁላ ከገደሏ ልትገባ ስትል ግንባር ለግንባር ገጥሞ ሲያደባያት ታሰበው። የአዲስ ህይወት ምዕራፉን ለመክፈትም ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ።

# አዳምና ሔዋን

አዳምና ሔዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ። በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተዋጽኦችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## "ዕጣዬ"

### ከአብረኸት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብረኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበቿልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነውም ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

### ክፍል 16

በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ ቁምስቅል በሚያሳየው ውጣ ውረድ በበዛበት የአሜሪካ ኑሮ ላይ እርስ በእርስ የመናቆርና እንደጠላት የጎሪጥ የመተያየት አዝማሚያ ሲጨመርበት ምን ያህል አስመራሪ እንደሆነ መገንዘብ አያቅትም። እኔም ሆንኩ በተለይ ሰይፉ ወደ አሜሪካን የመጣነው በቅርብ ሆኖ ሳለና አገሩንና ኑሮውን ለመልመድ ጥረት በምናደርግበት ወቅት ይህ ችግር ሲጨመርበት ኑሮ ምን ያህል እንደሚያስጠላ ይታያችሁ።

የምፅዋ ከተማ መያዝ፣ ከዚያም የወያኔ ጦር ወደ አዲስ አበባ መገስገስ፣ የአዲስ አበባ መከበብ፣ ብሎም የመንግሥቱ መሸሽ ወዘተ እያደር እየተፈጠሩ የሄዱት ሁኔታዎች ውጪ አገር ባለን ኢትዮጵያውያን መካከል ብዙ ግራ የመጋባት ብሎም የመከፋፈል ሁኔታ መፈጠር ምክንያት መሆን ጀመሩ። ቀደም ሲል በነበረው የደርግ መንግሥት የግፍ አገዛዝ ምክንያት አገር ለቆ በስደት ወደ ጎረቤት አገሮች ከዚያም በኋላ ወደ አሜሪካና አውሮፓ የተበታተነውና ደርግ ላይ በነበረው የጥላቻ አቋም አንድ በነበረው ኢትዮጵያዊ መሃል የጎላ መከፋፈል እየተፈጠረና እየታየ ሄደ። ቀደም ሲል የነበረው መለስተኛ መለያየት በፖለቲካ አቋምና አመለካከት፣ ወይም በመስመር ልዩነት ነበር እንጂ እንዲህ እንዳሁኑ በዘር ላይ ያተኮረና የከረረ አልነበረም።

ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ፣ ሻዕቢያም አስመራን ሲይዝ እያደር እየከረረ የሄደው ክፍፍል ግሎ ይፋ ወጣ። በትግራይና በኤርትራ ተወላጆች ቤት ዳንኪራውና ዳንሱ ቀለጠ። በቀረው ኢትዮጵያዊ ቤት ደግሞ ሐዘንና ንዴት ይታይ ጀመር። ለረዥም ጊዜ በጓደኝነት ይተዋወቁና ይዋደዱ የነበሩ ሁሉ በዘር መለያየትና መከፋፈል ጀመሩ። በየቦታው ጎራ የለዩ ስብሰባዎች ይደረጉ ጀመር። በአንድ ወገን ወያኔንና ሻዕቢያን የሚደግፉ የትግራይና የኤርትራ ልጆች በሌላው ወገን ደግሞ የቀረው ኢትዮጵያዊ የየራሱን ስብሰባና ሰላማዊ ሰልፎች መደረግ ተጀመሩ። በሌሎች እስቴቶች የምንኖር ኢትዮጵያውያን አበሻ በብዛት በሚገኝበት ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች መከታተል ጀመርን። ሰልፉ፣ አድማው ወዘተ እየተጋጋለ መጣ። ሌሎች ኢትዮጵያውያን በትግራይና በኤርትራ ልጆች ባለቤትነት በሚካሄዱት የንግድ ድርጅቶች ላይ አድማ መምታት ጀመሩ። ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የነበረው አሥመራ ቡና ቤት በፊት ዘርና ወገን ሳይለዩ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በጠቅላላ የሚዝናኑበት ቦታ ነበር። በዚያን ወቅት ታዋቂዋ አርቲስት አስቴር አወቀ እዚያ ነበር የምትጫወተው። እና ምፅዋ በሻዕቢያ የተያዘ ዕለት ባለቤቱ ሻምፓኝ ከፈተና ፌስታ በፌስታ መሆኑ ሲታይ አድማ ተመታበት። አስቴርም አጃቢዎቿን ይዛ ደህና ሁኑ ብላ ትታ ወጣች ተባለ። ይህ የንግድ ድርጅት ታዋቂ እንዳልነበረና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያስደስት እንዳልነበረ ሁሉ ወዲያው ገበያው እልም ብሎ በመጥፋቱ ባለቤቱ ደምበኞቹን ለመመለስ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቢለጥፍ ምን ቢል አልሆንለት አለውና ከነጭራሹ ቤቱን ዘጋው ተባለ። ብዙም ነገር ተባለ። ይኸው የወያኔና የሻዕቢያ የፖለቲካ ጨዋታ እያንዳንዱን ቤት በማንኳኳት በባልና ሚስት መሐል እንኳ ችግር እየፈጠረ መምጣቱ በብዛት ይታይ ጀመር።

እኛ ባለንበት እስቴት የሆነውንና በቅርብ የማውቀውን ላጫውታችሁ። ባል ሆዬ ከጎንደር የመጣ አማራ ነው። ሚስት ደግሞ የትግራይ ያውም የአድዋ ልጅ ናት። አባቷ ግን ኤርትራዊ ነው ይባላል። ሁለቱ ተገናኝተው የተዋወቁት እዛው የችግሩ አገር ሱዳን ነው። በጣም ይዋደዳሉ። በ10 ዓመት አብሮ የመኖር የጋብቻ ጊዜያቸው ሁለት ሸግዬ ሸግዬ ልጆች ወልደዋል። እሱም እሷም ይሠራሉ። ልጆችም ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። በጣም የሚቀናባቸውና የሚወራላቸው ባልና ሚስት ነበሩ። እና ወያኔ አዲስ አበባ፣ ሻዕቢያ ደግሞ አሥመራ ሲገባ በመካከላቸው ነገር ተጀመረ። በመጀመሪያ አካባቢ ነገሩ ይህን ያህል አልተካረረም ነበር። ጎራ የለዩ ስብሰባዎች በየቦታው ሲካሄዱ ምንም የአገር ጉዳይ የሚሰማቸው ግለሰቦች ቢሆኑም ከመሄድና ከመሳተፍ ተቆጠቡ። በመሐሉ ቤት ውስጥ አንዳንድ ጽሑፎች መግባት ይጀምራሉ። ወያኔና ሻዕቢያን የሚያጥላላ ጽሑፍ ሲመጣ ሚስት ዓይኗ ደም ይለብሳል። ወያኔንና ሻዕቢያን የሚደግፍ ጽሑፍ ሲመጣ ደግሞ ባል ዓይኑ ደም ይለብሳል። ቀስ እያለም መጀመሪያ በጨዋታ መልክ ቀጥሎም በክርክር መልክ ጭቅጭቅ ይጀመራል። የቤት ውስጥ ክርክር አደባባይ ይወጣና ሁለቱም በየግላቸው የተለያዩ ስብሰባዎች መሄድ ይጀምራሉ። ሚስት ሆዬ ቀደም ሲል ያልታያት የአማራ ትምክህተኝነት እየታያት መጣና የወያኔና የሻዕቢያ ደጋፊዎች

ከሚያደርጉት ስብሰባ ሳታሰልስ መሄድ ጀመረች። ባልም በበኩሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሰባዎች መሄድ ጀመረ። እሷም የምታምንበትን በገንዘብ ስትረዳ እሱም የሚያምንበትን በገንዘብ ይረዳ ጀመር። ለ10 ዓመታት ደምቆና አምሮ ሲገነባ የነበረው የትዳር ኑሮአቸው ቀስ በቀስ ጨለማ እየዋጠው መጣ። ጭራሽኑ ቤት ሲገቡ መነጋገርም አቆሙ። በመካከሉ ያሉት ልጆች እንግዲህ ይታያሁዋችሁ። ነገሩ ግን እየተካረረ ሄደ። የመጨረሻ መጥፎ ሁኔታ የደረሰው ጉንደር በአደባባይ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ላይ ወያኔ እርምጃ መውሰዱ የተሰማ ጊዜ ነበር። በዚሁ ወቅት የሞተ አንድ የባል ዘመድ ነበርና ለቅሶ ይረዳል። ጉንደሬው ባል ጠላቴን የምትደግፍ ከሆነ ከጉያዬ አቅፌ አልተኛምና ሚናዋን ትለይ ይላል። እሷም በበኩሏ የአዲሱ መንግሥት ደጋፊ ናትና «እስቲ ምን አባክ ትሆናለህ» ትለዋለች። የእነሱ ሳይሆን ለአስታራቂዎችና ለሽማግሌዎች ግራ ያጋባውና ያስቸገረው የልጆቹ ጉዳይ ነበር። ምንም የመስማማት ደረጃ ላይ መደረስ ስላልተቻለ ባልና ሚስቱ ተለያይተው ልጆቻቸውን ተከፋፍለው ለየብቻ መኖር ጀመሩ እላችኋለሁ። ይህ አንድ እኔ በቅርቡ የማውቀው ታሪክ ነውና በእኔም ላይ ይደርስ ይሆን ብዬ በመጠኑ መስጋቴ አልቀረም። ሆኖም እኔም ሆንኩ ሰይፍዬ ፍቅራችንና መዋደዳችን ያበረከተልንን አንድነት፤ እንዲሁም የተገናኘንበትንና ያለፍንበትን ሁኔታ ሁሉ በደምብ ስለምናጤነውና ራሳችንን በደንብ ስለምናውቀው ብዙም አልፈራሁም። ስጋቴ በእኔ ዘመዶችም ሆነ በእሱ ጓደኞች በኩል ከውጪ የነበረው ግፊት ነው።

በመሠረቱ እኔ ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ የመገንጠልን ጥያቄ የማልደግፍ ብቻ ሳልሆን ነገሩም ጭራሽ የማይገባኝ ነኝ። ያደግሁትና የማውቀው አዲስ አበባን ነው። ለነገሩ እህቴስ እንደእኔው አልነበር አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው። ዛሬ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆኖ በወሬ እንጂ አንዲት ቀን እንኳ አይታው ለማታውቀው አገር ሽንጧን ገትራ መሟገቷን ሳስበው ይገርመኛል። የሆኖ ሆኖ እኔ ከእሷም በኩል ሆነ ከሌሎች ዘመዶቼ የሚሰነዘርብኝን ነቀፌታ ከምንም ሳልቆጥር እዚህ ደርሼ ነበር። ሰይፉ ግን ከውጪ ያለው ግፊት እየበዛበት ነው መሰለኝ አንዳንዴ ግልፍ ይልና አንዳንድ ነገሮች ይናገር ጀመር።

አንድ ቀን ምሽት ሰይፍዬ ከወትሮው ለየት ያለ ስሜት ይዞ ቤት አገኘሁት። ሌላ ጊዜ ቀድሞኝ ቤት ከገባ ገና በሩን ከመክፈቴ ተንደርድሮ መጥቶ ይስመኝ ነበር። የዛን ዕለት ግን ከተቀመጠበትም ሳይንቀሳቀስ ጠበቀኝ። እኔም አሞት ነው ብዬ በጣም በመደንገጥ ምነው ሰይፍዬ ብዬ አጠገቡ ሄጄ ልስመው ስጠጋ እጁን ብቻ ሰጠኝ። እኔ ግን እጁን ትቼ እንደተለመደው ከንፈሩን ሳምኩትና

«ምነው አመመህ እንዴ?» አልኩት።

«ምንም አልሆንኩም።» አለኝና ፊቱን ዞር አደረገ። ትንሽ ቆየና

«የት ነው የቆየሽው» አለኝ

«እንዴ ሥራ ቦታ ነዋ» አልኩት

«ከስራ ቦታ 4:00PM አካባቢ ስደውል እንደወጣሽ ነው የተነገረኝ» አለ አነጋገሩ ቁጣን ያዘለ ነበረ

«ውይ ረስቼው መንገድ ላይ ስመጣ በአጋጣሚ ከአማረች ጋር ትራፊክ መብራት ላይ ተገናኘንና እፈልግሻለሁ እንከታተል ስትለኝ ተከትያት አንድ ቦታ አቁመን ቡና እየጠጣን አወራንና ተለያየን» አልኩት ተዝናንቼ።

«አማረች ያቺ ኤርትራዊ?» አለኝ በተጠየፈ አንደበት፤

«አዎ! ኢትዮጵያ ልትሄድ አስባለች መሰለኝ፤ መልዕክት ካለኝ እንድዘጋጅ ነገረችኝ» አልኩት።

«ምን ኢትዮጵያ ትያለሽ አሥመራ አትይም» አለኝ በቁጣ፤

እስካሁን የአነጋገሩን ቁጡነት ብዙም ልብ አላልኩትም ነበር። አሁን ግን ነገር የሚፈልግ ሰው አይነት ሆኖ ተሰማኝና ቀና ብዬ አትኩሬ ተመለከትኩት።

«ምነው አየሽኝ?» አለኝ፤

«አነጋገርህ ገርሞኝ ነዋ! ምነው ሰይፍዬ የተበሳጨህበት ነገር አጋጠመህ እንዴ?» አልኩት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ባለጌ ሰዎች ስልክ እየደወሉ መሳደብ እንደጀመሩ ስለማውቅ ምናልባት ዛሬም አግኝተውት እንደሆነ ብዬ በመገመት።

«ቁጡነት እንደሌለብኝ የምታውቂ መሰለኝ ባይሆን ...» አለና ፀጥ አለ።

«ባይሆን ምን ሰይፍዬ? ወንድነት ልትለኝ ነው? ጀግና ወንድ እንደሆንክ እኔ ራሴ እመሰክራለሁ።» አልኩት በልበ ሙሉነት። ደግሞ እውነቴን ነው ሰይፍዬ ሲያዩት ከሚያስፈራው ቁመናው ጀምሮ እስከ ምግባሩ ድረስ እውነተኛ ወንድ ነበር።

«ምነው ዛሬ ያለ ወትሮሽ አፍ አበዛሽ። ሲትዮዋ ንቃት ሰጠችሽ እንዴ?» አለኝ።

«እኔ ድሮም የነቃሁ ነኝ። ይህን ታውቅ የለ ሰይፍዬ?» አልኩት። በአንድ ነገር እንደተናደደ ስለገባኝ ምንድነው ያናደደህ ብዬ በመጠየቅ ነገሩን ከማባባስ ይልቅ እንዳልገባኝ ሆኜ ለማረሳሳት የማደርገው ዘዴ ነበር። እሱ ግን የባሰ ተናደደ።

«እንድታሾፊብኝ አይደለም እኮ የምጠይቅሽ! ዛሬ የት እንደነበርሽ ብቻ ነው ከአንቺ አፍ መስማት የምፈልገው። እውነቱን!!» አለኝ።

ግራ ግብት አለኝ። ሰይፉን በዚህ ዓይነት ባህሪ አይቼው ስለማላውቅ እንዴት አድርጌ እንደማስረዳው ጨነቀኝ። ሰዎች ደውለው ወይም አግኝተውት የነገሩት መጥፎ ነገር እንዳለ አሁን ገባኝ።

«ሰይፍዬ የትም ቦታ አልሄድኩም እንደነገርኩህ ከልጅቷ ጋር ቡና ለመጠጣት ነበር።» አልኩት በማስተዛዘን።

«ስብሰባውስ?!» አለኝ በቁጣ።

«የምን ስብሰባ?» አልኩት።

«የመገንጠሉ ስብሰባ ነዋ!» አለ።

የምለው መልስ አጣሁ። መልስ ልሰጠው እችል ነበር። ነገር ግን ነገር ማባባስ ይሆናል ብዬ ንዴቱ እስኪበርድለት ድረስ ጠበቅሁ።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ዜና ቤተክርስቲያናት

## ዳግማዊ ቁልቢ በሳንዲያጐ ተከበረ



በስለት ሰሚነቱ የሚታወቀው ዳግማዊ ቁልቢ በሳንዲያጐ ዲሴምበር 22/96 (ታህሳስ 19/89) የቅዱስ ገብርኤል በዓል በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ። በካሊፎርኒያ የሚገኙ በርከት ያሉ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ መዘምራንና ምዕመናን እንዲሁም ከተለያዩ ስቴት የመጡ ብዙ እንግዶች ተገኝተዋል። የእለቱን ቅዳሴ ፕሮግራም የመሩት ብፁዕ አቡነ መልከፀዲቅ ሲሆኑ ስለዕለቱ በዓል ሰፋ ያለ ትምህርት በአባ ወልደ ትንሳኤ ቀርቧል። ለበአሉ በጋራ መዝሙር ያቀረቡት፦ 1) የበርክሊ መድኃኒያለም መዘምራን 2) የሳኖዜ ብስራተ ገብርኤል መዘምራን 3) የሎሳንጀለስ የሁለቱም ገብርኤል መዘምራን 4) የሳንዲያጐ የቅዱስ ገብርኤል መዘምራን 5) የዴንቨር የቅድስተ ማርያም መዘምራን በመሆን በህብረት ያቀረቡት መዝሙር ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል።

«አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍፁም ልባችሁ፣ በፆምና በለቅሶ፣ በዋይታ ወደእኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ። አምላካችን እግዚያብሔር ቸርና መሀሪ ቁጣው የዘገየ ምህረቱም የበዛ ለክፋትም የተፀፀተ ነውና ወደ እሱ ተመለሱ።» ( ት.ኢይ.ም.2 ቁ.12–19) እንግዲህ ንስሐ በመግባት ወደ አምላካችን እንመለስ። እግዚያብሔርን እንፍራ። በራሳችን አንመካ፤ ኃይል የእግዚያብሔር ነውና። የአምላካችን የእግዚያብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን። የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል አማላጅነት አይለየን። ወስብሐት ለእግዚያብሔር አሜን


ከመዘምራን ማህበር

## የገናና የጥምቀት በዓላት በአትላንታ በደመቀ ሁኔታ ተከበሩ።



አትላንታ በምትገኘው በሳሕሊተ ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የገናና-የጥምቀት በዓል በከፍተኛ ድምቀት የተከበረ ሲሆን በተለይ የጥምቀት በዓል በቤተክርስቲያን ባሕል መሰረት ከቤተክርስቲያን ውጪ ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰብስቦ ጠበል በመርጨት የጥምቀቱን ስርዓት የበለጠ ድምቀት የሰጠው ሲሆን በዕለቱ ከስዊድን ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን የመጡት ሊቀ ካህናት መዘምር ቅዳሴውን መርተዋል።





# ከዚህም ከዚያም!



ቺካጎ ኔቪ ፒር በሚገኘው የሕፃናት ሙዚየም ገናንና ኩዋንዛን አስታኮ በተዘጋጀው በዓል ላይ የቺካጎው ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባል ሕፃን ነቢል ሙዘሚልና የፊሊፒንስና የፊንላንድ ኮሚኒቲ ሕፃናት ከኢሊኖይ ገዥ ባለቤት ከተከበሩ ወይዘሮ ብሬንዳ ኤድጋር ጋር።

ሕፃን ነቢል በአገር ልብስና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አሸብርቆ ከመሐል ይታያል።

## የሸክላ ሥራ (CERAMICS) ኤግዚቢሽን



በሸክላ ሥራ CERAMICS የተካነችው በአትላንታ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ወ/ አስቴር ካሳ ጆንሰን ባለፈው February 1/1997 ባሳየችው ኤግዚቢሽን ኢትዮጵያውያንና የውጪ አገር ዜጐች የተገኙ ሲሆን ከሥራዋ ውጤቶች ውስጥ የሸክላ ሳህኖች፣ የቡናና የሻይ ስኒዎች፣ የአበባ ማስቀመጫዎች፣ የተለያዩ ለግድግዳና ለጠረጴዛ የሚሆኑ ጌጣጌጦችና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከእነዚህ የሸክላ ስራ ውጤቶች ሌላ ለቤት ውስጥ፣ ለሠርግና ለአንዳንድ ዝግጅቶች የሚሆኑ አበባዎች የምታዘጋጅ መሆኗን ባደረግንላት ቃለ መጠይቅ አስረድታናለች። የሥራ ውጤቶች ለማየትም ሆነ ለመግዛት በ(770)808-4053 ደውሉ።



## ያለፈውን ሰንጠረዥ የመለሱ


1. ረታ ኃ. ማርያም ከአትላንታ
2. ገብሬል መካሻ ከጃርጂያ
3. ደረጀ አሰፋ ከላስቬጋስ
4. ሰይፉ መታፈሪያ ከአትላንታ
5. በዙና ሄቨን ከሳንዲያጎ (ሞክረዋል)

(ሳያቋርጡ 5 ሰንጠረዥ በትክክል ሞልተው ለሚልኩ ሶስት እትም በነፃ እንሸልማለን)

## ያለፈው ሰንጠረዥ መልስ



# ቃላት በሰንጠረዥ



### ወደጎን

1. አውሮፓ ያለ አገር
5. አበሰለች
8. የብርሃን ጭላንጭል
9. ይቅርታ አደረገልኝ
10. ትቆማለች
12. አቅጣጫ
14. መጥፎ መጥፎ ሸተተ
15. ተያዥ ብሆን
17. አገልጋይ
19. ያልተበላሸ
21. ጥይት በወገብ መታጠቂያ
22. የሚከበር
23. ወፈር ያለ ሸንበቆ
24. አፈወርቅ ተክሌ የሚታወቅበት
26. ማመልከቻ
28. መሚዘዝ
30. ዕውቀት
32. ጽሑፍ በዓይን መቃኘት
34. በእጅ ያዝ
35. የአይደለም ተቃራኒ
36. አንዱን ትቶ ለሌላው ማገዝ
37. ሳይታሰብ

### ወደታች

1. አዳኝ
2. አለመጣደፍ
3. ጠዋት
4. ሳይወራልን
5. አመለጠችህ
6. የግራ ተቃራኒ
7. ረሃብ
9. ኣላደረግሁም ብሎ ——
11. የሚለበልብ ቅጠል
12. ከሰውነት የሚወጣ የተቃጠለ አየር
13. ማድቤት
16. ውጣ ውስጥ ተኝቶ መጓዝ
17. በጦርነት ወቅት መሪ
18. ሆድ
19. ቸር
20. አልቻሉም
22. በንቅልፍ ወቅት የሚታይ
23. ኢሉባቦር ያለ ከተማ
25. ሰው ሲወለድ ተቆርጦ የሚቀበር
26 አጥግበን
27. መኖሪያ
29. መዳፍና ትከሻ መሐል ያለ
31. ከቻይና በታች ያለ አገር
33. የ "Y" ቅርፅ ያለው እንጨት
35. ጀንዲ

መልሶን ይላኩ!!

የመጽሔቱ አባልነት ቅጽ ከዚህ ጀርባ አለልዎ።

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

| | 12 ISSUES | 6 ISSUES |
|---|---|---|
| U.S. | $30.00 ☐ | $16.00 ☐ |
| Canada | $40.00 ☐ | $22.00 ☐ |
| Europe | $56.00 ☐ | $30.00 ☐ |
| Asia | $70.00 ☐ | $38.00 ☐ |
| Institutions | $80.00 ☐ | $40.00 ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* __________

================================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* __________

================================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*




# ናዝሬት ምግብ ቤት

## NAZARETH RESTAURANT

*Authentic Ethiopian Cusine*

5291 Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083

**በቅርቡ የተከፈተው
የናዝሬት የአገር ባህል ምግብ ቤት
የተሟላ የባር አገልግሎት አለው።
ዓርብና ቅዳሜና እሁድ ምሽቶች
የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።**



**የአገርን ትዝታ የሚቀሰቅስ የባህል ምግብ ተመግቦ ምሽቱን
ከአገር ልጆች ጋር ለማሳለፍ የናዝሬት ምግብ ቤት አለላችሁ።**

**ና
ዝ
ሬ
ት**

**ብቅ ብላችሁ ጎብኙን!!
በመስተንግዷችን ትደሰታላችሁ!!
በምግባችን ጣዕምን ትረካላችሁ!!**

Phone: (404) 294-0043

**NEVER UNDERESTIMATE THE MIND OF AN ETHIOPIAN... or what he or she can do when given the freedom to be creative!!**

**⇩ This could be your business card ⇩**

**MicroMall 2000**
THE FUTURE IS NOW

LOUL ASFAW
Senior Managing Partner

(770) 991-6002 • Fax (770) 991-9533 • Toll Free (888) 6-INCOME
908 Forest Pond Drive • Marietta, GA 30068
An affiliate of MicroMall U.S.A.

**MicroMall 2000**
THE FUTURE IS NOW

KIDANE TEGEGNE
Independent Managing Partner

(214) 373-4813 • Fax (214) 373-4318 • Toll Free (888) 6-INCOME
P.O. Box 823634 • Dallas, TX 75382
An affiliate of MicroMall U.S.A.

## The result is an unparalleled business opportunity in America: The first of its kind... A HOME-BASED MALL

# MicroMall 2000 ™

**A revolutionary home-based business which provides proven solutions to many of America's problems. In the meantime, it gives you the opportunity to achieve the total financial freedom that you deserve**

**Friends...** the world is in the midst of the information revolution, and MicroMall 2000 is right in the front line. The education you once had is no longer enough to keep you competitive. You need to keep up with the changes. We are inviting you to join us in the revolution and become well informed and knowledgeable while earning high five and six figure income from diversified sources right away.

If you feel like you are trapped in an unsatisfying profession or in a dead-end job, let us show you the way out to a magnificent career that you will be proud of.

***MicroMall 2000 is:***

- *A business owned 100% by you, with Ethiopian and American partners to assist you every step of the way.*
- *A business you can run from almost anywhere and earn more money than you ever dreamed.*
- *A business which does not require large start-up capital, that you can do full or part time.*
- *A business that provides on-going support and training and offers a no risk guarantee.*

**We are looking for a few good associates and partners who have a serious interest in making money in their own business by following our proven step-by-step plan.** WE ARE NOT INTERESTED IN YOUR MONEY! WE ARE INTERESTED IN GETTING THIS LIFE CHANGING INFORMATION IN YOUR HANDS SO THAT YOU CAN START MAKING MONEY IMMEDIATELY! TAKE ACTION NOW!!!

**Name:** ____________________ **Home Phone:** ____________

**Address:** ____________________ **Work Phone:** ____________

**City/State/Zip Code:** ____________________

**Special Offer** — If you join now, you will receive a FREE training kit on "The Science of Getting Rich"

**Fax this form or call:**

**(770) 991-6002** or Toll Free **(888) 646-2663** or **(888) 6-INCOME** Fax **(770) 991-9533**

**If you live in Atlanta, Dallas, Washington D.C., Los Angeles, or the Bay Area, MicroMall 2000 will be happy to set you up in your new business right away!**

***MicroMall 2000™*** - **P.O. Box 78033, Atlanta, GA**